

# ፈለገ ጥበብ

፳፫ ዓመት ቁጥር ፪

መስከረም [illegible]



© Safeguarding Religious Treasures of the Ethiopian Orthodox Church



ዋጋ ብር 3

በንግድ ማተሚያ ድርጅት ታተመ

www.ethiopianorthodox.org

# እኛና እናንተ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

ለፈለገ ጥበብ መጽሔት ዝግጅት ክፍል እንደምን አላችሁ? የፈለገ ጥበብ መጽሔት በመጀመርያ እትሟ በጣም ብዙ ቁም ነገሮችን ይዛ ስለወጣች ከፍተኛ ትምህርት አግኝቻ ባታለሁ፤ በተለይ አባታችን ጳባቴ አርአያ ሥላሴ ከሕይወት ልምዳቸው በመነሳት የሰጡን ትምህርት ለኛ ለወጣቶች ብዙ ግንዛቤ ሰጥቶናል።

ለወደፊቱም እንዲህ ዓይነት አባቶች እየፈለጋችሁ የእምዳችሁ እንግዳ ብታደርጉዋቸው ለኛ ለወጣቶች ከፍተኛ ትምህርት ይሰጡናል። በተረፈ መልካሙን ሁሉ እመኝላችኋለሁ:- የእግዚአብሔር ቸርነትና የእመቤታችን ድንግል ማርያም ተራዳኢነት ከሁላችን ጋር ይሁን:-

ስዩም ከ.ዳኦ – ከአዲስ ከተማ

✣ ✣ ✣

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

ውድ የፈለገ ጥበብ መጽሔት አዘጋጆች:- በቅድሚያ ሰላምና ጤና እመኝላችኋለሁ፤ ዛሬ አንድ ብዩ እንድጽፍላችሁ እግዚአብሔር አነሳሳኝ፤ ድንግልም ፈቃዷ ሆነ፤ ስለዚህ አስተያየቴን ተቀበሉኝ።

፩. በመጽሔታችሁ የቀረቡት እንግዶችን አድንቄአቸዋለሁ፤ ለቤተ ክርስቲያናችን ታላቅ አስተዋጽኦ ያበረከቱ በመሆናቸው አርአያ ይሆኑናልና፤ ቢሆንም ለወደፊቱ የእንግዶቻችሁን ቁጥር ቀንስ አድርጋችሁ በየተራ ብታቀርቡዋቸው ይመረጣል።

፪. «መድፍነበር» በሚል አምድ የወጣው ጽሑፍ አርኪቶኛልና የበለጠ ትኩረት ስጡበት። መናፍቃንን ኢሳፍሮ የሚመልስ ነውና። ይህ ከሆነ አብረን እንዘልቃለን፤ የአንድዩ እናት በእማላጅነቷ አትለየን።

ዲ.አስግድ በረደድ – ቅድሥት ሥላሴ (አራት ኪሎ)

✣ ✣ ✣

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

ለተከበራችሁ የፈለገ ጥበብ መፅሔት አዘጋጆች ሰላምታዩ ይድረሳችሁ። መናፍቃንና ከሀዲያን ቤተክርስቲያናችንን ለማፍረስ ቆርጠው በተነሱበት በዚህ ዘመን ከኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን ጉን ትቆሙ ዘንድ ላነሳሳችሁ እግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይድረሰው። ከብዙ ዓመታት በኋላ ብቅ ያለችውን ቁጥር ፩ መጽሔት በእጄ ገብታ አነበብኳት። ትደግ ትመንደግ ብለናታል። ነገር ግን ለእድገቷ ይረዳ ዘንድ መመካከር ደግ ነውና ካነበብኩት ውስጥ ቢስተካከሉ መልካም ነው ያልኳቸውን ከዚህ በታች ሳቀርብ አነሳሴ ለጋራ እድገት እንጂ እንዲሁ ለመንቀፍ ብዩ አለመሆኑን እናንተ ወንድሞቼ እንደም ትረዱልኛ እርግጠኛ ነኝ።

፩. በ፮ ወር መውጣቷ ቀርቶ በየሶስት ወሩ ብትወጣ የእግዚአብሔር ቃል ለጠማው ምዕመን በረከት ትሆናለች።

፪. የዓምዶቹ ዓይነት በቁጥር ቢጨምር። ለምሳሌ በቁጥር ፩ ላይ ፬ ሰዎችን ቃለ መጠይቅ አድርጋችኋል። የሚጠየቁትን ደግሞ ከአ.አ ውጭ ካሉ አባቶችና ወንድሞችና እህቶች ጭምር ቢሆን መልካም ይመስለኛል።

፫. የሚቀርበው ጽሑፍም ሆነ ቃለ መጠይቅ መንፈሳዊ መልእክትና የአንባቢ ዎችን መንፈሳዊ ሕይወት የሚያበረታ መሆኑን እርግጠኞች ብትሆኑ መልካም ነው። ሐዋር ያው ቅዱስ ጳውሎስ በቆላ.፬፥፮ ላይ ንግግ ራችሁ ሁል ጊዜ በጨው እንደተቀመመ ይሁን እንዳለው ነገራችን ሁሉ ይህን አልፎ አለም በሚያጣፍጠው የእግዚአብሔር ቃል የታገዘ ቢሆን መልካም ነው። እንዲያው ስትቶፉ አይሁንብኝና ከመጽሔቷ የታዘብኩትን ልገን ራችሁ። ዶ/ር የማነ ካቀረቡት «የእሽናፍሬት ምስጢር» በሚለው ጽሑፍ የዶ/ር ዶሪስ ስም ከ፲፰ ጊዜ በላይ ሲጠቀስ የእግዚአብሔር ስም ግን አንድም ጊዜ አልተጠቀሰም። ይህ ስል የጽሑፉን ጠቃሚነት መካዴ ሳይሆን ከዓለ ማዊ መጽሔቶች የሚለየውን መንፈሳዊ ቃና ስላጣሁበት ነው።

ከአርበኛው መነኩሴ ጋር ባደረጋች ሁትም ቃለ መጠይቅ አንዳንድ ከመንፈሣዊ ሕይወት ጋር የማይገናኙ ጥያቄዎች ጠይቃ ችኋል። ለክርስቲያን የ፲፱፻፺፫ ዓ.ም መፈንቅለ መንግሥት ሂደት፤ የጄኔራሎቹ ባሕርይ ወይም የኮሪያ ጦርነት ገጠመኝ ምኑ ነው? ይልቁንስ መንፈሣዊ ተጋድሎአቸውን ብታስ ነብቡን ለኛ ለወጣቶቹ ትምህርት በሆነን ነበር።

ይህን ያልኩበት ምክንያት በአሁኑ ዘመን እንደ አሸን ለፈሉት የቤተ ክርስቲያን ተቃዋሚዎችና ከሀዲያን ተጨማሪ የዘለፋ በር ይከፍታል የሚል ስጋት ስላደረብኝ እንጅ ነቀፋ ለማትረብ አይደለም።

በተረፈ እግዚአብሔር የቃሉን ደጅ ይከፍትላችሁ ዘንድ የእናቱ የቅ/ድ/ማርያም ምልጃ የቅዱሳን ተራዳኢነት አይለያችሁ አይለየን አሜን።

ወሰብሐት ለእግዚአብሔር

ደረጀ አሸብር – መቀሌ ዩንቨርሲቲ ደብረ ንፃሬ እንዳኢየሱስ ሰንበት ት/ቤት

✣ ✣ ✣

ለፈለገ ጥበብ መጽሔት አዘጋጅ

አዲስ አበባ

መናፍቃን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነትን ለማፋለስ ከመቼውም በበለጠ ሁኔታ ውር ውር በሚሉበት በአሁኑ ወቅት ፈለገ ጥበብ መጽሔት የበሰሉ ትምህርት አዘል መልእክቶችን ይዛ ብቅ በማለት ማስተማር መጀመርዋ የሚያስ መሰግናት ነው። እከራረሟ እንደ ጅምርዋ ያማረ እንደሚሆን ተስፋ አለኝ።

ነቢዩ ኤ.– (አ.አ)

✣ ✣ ✣

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!

ሰላምና ጤና ይስጥልኝ የፈለገ ጥበብ መጽሔት አዘጋጆች፤ ከሁሉ በፊት መጽሔት በቋሚነት ለማዘጋጀት በማሰባችሁ እጅግ ተደስቻለሁ። ከምንም በላይ ከምንም በፊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክር ስቲያን ሕፃናትን፤ ወጣቶችንና ወላጆችን በአንድነት ሊያገኝ የሚችል መጽሔት ያለማቋረጥ ሊወጣ ይገባዋልና። በዚህ አጋጣሚ በአባቶቻችን ዘመን የነበረውን የሬድዮ ፕሮግራም ተመልሶ መንፈሳዊ መልእክቱን በየቤታችን ሳለን በጆሮአችን ለመስማት ያብቃን እላለሁ። ከዚህ ሌላ:-

ቃለ መጠይቅ አምዶቻችሁ ቀንስ አድርጋችሁ በምትኩ ጥሩ ጥሩ ትምህርቶች፤ ምክሮች፤ አባባሎች፤ ብታክሉበት ይመረ ጣል። ሥርዓተ ቤተክርስቲያንና ክብረ ቅዱሳን በተመለከተ የቀረቡት ጽሑፎች ወድጃቸዋለሁ በተረፈ መጽሔታችሁ በየ ፮ ወሩ የመሆኑ ጉዳይ ያሳስባል፤ ስለዚህ ቢቻል በየ፪ወሩ ካልሆነም በየ ፫ ወሩ ቢሆን እጅግ የምረጣል።

መክሊት – አዲስ አበባ

✣ ✣ ✣

ከአዘጋጁ – በደብዳቤ፤ በአካል በመምጣትና ስልክ በመደወል አስተያየ ታችሁን ላካፈላችሁን፤ ምክራችሁን ለለገሳች ሁን ሁሉ እናመሰግናለን። በእናንተ በአንባ ብያን አስተያየት ተመርኩዘን ድክመቶቻችንን ለማረም ሞክረናል። የመጽሔትዋ ኅትመት ቢተመለከተም በየ ፮ ወሩ መሆኑ ቀርቶ በየ ፫ ወሩ እንዲሆን አድርገናል። ፈለገ ጥበብ የናንተ ናትና ነገም ተነገ ወድያም የናንተ ድጋፍና አስተያየት እንፈልጋለን። የአንባብያን ተሳትፎ የብርታታችን ማገርና ዋልታ ነውና።

## ቃለ በረከት



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት በተለያዩ ጊዜያት ካስተላለፉት ቃለ በረከት

የተወሰዱ ምርጥ ጥቅሶች

«ማዕርግ በሥራ ካልታገዘ ዋጋ የለውም፤ እያንዳንዳችን የደረብነው የክብር ካባ በሥራ ካልተደገፈ ማፈሪያችን ነው። ...ስለዚህ አደራችሁን እኛ መሥራት ያለብን አሁን ስለሆነ እንሥራ...ነገ የኛ አይደለም ትናንትም የአባቶቻችን ነበር።»

(የቅዱስ ራጉኤልን ትንቤት መርቀው ሲከፍቱ በተለይ ለደብር አስተዳዳሪዎች ካስተላለፉት ቃለ በረከት፤ ሐምሌ ፮ ቀን ፲፱፻፺፩ዓ.ም)

✣ ✣ ✣

«አሁን ስላለፈው ጊዜ እያለቀስን የምናባክነው ጊዜ የለንም፤ ዛሬ ሁሉም በእጃችን ነው፤ ለባሕላችን፤ ለታሪካችን፤ ለሃይማኖታችን፤ በፈቃደኝነት፤ በኅብረት ሆነን የሚያስፈልገንን የምናሟላበት ወቅት ነው። ይህች የምንሳሳላት ቤተ ክርስቲያን መለያ ምልክቷ ሰላም፤ ፍቅር፤ አንድነት ነው። ይህ ደግሞ ዛሬ የተከሰተ ሳይሆን አብሯት የነበረ የዘመናት ዓላማዋ ሆኖ የቆየ ነው። ስለዚህ ሁላችንም ሥራችንን በጥራት ከሁሉም በላይ ከውስጣዊ ስሜት በመነጨ ፈቃደኝነት በመሥራት አገልግሎታችንን ለማበርከት መዘጋጀት አለብን።»

(ሐምሌ ፫ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም አዲሱ ጽርሐ መንበረ ፓትርያርክ ሕንፃን ባርከው ሲከፍቱ)

✣ ✣ ✣

«አባቶቻችን የተውሶ ታሪክና ሃይማኖት አላወረሱንም፤ ከውጭ የተቀበሉት፤ የተበደሩት፤ የተከለሰ ሃይማኖትና ታሪክ የላቸውም፤ ቤተ ክርስቲያናችንም የታሪክና የሃይማኖት ምንጭና ዐምድ ናት፤ የጌታን ሕግና ሥርዓት ሳታፋልስ፤ ሳታዛባ የያዘች ሃይማኖት ናት። እኛ የምንከተለው ሃይማኖት ጌታችን ያስተማረው፤ ሐዋርያት የደነገጉት፤ አባቶች ያጸኑት የተጣራ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት ነው። እኛ የምንከተለው መጽሐፍ ቅዱስን ነው። መታደስ መሻሻል ያለበት የተሳሳተ ነገር ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ግን ምን ጊዜም እውነት ነው፤ እውነት ደግሞ አይሰለችም፤ አይለወጥም፤ አይታደስምም።»

«ኢትዮጵያውያን የማያኮራ፤ የማይታወቅ፤ ተድበስብሶ የሚታለፍ ታሪክና ሃይማኖት የላቸውም። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምትከተለው ሃይማኖት የእግዚአብሔር ሥራ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ነው። በእድርተኛ የተቋቋመ፤ አቶ እገሌ ወይዘሮ እገሊት በዚህ ቦታ ሄደው አቋቋሙት የሚባል የማኅበር ሃይማኖት ወይም ደግሞ በኮሚቴ የተሻሻለ፤ የተቀየጠ ሃይማኖትም አይደለም። ከመጀመሪያው፤ ከመነሻው ጀምሮ በማይናወጥ የክርስቶስ መሠረት የተቋቋመ ነው። ለዚህም ነው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የጠራ እምነቷን ሳትለውጥ በሺዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት ጸንታ የቆየችው። የሚሻረው የሚለወጠው የሰው ሥራ ብቻ ነውና።»

ጥር ፲፩ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም በዓለ ጥምቀት

www.ethiopianorthodox.org

# ፈለገ ጥበብ

፪ኛ ዓመት ቁጥር ፪
መስከረም ፲፱፻፺፪

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ቤተክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች
ማደራጃ መምሪያ
በየ፫ ወሩ የሚዘጋጅ መጽሔት

## ከአዘጋጁ ብዕር

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤

በቁጥር ፩ ፈለገ ጥበብ መጽሔት ከእናንተ ጋር ለመገናኘት የመንፈቅ ቀጠሮ ተሰጣጥተን ነበር የተለያየነው። ይሁንና በእግዚአብሔር ፈቃድ፤ በእናንተ ጸሎትና ድጋፍ ፈለገ ጥበብን ከአንባቢዎቿ ጋር በየ ፫ ወሩ ለማገናኘት ወሰን። ለዚህ መነሻችን የናንተ ጥያቄ ነውና በውሳኔው እንደምትደሰቱ እርግጠኞች ነን።

ፈለገ ጥበብ ያለፈ ድክመትዋን አሻሽላ በአዲስ ዓመት፤ በአዲስ አቀራረብ ብቅ ብላለች። አራት ዓይና መልአከ ገነት ገብረ ሥላሴን ጨምሮ ከቤተክር ስቲያናችን እውቅ ሊቃውንት የተበረከቱ መንፈሳዊ የእውቀት ስንቅ ሰንቃ እነሆ ትላችኋለች። «ከወጣቱ ለወጣቱ» በሚለው ቋሚ አምዳችን ከታዋቂው ሻለቃ ኃይሌ ገ/ሥላሴ ጋር «እናስተዋውቃችኋለን»

ከዚህ በተረፈ የጐደለውን ለመሙላት፤ የጠበበውን ለማስፋት አሁንም የናንተን ተሳትፎ እንጠብቃለን። ዘመኑ ዘመነ ሰላም፤ ዘመነ ምሕረት፤ ዘመነ በረከት ያድርግልን አሜን።

## ማውጫ

❖ ቃለ በረከት . . . . . . . . . ፩
❖ የአብርሃ ወአጽብሐ መስቀል ፫
❖ መድፍነ ፀር
ምሥጢረ ሥጋዌ . . . . . . . ፬
❖ ቅዱስ መስቀል . . . . . . ፳
❖ ወጣቱና ቤተክርስቲያን . . ፲
❖ ከወጣቱ ለወጣቱ . . . . . . ፲፫
❖ መልካም እረኛ እኔ ነኝ . . . . ፲፮
❖ እኔም ወጣት ነበርኩ . . . . . ፳
❖ ትምህርተ ሃይማኖት
ትምህርተ ተዋሕዶ . . . . ፳፭
❖ እስትጉቡእ . . . . . . . . ፳፰
❖ የዘመን አቆጣጠር .
ዓመተ አዳም ወኖኅ . . . . . . ፴፩

ስልክ ፲፩– ፳፫–፳፱
ፖ.ሣ.ቁ.፹፩ ሺህ ፪ መቶ ፹፮
አዲስ አበባ

አዘጋጅ:- ካሕሳይ ገ/እግዚአብሔር
ኤዲተሮች:- ሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ ዓለማየሁ
ቀሲስ በላይ ተገኝ
መጋቤ ብሉይ ሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ


# ስለ ገባሬ ተአምር የአብርሃ ወአጽብሐ ገዳም የወርቅ መስቀል ምን ያህል ያውቃሉ?

ይህ መስቀል የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ አባ ሰላማ ከአብርሃ ወአጽብሐ ጋር በመሆን የኢትዮጵያን ሕዝብ ያጠመቁበት ታሪካዊ መስቀል ነው። አባ ሰላማ፤ አብርሃ ወአጽብሐና ከነሱ በኋላ የነበሩ ቅዱሳን አበው በዚህ ገባሬ ተአምራት መስቀል በርካታ ገድል ፈጽመዋል። በዚህ መስቀል እጅግ በርካታ መኻኖች የልጅ ፍሬ አግኝተዋል፤ ዓይነ ሥውራን ብርሃን ለማየት ችለዋል፤ ወዘተ...

በአጭሩ የዚህ ገባሬ ተአምራት መስቀል ታሪክ ለመዘገብ ራሱን የቻለ መጽሐፍ ማዘጋጀት ያስፈልጋል። ለአሁኑ ግን አንድ ሁለቱን እናካፍላችሁ።

ሀ. አፄ ምኒልክ ኢጣልያን ለመውጋት ወደ አድዋ ሲዘምቱ አንድ ቀን የአብርሃና አጽብሐ ገዳም አጠገብ ከምትገኝ አጉላ ከምትባል ቦታ አረፉ። በዚህን ጊዜ ታላቁና ታሪካዊ ገዳም እዛ አካባቢ እንደሚገኝ ሰምተው ማንም ሰው ቤተ ክርስቲያኑን እንዳይነካ ለመኳንንቶቻቸው ትእዛዝ አስተላለፉ።

ይሁንና የንጉሡ ትእዛዝ ከመድረሱ በፊት እግረኛ ወታደሮች የአብርሃ ወአጽብሐ ገዳምን ዘረፉት። ንጉሡም ይህንን በሰሙ ጊዜ የተዘረፉት እቃዎች በሙሉ ወደ ቦታቸው እንዲመለሱ አደረጉ። ነገር ግን የአብርሃና የአጽብሐን መስቀል የወሰደ አንድ የወረኢሞኑ ወታደር (የደጃዝማች ሊበን አሽከር) የእስልምና እምነት በልቡ ነበርና የካህናት ግዘት አያስርም፤ የንጉሥም ትእዛዝ ምንም አይጐዳም በማለት መስቀሉን ደብቆ ሀገሩ ገባ። በዛም መስቀሉን ሸጦ በሀብት ለመክበር ከቤተሰቦቹ ጋር ተመካክሮ ወሰነ። ይሁንና መስቀሉን ወስዶ ለመሸጥ በተሰናዳበት ጊዜ ድንገተኛ በሽታ በቤቱ ገብቶ በመጀመሪያ መስቀሉ የሰረቀውን ወታደር ቀጥሎም ቤተሰቦቹ እንዳሉ አለቁ።



ከዚያ በኋላ የሟቹ ወታደር ዘመዶች ወንድማችን ያመጣውን የወርቅ መስቀል እንወስዳለን ብለው ከሩቅ አገር መጡ። ከመጡ በኋላ ግን እኔ እወስድ እኔ እወስድ ሲሉ ተጣልተው ለዳኝነት ደጃዝማች ሊበን ዘንድ ቀረቡ። ከዛ መስቀሉ የአብርሃና ወአጽብሐ መስቀል መሆኑ ታወቀ። ጉዳዩም ንጉሡ ንጉሥ ምኒልክ ዘንድ ደርሶ በታላቅ ክብር ወደ ገዳሙ እንዲመለስ ሆነ።

ለ. ሁለተኛው ተአምር ደግሞ በራስ ጉግሣ ጊዜ የተፈጸመ ነው። ከወርቅ መሠራቱን የሚያውቁ አንጠረኞች መስቀሉን ሰርቀው ተሰወሩ። ይሁንና ወስደው በእሳት ሊያቀልጡት ሲሞክሩ የተለያዩ ተአምራት እያሳየ ስላስቸገራቸው ለገንዘብ ብለን ሕይወታችን ከምናጠፋ ይቅርብን ብለው መስቀሉን ወስደው ለራስ ጉግሣ አስረከቡ።

እንደ አጋጣሚ ሆኖ በወቅቱ ከሌቦች የተያዙ በመልክና በቅርጽ ተመሳሳይ የሆኑ ሌሎች መስቀሎችም ስለ ነበሩ የአብርሃ ወአጽብሐ መስቀል በትክክል የትኛው እንደ ሆነ ለመለየት አስቸገረ። በዚህን ጊዜ ራስ ጉግሣ «ከእነዚህ መስቀሎች አንዱ የአብርሃ ወአጽብሐ መስቀል ከሆነ ራሱ ምልክት ያሳያልና (ተአምራት ይሠራልና) ሁሉንም መስቀሎች አምጡልኝ» ብለው ካስመጡ በኃላ መስቀሎችን ጠረጴዛ ላይ ደረደሩዋቸው። በዚህን ጊዜ የአብርሃ ወአጽብሐ መስቀል ውሃ ማመንጨት ጀመረ። ከዛ በፊትም መስቀሉ ተመሳሳይ ተአምራት ያሳይ ስለ ነበረ መስቀሉ በትክክል ራሱ መሆኑ ታውቆ ወደ ገዳሙ እንዲመለስ ተደረገ።

በአንድ ወቅትም መስቀሉን ይዘው ይቀድሱ የነበሩ አንድ ቄስ ባልታወቀ ምክንያት ድንገት መሬት ላይ ሲወድቁ መስቀሉ ማንም ሳይነካውና ሌሎች ካህናት መጥተው እስኪይዙት ድረስ በመጸሩ ላይ እንዳለ በወለሉ ላይ ቀጥ ብሎ ቆሞ ቆይቷል። በነገራችን ላይ ለመስቀሉ ክብር ሲባል የአብርሃ ወአጽብሐ መስቀል ከካህን በስተቀር ዲያቆን እንዲይዘው አይፈቀድለትም።

ከፈልግ ምንጭ ታሪክ ነገሥት አብርሃ ወአጽብሐ ከሚል በሊቀ ካህናት ኃይለ ሥላሴ ዓለማየሁ የተዘጋጀ መጽሐፍ ❖



www.ethiopianorthodox.org

# ዘወደፍኑ ፀር

ይህ ዓምድ መናፍቃንና አጽራረ ቤተክርስቲያንን የሚያጋልጡ ጽሑፎች የሚቀርቡበት የእመቤታችን፣ የጻድቃንና የሰማዕታት አማላጅነት፣ ተራዳኢነት የሚተነተንበት ይሆናል።



ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ፣ ጋር በጽርሐ አርያም በመጽሔተ ብርሃን፣ በሚታዩበት ምሥጢር ለመላእክት ታይቶአል፤ እንግዲህ መናፍቃን ይህን ሳይገነዘቡ ማለደ ይላሉ፤

መልአከ ገነት ገብረ ሥላሴ አወቀ በአሁኑ ጊዜ በቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ ት/ቤት የመጽሐፍተ ብሉያት መምህር ሆነው በማገልገል ላይ ናቸው። መልአከ ገነት ገብረ ሥላሴ የቅኔ፣ የመጻሕፍተ ብሉያትና ሐዲሳት፣ የመጻሕፍተ ሊቃውንት ትርጓሜ፣ የመጻሕፍተ ሕግጋት፣ የድጓና የአቋቋም አብነት፣ በአጠቃላይ እንደ ቀደምት አባቶቻቸው አራት ዓይና ተብለው የሚጠሩ የቤተክርስቲያናችን የእውቀትና የምሥጢር ቋሚ መድብል (መዝገብ) ናቸው።

መልአከ ገነት ገብረ ሥላሴ ለዛሬ በኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት አርዮሳውያንና የሉተር ተከታዮች በሚያነሱዋቸው የኑፋቄ ጥያቄዎች ዙርያ ሰፊ ትምህርት ይሰጡናል።

## ምስጢረ ሥጋዌ

«ወውእቱ ቃል ሥጋ ኮነ፣ ያ ቃል ሥጋ ኾነ» ዮሐ.፩፥፲፬።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ «ኮነ ሰብእ ዘእንበለ ኃጢአት ባሕቲታ ከኃጢአት በቀር ሰው ኾነ»፣ ሰው በኾነ ጊዜም የሰውነት ሥራ ሠራ። የሰውነት ሥራ ማለትም አስተማረ ማለት ነው። የሰውነት ሥራ ሠራ ማለት አምላክነቱን፣ ምልእቱን ስፋቱን ርቀቱን ለቆ ሰው ሆነ ማለት አይደለም። አልተለወጠም እመቤታችን ታቅፋው ሳለ፣ በመንበረ ክብሩ በጽርሐ አርያም አለ። ሰው መሆኑ ስፋቱን ምላቱን ርቀቱን አይወስነውምና ከመንበረ ክብሩ አልተለየም። «ወሶበርአዩ እግዚአሙ ዘአስተጋብአ ኵሎ ፍጥረታተ እንዘ ይነብር ውስተ ኀፅንኪ...ኀሠሥዎ ውስተ አርያም ወበህየ ረከብዎ ምስለ አቡሁ ወመንፈስ ቅዱስ ከመትካት» እንዲል።

አይደለም፣ የሰውነት ሥራ ሠራ ማለት፣ ትምህርት ይባላል እንጂ ምልጃ አይባልም «አፍቅሩ ጸላእተክሙ» ጠላቶቻችሁን ውደዱ ብሎ አስተምሯል። አንድ እውነተኛ መምህር ያንን የሚያስተምረውን መሥራት አለበት፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ጠላቶቻችሁን ውደዱ ያለውን በመስቀል ላይ ገለጠው። ለንጊኖስ ጐኑን ሲወጋው ደሙ ተፈናጥቆ ዓይኑን ቢነካው ጠፍቶ የነበረ አንዱ ዓይኑ በግ ብሎ በራለት። ዮሐ.፲፱፥፲፯–፴፬።

ኀቢ ምእትም (የመቶ አለቃ) እንደዚያ የመግነዙን እራፊ አንስቶ ዓይኑን ቢያሽው ዓይኑ በርቶለታል። አምላክነቱን አልለቀቀም። «አፍቅሩ ጸላእተክሙ» ጠላቶቻችሁን ውደዱ ያለውን ለመፈጸም ጐኑን የወጋውን ዓይኑን ማብራት፣ «አባ ሥራይ ሎሙ እስመ ዘኢየአምሩ ይገብሩ» እነዚህ አላዋቂዎች ናቸውና አባት ሆይ ይቅር በላቸው ማለቱ እናንተም ጠላቶቻችሁን ውደዱ። ሃይማኖታችሁን ካዱ ብለው እንዲህ መከራ ቢያጸኑባችሁ፣ እንደ በደሉን እንበድላቸው አትበሉ፤ መከራውን ታግሣችሁ ተቀበሉት ሲለን ነው። ሰግዱ ስገዱ፣ ጸልዩ ጸልዩ ጾሙ ጹሙ፣ የሐዋርያትን እግር አጥቦ የባለ እንጀራችሁን እግር እጠቡ ትሕትናን ገንዘብ አድርጉ ብሉናል።

ጌታችን የሠራው ሁሉ ለኛ አብነት ሆኖናል። ይህ ሁሉ ትምህርት ይባላል እንጂ ምልጃ አይባልም። «ኮነ በኵረ ወጥንተ ለኵሉ ምግባረ ሠናይ፣ ለበጎ ሥራ ሁሉ መሪ ሆነን» እንዲል። (ዮሐንስ አፈወርቅንና ቄርሎስን ተመልከት።)

መናፍቃን፣ ጥልቀት ያለውና ምሥጢራትን በትክክል የሚመረምር ትምህርትና መንፈሳዊ ዕውቀት ስለሌላቸው፣ አምላክነቱን ምላቱንና ርቀቱን በአጠቃላይ መለኮታዊ ባሕርዩን ለቆ ወይም ተለውጦ ሰው ብቻ የሆነ ይመስላቸዋል። የሰውነቱን ሥራ ይዘው ይኳዛሉ።

ለእኛ ይከራከርልናል ስለመባሉ እንደሆነም መንፈስ ቅዱስንም «ወይትዋቀስ በእንቲአነ » ይለዋል «ወይትዋቀስ በእንቲአነ» ስለ እኛ ይከራከራል ያለውን አረጋዊ መንፈሳዊ ሲተረጉም። «ያጸሊ ለነ ርእሰነ» እንድንጸልይ ያደርገናል፣ ያተጋናል፣ በጎ ሥራ እንድንሠራ ያደርገናል ማለት ነው እንጂ። «ዓርገ ውስተ ሰማያት ወነበረ በየማነ አቡሁ» ወደ ሰማያት አረገ፣ በአባቱ ቀኝ ተቀመጠ፣ ካለ በኋላ ዛሬ ምልጃ የለም። ከዕርገት በፊት የሠራውም ሥራ ትምህርት ነው እንጂ ምልጃ አይባልም።

ከአረገ በኋላ የሰውነት ሥራ ሠራ የሚል ሰው አእምሮን ያጣ እንስሳ ይባላል፤ ነቢረ የማንስ ያኤምር ኀበተዋሕዶቶሙ በክብር «በአብ ቀኝ ተቀመጠ ማለትስ በክብር ትክክል መሆናቸውን መናገር ነው።» ብሎ ዮሐንስ አፈወርቅ ተርጉሞታል። ስለዚህ፣ ይትዋቀስ በእንቲአነ ማለት እንድንተጋ፣ እንድንጸልይ ያደርገናል ማለት ነው። የአብ የወልድ፣ የመንፈስ ቅዱስ ፈቃዳቸው አንድ ነው። አብ ልብ፣ ወልድ ቃል፣ መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ፣ ናቸው። እንደ አንድ ሰው ይሠራሉ እንጂ ማላጅ ተማላጅ የለም። ሰው ልቡን ይኽ ያለማኛል ይኽ ያጠፋኛል ብሎ የወደደውን ይሠራበታል እንጂ ለልቡናው ጉብ አይሰጥም፣ አይሰግድም፣ አይለምንም። አብ ልብ እንደሆነ «ወህየንተ ልብ ነአምር ለአብ ከመ ውእቱ አብ፣ ወህየንተ ቃል ነአምር ለወልድ ከመ ውእቱ ቃል፣ ወህየንተ እስትንፋስ ነአምር ለመንፈስ ቅዱስ ከመ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ፣ በልብ ፈንታ አብ ልብ እንደሆነ እናውቀዋለን። በቃል ፈንታ ወልድ ቃል እንደሆነ እናውቀዋለን። በእስትንፋስ (በሕይወት) ፈንታ መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ (ሕይወት) እንደሆነ እናውቀዋለን።» ብሎ ሊቁ በሃይማኖተ አበው መድቦታል።

ይኽ የመሰለው አብ ልብ፣ ወልድ ቃል፣ መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ፣ የተባለው፣ እዎ እንደ ሰው በልቡ እሚያስበውን የአብ አካል ይሠራል። በቃሉ እሚናገረውን የወልድ አካል ይሠራል፣ በእስትንፋሱ የሚሠራውን የመንፈስ ቅዱስ አካል ይሠራል። እንደ አንድ ንጉሥ ይሠራል እንጂ፣ በፈቃድ መለያየት የለም። አንዱ አንዱን አይቀድመውም «ኢይቀድም አሐዱ አምካልዑ ወካልዑ አምሣልሱ» አንዱ (አብ) ከሁለተኛው (ከወልድ)፣ ሁለተኛው (ወልድ) ከሦስተኛው ከመንፈስ ቅዱስ አይቀድምም እንዳሉ ሰለስቱ ምዕት ፩፥፩ ሃይማኖተ አበው) ይኸ ነው እንጂ፣ አንዱ ማላጅ አንዱ ተማላጅ ከተባለ ይኸውማ አንደኛውንም ምሥጢረ ሥላሴ ሁሉ ፈርሶ፣ ሰው ሲሆን ተለውጦ ሰው ሆኖአል። አምላክነቱን ለቆአል ማለት ጭምልቅልቅ ያለ ትምህርት ነው።

ታዲያ አማላጅነት የሚለው ቃል ትርጉሙ ምንድነው? የተባለ እንደሆነ፣ ምልጃ የሚባለው ለወዳጆቹ ለፍጡራን፣ «ዘሐነጸ ለከ መርጡለከ እምሕርለከ» ቤተክርስቲያን የሠራልህን እምርልሕ አለሁ፣ «ዘአስተየ ጽዋዓማይ ቁረር በስመ ረድዕየ እማን እብለከሙ ኢየኀጉል እስበ «በደቀመዝሙር ስም ስለአምላክ ጴጥሮስ፣ ስለ አምላክ ጳውሎስ ብሎ፣ ስለ አምላክ ዮሐንስ ብሎ የሰጠ ዋጋውን አያጣም» ብሎ የሰጠው ቃል ኪዳን ነው። (ማቴ.፲፥፵–፵፩)። ጽዋዓ ማይ ያለው ዝክሩን ነው። እመቤታችንም «ወከዕበ ተማኅፀነ በማርያም እምከ እስመ እንተ ትቤላ ዘጸውዓ ሥመኪ የሐዩ ሕይወተ ዘለዓለም» ሲል መንፈስ ቅዱስ ከሕፃንነቱ ጀምሮ ያደረበት ያዕቆብ ዘሥሩግ ገልጦታል። እነሱ ምልጃ የለም መስኂቸው አዋልድ መጽሐፍ አንቀበልም፣ የቤተክርስቲያን መጽሐፍ አንቀበልም፣ ብለው ወድቀዋል። «እንዘ ይጠበቡ አብዱ» ይላል ቅዱስ ጳውሎስ፣ የተራቀቅን መስኂቸው የእግዚአብሔርን ወዳጆች ሊያዋርዱ ይፍጨረጨራሉ። ለምን መረጥካቸው ተብሎ እግዚአብሔር አይጠየቅም። ለምን ጨለማ ፈጠርክ? ለምን ብርሃን ፈጠርክ? ብሎ መጠየቅ ድንቁርና ነው። እናም እመቤታችንን አከብሮአታል። በተቻለን በስምዋ እንዘክራለን። ታማልደናለች «ሰዓሊ ለነ ቅድስት» እያልን እንለምናታለን። ጻድቃንም ይኸው በሰጣቸው ቃል ኪዳን መሠረት እንዲያውም «ዘጸውዓ ስመ ወለቱ እው ስመ ወልዱ፣ አልህቀ» በስምህ ሴት ልጁን ወንድ ልጁን የጠራ አሣድገዋለሁ ብሎታል፤ አባ እክሉግ ለሚባለው ቅዱስ ቃል ኪዳን ሲሰጠው። አክሉግ ብሎ በአንተ ስም ዓለማዊ ስም የጠራ እምርልሃለሁ አለው። አንድ ሰው የወደደውን ልጅ ጊዮርጊስ፣ ሚካኤል ቢለው የክርስትና ስም አይሆንም። የዓለም ስም ይሆናል። ሲሳሉለት ታቦቱም ይሰማል፣ በሕዝቡ በኩልም አንዳንድ ጥፋት አለ፣ መምህራንም ዝም ብለው ያያሉ፣ አይጥ እየተሳለ፣ እባብ እየተሳለ፣ ቁልቢ ገብርኤል የሚሄድ አለ። ለዛፍም የሚሰግድ አለ፤ ይኸንን መምህራኑና ጳጳሳት ተው ማለት ይገባቸዋል።

አሁን መናፍቃን ሳይገባቸው እንደመነሻ አድርገው ኢየሱስ ክርስቶስ ዛሬም ይማልዳል ለማለት ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚጠቅሱት ጥቅስ ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ ከታቡ ምዕራፍ ፰ ቁጥር ፴፬ ላይ «ክርስቶስ ኢየሱስ ዘሞተ ወተንሥአ እሙታን ወሀሎ ይነብር በየማነ እግዚአብሔር ወይትዋቀስ በእንቲአነ» የሞተው ይልቁንም ከሙታን የተነሣው በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው» የሚለውን ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስን አማላጅ የሚሉ ያልተማሩ፣ እንድያው በስም ብቻ ክርስቲያን የተባሉ ናቸው፤ ይህንን የሚናገሩትን ክርስቲያን አይባሉም። እነዚህ ማላጅ ነው ሲሉ ፈራጁስ ማነው? «ሑሩአምኔየ» «ከእኔ ወግዱ» የሚል ማነው? ቢኋቸው መልስ አያገኙም (ማቴ.፳፭፥፵፩) አብ ይፈርዳል እንዳይሉ «እስመ አብሰ ኢይኮንን መነሂ አላ ኵሎ ኵነኔሁ አወፈዮ ለወልዱ» አብስ በማንም በማን አይፈርድም፤ ፍርድን ሁሉ ማስተማሩን ይኸ ሁሉ በልጁ (በወልድ) ሕልው ሆኖ ሠራ እንጂ አብ አይፈርድም ይልባቸዋል። (ዮሐ.፭፥፳፫)።

መንፈስ ቅዱስ ይፈርዳል እንዳይሉም መንፈስ ቅዱስ ሥጋ አልለበሰም። ሥጋ የለበሰው ኋላ ሰማይን እና ምድርን ለማሳለፍ የሚመጣው በክበበ ትስብእት የታየው የወልድ አካል ነው። የመንፈስ ቅዱስ አካል ደግሞ ለእኛ አይገለጥልንም። እና ስለዚህ ፈራጁን ማላጅ ነው ማለት የክሕደት ክሕደት ነው። ወይም የሐዋርያትን ትምህርት አልቀበልም ማለት ነው። ሐዋርያት የሰውነቱንም የአምላክነቱንም ነው የሚያስተምሩት እንጂ፤ የሰውነቱን ሥራ ብቻ ይዞ አማላጅ ነው ማለት አላዋቂነት ነው።

አምላክነቱን አልለቀቀም ሰው ሆኖ ሳለ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሳለ «አንተ ንቡር ዲበ አርያም ወአንተ ስቁል ዲበ ዕፀ መስቀል» በላይ በጽርሐ አርያም እንዳለ፣ በዕፀ መስቀል ላይ አለ፤ በአካል ነፍስ ደግሞ ወደ ሲኦል ሄዶ ነፍሳትን አወጣ ምልዓቱን ስፋቱን ርቀቱን፣ አምላክነቱን አልለቀቀምና።

በሌላ በኩል ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ፣ «ወልድኒ ይገኒ ለዘአግነዩ ሎቱ ወልድም ላስገዛለት ይገዛል» ይላል ብለው (፩ኛ ቆሮ ፲፭፥፳፰) ይህን ዓረፍተ ቃል እንደ መነሻ አድርገው፤ ወልድ በባሕርዩ የተገዢነት ባሕርይ እንዳለው አድርገው ያስተምራሉ።

የዚህ ቃል ትክክለኛ ትርጉም ደግሞ ለፍርድ በሚመጣበት ጊዜ ሁሉን ላስገዛለት ለሞት ይገዛል ማለት፤ ለሞት የሚገዛ ሆኖ አይደለም የዚያን ጊዜ ለአዳም ልጆች የሠራውን፤ የካሰውን ካሣ፤ ይህን ዓለም ለማሳለፍ ሲመጣ ይገለጣል ማለት ነው። በዕለተ ዓርብ የሠራውን በዕለተ ምጽአት

www.ethiopianorthodox.org

ይገልጠዋል ማለት ነው። «እንዘ መስቀልየ የሐውር ቅድሜየ» እንዲል፤ የተሰቀለበትን መስቀል መላእክት ተሸክመው የተወጋበትን ጦር፤ የተቸነከረበትን ቅንዋት ይዘው ይታያሉ። እንግዲህ ለአዘክሮ በቀል እናንተ እኔ እንዲህ አድርጌ መከራ ተቀብየ፤ መከራ ተቀበሉ ብየ አስተምሬ ክርስቲያን ነን ብላችሁ ይኸንን አፈረሳችሁ? ብሎ ሐጥአንን ወቅሶ «ሑሩ እምኔየ» «ክእኑ ወግዱ» ይላል። መከራ የተቀበሉትን፤ ትምህርቱን የተቀበሉትን በሃይማኖት የጸኑትን፤ እነዚህን «ንዑ ኀቤየ ቡሩካኑ ለአቡየ» የአባቴ ቡሩካኑ ወደኔ ኑ ብሎ ብርሃን አልብሶ ወደ መንግሥተ ሰማይ ያገባቸዋል። እና ያንን በዕለተ ዓርብ ለአዳም ልጆች ያደረገውን ውለታ (ካሣ) በምጽአት ይገልጸዋል ማለት፤ ጦሩ ይታያል፤ ቅንዋቱ ይታያል፤ መስቀሉ ይታያል። እንደ ሞተ እንደ ተሰቀለ ሆኖ ስለታየ፤ ሁሉን ላስገዛለት ለሞት ይገዛል አለ ቅዱስ ጳውሎስ። ለመሆኑ በምጽአት ደግሞ ፃዕርና ተገገር አለን? እንኳንስ በአብ፤ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ፤ በሌሎች በጻድቃን፤ በመላእክትም ፃዕር ተገገር የለባቸውም ብሎ ሲያጠይቅ ለወቀሳ መስቀሉን ይዘው መላእክት ይመጣሉ። «እንዘ መስቀልየ የሐውር ቅድሜየ» የተሰቀልኩበት መስቀሌ ፊት ፊት ይሄዳል። «ዘኢጾረ መስቀለ ሞቱ ኢይክል ይጸመደኒ» መስቀሉንም የማይዝ፤ በኋላዬም የማይከተለኝ ያለውን፤ ጨክኖ ነፍሱን ከሥጋው የሚለይበት መከራ ተቀብሎ በመከራ ካልመሰለኝ የእኔ ደቀመዝሙር ሊባል አይገባውም ብሎ በወንጌል እንደጻፈ (ማቴ.፲፥ ቁጥር ፴፰።)

በዕለተ ምጽአት ለወቀሳ ይገለጣል ማለት ነው እንጂ እንኳን ወልድ ለአብ ሊገዛ የዚያን ጊዜ በምዕመናንም ፃዕር ተገገር የለባቸውም፤ በጻድቃን የለባቸውም፤ በመላእክት የለባቸውም፤ በወዲያ ዓለም ገገር ተገገር የለም። ሁሉም ላስገዛለት ፊል ቅጽልነቱ ለአብ የሚመስላቸው ካሉ ተሳስተዋል፤ መስሎአቸው ተሳስተው ነው። ይኸማ ሥጋ አምላክ አልሆነም፤ አምላክ ሰው አልሆነም፤ ያሰኛል። እንድን አካል ፃዕር ተገገር አድርጎ ሁለት ባሕርይ፤ መለኮት ለብቻ ይሠራል፤ ሥጋ ለብቻ ይሠራል፤ ያሉ የሁለት ባሕርይ የእነ ልዮን ነው፤ ይኸም ትክክል አይደለም። ሊቃውንት በነፍስ እና ሥጋ መስለው በሃይማኖተ አበው ተናገሩ እንጂ ሁለት ባሕርይ አላሉትም። ነፍስ ተለውጣ ሥጋ አትሆንም ሥጋም ተለውጦ ነፍስ አይሆንም።

ስለዚህ ሳይለወጥ ምልአቱን፤ ስፋቱን፤ ርቀቱን፤ ሳይለቅ ነው ሰው የሆነ እንጂ፤ በሰውነቱ ለአብ ይገዛል እንዴት ይባላል? ይኼስ አይደለም «ሕቀ አኅፀፅኮ እመላእክቲከ» ከመላእክት ጥቂት አሳነስኸው ይላል። (መዝ.፰፥፭፤ ዕብ.፪፥፯።) ይህ ማለት ግን፤ የአዳምን ሥጋ ስለለበሰ ከመላእክት አሳነስኸው እንደምነው ቢሉት «ወዘአኅፀፆሰ ለክርስቶስ በእንተ ሕማመ ትስብእቱ» ከመላእክት ያነስ ስለ ሕማሙ፤ ስለሞቱ ነው። መላእክት ታመሙ፤ ሞቱ አይባልም። እሱ ግን የአዳምን ሥጋ ስለለበሰ፤ በአዳም ሥጋ ታመመ፤ ሞተ ይባላል። የሰውነቱን ሥራ ሲሠራ የአምላክነቱ የቀረ ይመስላል፤ የአምላክነቱን ሥራ ሲሠራ ደግሞ የሰውነቱ የቀረ ይመስላል። ስለዚህ ሥጋን እንደ ተዋሐደ ለማጠየቅ አንድ ጊዜ የሰውነት ሥራ ይሠራል፤ አንድ ጊዜ የአምላክነት ሥራ ይሠራል ይህም አልተለወጠም ማለት ነው። ነፍስ ሳትለወጥ ከሥጋ ጋራ እንድትኖር፤ ሥጋም ሳይለወጥ ግዘፉም ሳይለቅ፤ ከነፍስ ጋራ ተዋሕዶ እንዲኖር፤ መለኮት እና ትስብእትም ተዋሕደው አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆነው ይኖራሉ እንጂ ሁለት ባሕርይ አይባሉም። ሰው ሁለት ባሕርይ አይባልም። አማትሞት ነፍስ አለችው፤ የሚሞት ሥጋ አለው፤ ስለዚህ ሁለት ባሕርይ አይባልም። እሳት፤ ነፋስ፤ ውሃ፤ መሬት፤ ተጠራቅመው እነዚህ አራት ባሕርያተ፤ ሥጋ ሦስት ግብራተ ነፍስ ሰባት ባሕርያት ተጠራቅመው እነዚህ አንድ ሰው ይባላሉ እንጂ ሁለት ሰው አይባልም።

ቁርሉስ፤ አንድ ቁርሉስ እባላለሁ እንጂ ሁለት ቁርሉስ እባላለሁን? ይለዋል፤ ያን ንስጥሮስን፤ አሁንም በዕለተ ምጽአትም ወልድ ለአብ አይገዛም። በግርማ መንግሥት መጥቶ ይፈርዳል እንጂ በወድያ ዓለም ገገር፤ ተገገር የለም። እንኳን በአብ፤ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ሊታሰብ ይቅርና በምእመናን እንኳ ገገር ተገገር የላቸውም።

መናፍቃን የአምላካችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር ዝቅ ለማድረግ አስበው ጌታን ዕሩቅ ብእሲ ወልደ ዮሴፍ ይሉታል እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኋላ ሌሎች ልጆች ወልዳለች ይላሉ። ለዚህም እንደ ማስረጃ የሚጠቅሱት በማቴዎስ ወንጌል ፲፫፥፶፭፤ ማርቆስ ፮፥ ቁጥር ፴፪፤ ሉቃስ ፰፥፲፱ ያለውን ነው። ትክክለኛ ትርጉሙ እና ምሥጢሩ ግን ለነሱ እንደመሰላቸው አይደለም፤ ለምሳሌ አባት የሚባል ሰባት ዓይነት ነው።

፩ እግዚአብሔር አባት ይባላል፤
፪. አሳዳጊ አባት ይባላል።
፫. የክርስትና አባት አባት ይባላል።
፬. ወላጅ አባት አባት ይባላል።
፭. የቀለም አስተማሪ አባት ይባላል።
፮. የጡት አባት አባት ይባላል።
፯. የቆብ አባት አባት ይባላል።

በዚህም መሠረት ዮሴፍ አብሮ ስለተሰደደ፤ ተሸክሞት ስለተጓዘ፤ አሳዳጊ አባት ይባላል እንጂ ወላጅ አባት አይባልም። አባት የሚለው ትርጉም በመጀመሪያ ቢያጠኑት፤ ደኅና ነው። አበዊነ ሐዋርያት (አባቶቻችን ሐዋርያት) እንላለን ወልደውን ነው? አብርሃም አባታችን፤ ይስሐቅ አባታችን ያዕቆብ አባታችን እንላለን ይኸ የሃይማኖት አባቶችን ነው እንጂ በሥጋ ወልደውን አይደለም። ይህ የመናፍቃን አባባል አለአዋቂ አባባል ነው። እመቤታችንም፤ ወላዲተ አምላክ፤ ድንግል ፍጽምት መሆንዋን ለማጠየቅ፤ መንፈስ ቅዱስ በነቢዩ በሕዝቅኤል አድሮ እንዲህ ብሎአል።

«ዝንቱ አንቀጽ ይኩን ዕፁወ ወኢይትርሐው ወኢይባእ ቦቱ ብእሲ እስመ እግዚአብሔር አምላክ እስራኤል ቦአ ቦቱ» ይኸ በር እንደ ተዘጋ ይኑር፤ የእሥራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር ገብቶ የወጣበት ነውና ለዘለዓለም ተዘግቶ ይኑር። ሕዝ.፵፬፥፪–፫። ለዚህ እነ አባ ኤፍሬም፤ እነ አባ ሕርያቆስ የመሰሉ ሊቃውንት ትርጉም ሲሰጡ «ኖኅትስ ድንግል ይእቲ እንተ ወለደት ለነ መድኅነ እምድኅረ ወለድት ኪያሁ ነበረት በድንግልና» በር የተሰኘችስ መድኅን ክርስቶስን የወለደችልን እሷ (እመቤታችን) ናት። እሱን ከወለደች በኋላ በድንግልና ጸንታ ኖረች ብለው አረጋግጠዋል። «ኢይባእ ቦቱ ብእሲ አላ ይኩን ዕፁወ» ተዘግቶ ይኑር እንጂ ሰው አይግባበት። ይኸ አዳራሽ የተባለ ማነው? እስኪ ይንገሩን? ሕዝቅኤል ያ በር ተዘግቶ ይኑር ሰው አይግባበት፤ የእስራኤል ፈጣሪ እግዚአብሔር ገብቶ ወጥቶበታልና ያለው የትኛው በር ነው በኢየሩሳሌም ተዘግቶ የኖረ? ሳይፈርስ የኖረስ፤ ሰው አይግባበት የተባለውስ? የትኛው ነው? ብትለው መልስ አያገኝም።

አንቀጸ ብርሃን የተባለች እመቤታችን ናት። እነ ዮሐንስ አፈወርቅም «ተፈስሒ ማርያም ዘኢተበትከ ማኅተመ ድንግልናኪ እምድኅረ ልደቱ» ከልደቱ በኋላ ሰስሎተ ድንግልና ያልደረሰብሽ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ ብሎ በሃይማኖተ አበው ገልጸውታል። እና መጻሕፍት የተናገሩትን አልቀበልም ካሉ እንዴት ክርስቲያን ሊባሉ ይችላሉ? በማቴዎስ የተጻፈው «እናቱና ወንድሞቹ» ነው የሚለው ወንድሞቹ የተባሉ እነ ዮሐንስ እነ ያዕቆብ ናቸው? ወይስ የሰው ልጅ በሙሉ ነው? ቢባል፤

፩. በሥጋ ዮሴፍ የእኅትዋ ልጅ ነው። ያዕቆብ ማታንን እና ቅስራን ይወልዳል፤ ቅስራ ኢያቄምን፤ ኢያቄም እመቤታችንን ይወልዳል። ያዕቆብ ለዮሴፍ ሦስት ቤት ማለት ነው። ማቴ.፩ ቁጥር ፲፭።
፪. ዘመድ የሆነ ሁሉ ወንድም ይባላል።
፫. ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ወንድም ይባላል። ይኼ አጭሩ ነገር ወደ ግራ እናጣምምህ ቢባል እንዴት ሊሆን ይችላል? ወንድም የሚባል የአባት ወይም የእናት ልጅ ብቻ አይደለም። ክርስቲያን ወንድም ይባላል ወዳጅ ወንድም ይባላል፤ ዘመድ ወንድም ይባላል። ታዲያ ስለዚህ ነው እነ ዮሳ፤ እነ ያዕቆብ የጌታ ወንድሞች የሚባሉት። እመቤታችን በዮሴፍ ቤት ሳለች እነ ያዕቆብን እንደ እናት ስለአሳደገቻቸው «እኅት ለእግዚእነ» «የጌታችን ወንድም» ይለዋል። ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በእሱ ያመኑ ምዕመናንን «አማን እብለክሙ ኮሉ ዘገብርክሙ ለአሐዱ እምእሉ ንዑሳን አኀውየ እለ የአምኑ ብየ ሊተ ገበርክሙ» እውነት እላችኋለሁ ለእነዚህ ለአንዱ በእኔ ካመኑ ምዕመናን ወንድሞቼ ያደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት። ማቴ.፳፭ ቁጥር ፵። «አኀውየ» ያላቸው የዮሴፍ ልጆችን ነው? ሐዋርያትን ሁሉ ወንድሞቼ ይላቸዋል ለምንድነው አትለውም? ወበእንተዝ ኢየሐፍር ብሂሎቶሙ ለነዳያን አኀውየ» ስለዚህ ድሆች ሐዋርያትን ወንድሞቼ ማለትን አላፍርም አለ ቅዱስ ጳውሎስ። ዕብራውያን ፪፥፲፩። ቁም ነገሩ ከቅርብ እያለ እንዲያው ገደል መግባት ነባቢት ነፍስ ያላቸው ሰዎች ወንድም የሚባለውን አባት የሚባለው እንዴት ለይተው አያውቁም?

በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፳፮ ቁጥር ፴፱ ላይ ጌታችን በጸሎተ ሐሙስ በጌቴ ሴማኒ ሲጸልይ «አባቴ ሆይ ቢቻልስ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ፤ ነገር ግን አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን» ብሏል። እና ሁለት ፈቃድ አለ ይላሉ። በመሠረቱ በምሥጢረ ሥላሴ ትምህርት የሥላሴ ፈቃድ አንድ መሆኑ ይታወቃል። በዚህ ገጸ ንባብ ሁለት ፈቃድ እንዳለ አድርጎ ማስተማር ክሕደት ነው።

የእኔ ጽዋዓ ሞት ከእኔ ወደምእመናን ይለፍላቸው እኔን አብነት አድርገው መከራ እየተቀበሉ እኔ በዕለተ ዓርብ የተቀበልኩት መከራ እየተቀበሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት ይግቡ እኔ የጀመርኩላቸው ሐዋርያት ከዚያ ቀጥለው ሰለስቱ ምዕት ምእመናን ከእኔ መከራ ይቀበሉ ይኸ ጽዋዐ ሞት ከእኔ ወደ እነሱ ይለፍላቸው። ጽዋዕ በተርታ እንዲጠጣ ሞትም በተራ ነውና። ከእሱ ቀጥለው ሐዋርያት ከዚያም ሰባ ሁለቱ አርድዕት ከዚያም እስከ ምጽአት ያሉ ምዕመናን ክርስቶስን በመምሰል መከራ ይቀበሉ አለ።

የእኔ ፈቃድ ከአንተ ፈቃድ ሆኖ የእኔ ፈቃድ ይደረግ አልልም የእኔ ፈቃድ ከአንተ ጋራ አንድ ነውና የአንተ ፈቃድ ይደረግ እላለሁ እንጂ፤ ነው ያለው። ትርጓሜው በፈቃድ ልዩ ናቸው አይባልም። «ንባብ ይቀትል ወትርጓሜ የሐዩ» ንባብ ይገድላል ትርጓሜ ግን ያድናል ያለው እንዲህ ያለ ንባብ ነው። ንባቡ ሁለት ፈቃድ እንዳለ መስሎ ተነገረ እንጂ «አሐቲ ሥምረት አሐቲ ፈቃድ አሐቲ ሕላዌ» አንዲት ሥምረት፤ አንዲት ፈቃድ፤ አንዲት አኗኗር እያለ በሃይማኖተ አበው ተገልጾአል። እነ ቅዱስ ኤፍሬም «እስመ በፈቃዱ ወበሥምረቱ አቡሁ ወመንፈስ ቅዱስ መጽአ ወአድኀነነ» በባሕርይ አባቱ በአብ፤ በባሕርይ ሕይወቱ በመንፈስ ቅዱስ በራሱ ፈቃድ መጥቶ አዳነን። አለ እንጂ ሥላሴ በፈቃድ ብዙ ናቸው አላለም። በቸርነት፤ በርኅራኄ፤ በቅድምና፤ በፈቃድ አንድ ናቸው። ይኼ ትርጓሜው ሌላ መስሎት ነው እንጂ የእኔ ፈቃድ ከአንተ ፈቃድ ጋር አንድ ነውና የእኔ ፈቃድ ይደረግ አልልም። የአንተ ፈቃድ ይደረግ እላለሁ። ፈቃዳችን አንድ ነውና። «እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም፤ እንደሰማሁ እፈርዳለሁ ፍርዴም ቅን ነው፤ የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና።» ብሎ ተናገሯል። (ዮሐ.፭ ቁጥር ፴) አብ ሥጋ አለመልበሱን ወልድ ሥጋ መልበሱን ተናገረ። ታመመ፤ ሞተ፤ የሚባል አንድ አካል ነው። አብ፤ መንፈስ ቅዱስ፤ ታመሙ፤ ሞቱ አይባሉም። ስለዚህ የተለየ መስሏቸው ነው እንጂ በፈቃድ አንድ ነው። ስለዚህ እንዳያስቱአችሁ ተጠንቀቁ። ✣

## የአሥራ አንድ ነገሮች ምሳሌ

ብረት ጽኑ ነው እሳት ያሸንፈዋል
እሳት ብርቱ ነው ውሃ ያሸንፈዋል
ውሃ ብርቱ ነው ደመና ይሸከመዋል
ደመና ኃያል ነው ነፋስ ይበትነዋል
ነፋስ ብርቱ ነው መሬት ይገድበዋል
መሬት ጽኑ ነው ሰው ያሸንፈዋል
ሰው ብርቱ ነው ኃዘን ያሸንፈዋል
ኃዘን ጽኑ ነው መጠጥ ያሸንፈዋል
መጠጥ ብርቱ ነው እንቅልፍ ያሸንፈዋል
እንቅልፍ ብርቱ ነው ሞት ያሸንፈዋል
ነገር ግን ሁሉንም ሴት ታሸንፋቸዋለች።

## መጠጥና ሰካራም

መጠጥ – ያሰክራል – ራስን ያዞራል
ጣፊያን ያሳርራል – አዕምሮን ያጠፋል
አንደበትን ያጥፋል – አንጀትን ያቆስላል
ጉበትን ያበስላል – ሆድን ያምሳል
ሰውነትን ይጐዳል – ልብን ያነዳል
አፍን ያሳብዳል – ጉልበትን ያርዳል
ጊዶል ይጥላል – እንደፈረስ ይጋልባል
. . . . በድንገት ይገድላል

## ሰካራም

ደህና ሲሉት ይግታል
አለ ሲሉት ይሞታል
ባይሞትም ዓይን ያለው ሬሳ ነው
ቢሞትም ሳይቀበር የቆየ በድን ነው

ምንጭ ሥነ ምግባር (፲፱፻፺፭)

www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱስ መስቀል

ከመ.ጋቢ ብሉይ ስይፈ ሥላሴ ዮሐንስ



**መ**ስቀል:- በፊደልም በቅርጽም አራትነት ያለው ነው። «ርቡዐ ኖኅያት ወገጽ» ማለት ነው። መስቀል ሌላም ብዙ ዓይነት ቅርፅ አለው።

ይሁን እንጂ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለሙን በአራቱ መዓዝን ይቀድሰው ዘንድ በቅርጽ መልክ አራትነት ባለው መስቀል ላይ ተሰቀለ። ዛሬም ክርስቲያኑ ዓለም ሁሉ የሚጠቀምበት ይኸው በአራትነት ምዑዝን የሆነው መስቀል ነው።

መስቀል አጭር ቃል ነው። ግን ይህ ቃል ሲነገርና ሲሰማ ወደ ክርስቲያናዊ ሰው ልብ ጠልቆ ይገባል፤ ነገረ መስቀል ሲዘከር ራሱ ዘንበል ይላል፤ እጅ ይንቀሳቀሳል፤ ጣቶች እርስ በእርሳቸው ትእምርተ መስቀል ይሠራሉ። መስቀል በእርሱ ላይ የተሰቀለውን እግዚአ-ስብሐት ክርስቶስን ያሳስባልና።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ና ቅዱስ ያሬድ ዘአክሱም እንደ ተናገሩ «መስቀል መልዕልተ ኩሉ ነገር» መስቀል ከሁሉ ነገር በላይ ነው። እግዚአብሔር ዓለምን ያዳነበት፤ ከጥበብ ሁሉ በላይ የሆነ ጥበብ ነውና።

በመስቀል የእግዚአብሔር አብ፤ የእግዚአብሔር ወልድና የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ፍቅር ተገለጠ፤ ወልድ በራሱ፤ በአባቱና በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ሰው ሆኖ በመስቀል ላይ ሞቶ አድኖናልና።

በመስቀል የሲኦል መሠረት ተናወጠ፤ ሰውና እግዚአብሔርን ለይቶ የነበረው የኃጢአት መጋረጃ ተቀደደ፤ የጥል ግድግዳ ተናደ፤ ሞት ድል ሆነ፤ የትንሣኤም መንገድ ተከፈተ።

የመስቀሉ ነገር:- በሰው አእምሮ ሊስተዋል የማይችል ረቂቅ ነው። አምላክን ሰው እስከ መሆንና እስከ ሞት ያደረሰውን የሰው ፍቅር ከማንከር በቀር መመርመርና ድርሰ-ነገሩን ማስተዋል አይቻልም። ንግሥት ዕሌኒ የመስቀሉን ነገር ስታሰላስል መልአኩ በተገለጠላት ጊዜ «ስለ ክርስቶስ መስቀል ንገረኝ» አለችው። መልአኩም «እኛ ማኅበረ መላእክት ስለ ክቡር መስቀሉ መነጋገር ጀመርን፤ ግን የመስቀሉ ነገር ዕፁብ ነው» አላት። (ቅዱስ ያሬድ ድጓ)፣

በመሆኑም ለአንዳንዶች ስንፍና፤ ለሌሎችም ፈተና ሆኖባቸዋል። እንዲሁም እንቅፋት የሆነባቸው አሉ። ለሚያምኑ ግን መስቀል ጥበብና ከፈተና እንደ ወርቅ ነጥረው የሚወጡበት ነው።

መስቀል ሕይወትን ለማጥፋት በተነሡ ጠላቶች ተዘጋጀ፤ ነገር ግን አዲስ ዘለዓለማዊ ሕይወት በመስቀል ተገኘ። መስቀል እውነትን ለመደምሰስ ታስቦ በእውነት ጠላቶች በቀራንዮ ተተከለ። ነገር ግን በመስቀል ለዓለም እውነት ተሰበከ። አይሁድ በመስቀል ላይ የተፈጸመው አሰቃቂ ሞት ሰዎችን ከክርስቶስ እንደሚያርቅና ፈጽሞ እንደሚለይ አስበው ነበር፤ ነገር ግን በመስቀል ላይ የፈሰሰው የክርስቶስ ደም ዓለሙን ሁሉ ወደ እርሱ አቀረበው። «ከምድር ወደ ላይ ከፍ ባልሁ ጊዜ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ (፲፪:፴፪) በማለት መድኀኔዓለም ክርስቶስ በመስቀሉ የሰውን ልጅ ወደ ራሱ አቅርቦታል። እንደዚሁም «ዘበመስቀልከ አቅረ ብከነ ኀበ አቡከ...» በመስቀልህ ወደ ባሕርይ አባትህ ያቀረብኸን አንተ ነህ፤ እንደ ተባለ በመስቀሉ ላይ በፈጸመው መሥዋዕትነት ከእግዚአብሔር አብ ዕርቅንና ሰላምን እንድናገኝ አድርጓል።

ስለዚህ መስቀል የደስታችን፤ የነፃነታችን፤ የዕርቃችንና የሰላማችን ምልክት በመሆኑ ለመስቀል ክብርን እንሰጣለን፤ እንሰግዳለን። እነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ስለ መስቀል ኃይል የመሰከሩትን እኛም እንመሰክራለን እንዲህ እያልን:-

«መስቀል የክርስቲያኖች ተስፋ ነው፤

መስቀል የሙታን ትንሣኤ ነው፤

መስቀል የዕውራን መሪ ነው፤

መስቀል ተስፋ ቅቡፃን ነው፤

መስቀል ትንቢተ ነቢያት ነው፤

መስቀል ስብከተ ሐዋርያት ነው፤

መስቀል ክብረ ሰማዕት ነው፤

መስቀል የጻድቃን ሞገስ ነው፤

መስቀል የመነኮሳት ጽሙና ነው፤

መስቀል የደናግል ንጽሕና ነው፤

መስቀል የቤተ ክርስቲያን መሠረት ነው፤

መስቀል የዓለም ሰላም፤ መረጋጋትም ነው።» (ግብረ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ቅፅ ፪)

እንደ ሊቁ አባባል:- የነቢያት ሁሉ የትንቢታቸው ዓላማ ክርስቶስ በሕማመ መስቀሉ፤ በሞተ መስቀሉ ዓለምን እንደሚያድን ነበር። «...በሚያለቅሱና በሚተክዙ ሰዎች ግንባር ላይ ምልክት ጻፍ አለው፤ ... ምልክቱ ወደ አለበት ሰው ሁሉ አትቅረቡ...» አላቸው (ሕዝቅ. ፱፥፩-፯) የዚህም ትንቢት ፍካሬ መስቀል ነው። ምልክት ማለት በዕብራውያን ቋንቋ ታው ማለት ነው። ታው የተባለ የዕብራይስጥ መጨረሻ ፊደል ሲሆን ቅርፁ የመስቀል ዓይነት ነው።

የሐዋርያትም የስብከታቸው መነሻና መድረሻ «ንሕነሰ ንሰብክ ክርስቶስሀ ዘተሰቅለ» እኛስ የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን የሚለው ስረይ ነው። (፩ቆሮ.፩፥፳፫)

ንጉሠ ስብሐት ክርስቶስን በመስቀል ላይ የሰቀሉ ሰዎች ክርስቶስንና ተከታዮቹን ሁሉ እስከ መጨረሻ ያሸነፉ መስሏቸው ነበር። ይሁን እንጂ በክርስቶስ የሚያምኑና በመስቀሉ መንገድ እርሱን የሚከተሉ ሁሉ ሰይጣናትንና ክፉ ምኞቶችን፤ የመስቀል ጠላቶችንም በየጊዜው ድል ሲያደርጉ ኖረዋል፤ ይኖራሉም። የመስቀሉን ኃይል ደጋግሞ የሚያነሣው አፈ ወርቅ እንዲህ ይላል:-

«ክፉ መንፈስ የተመታበትንና የቆሰለበትን ሰይፍ ካየ ወደባለ ሰይፉ ሊቀርብ አይችልም። ይህ ሰይፍ ሰይጣን የተመታበት መስቀል ነው። ስለዚህ ማንም የመስቀል ምልክትን ለማድረግ አይፈር በቤታችን፤ በግድግዳችን፤ በበራችን፤ በግንባራችን፤ በደረታችን፤ በጣታችንና በክንዳችን የመስቀል ምልክት ይኑረን። ምክንያቱም መስቀሉ:-

ድላችን ነው፤ ከተሰጡን በረከቶች ሁሉ ታላቁ በረከት ነው፤ ነፃነታችን ነው፤ ዝመራ ዘውዳችን ነው፤...የቤተ ክርስቲያን ጌጥ ነው። በመሆኑም መስቀሉን በአእምሮአችሁ እንደ ማሕተም አትሙት።» (ግብረ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ቅፅ ፯)

በዚህ ቅዱስ አባትና በሌሎችም ቅዱሳን አበው ትምህርትና ምክር መሠረት የቅድስት ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ምእመናን ሁሉ ማንኛውንም ተግባር፤ ጸሎትን፤ ምግብን፤ ጉዞን ከመጀመር በፊትና በኋላ ባትእምርተ መስቀል ያማትባሉ፤ በፈተና፤ በኀዘንና በሕማም ጊዜ፤ ክፉ አሳብ በሚመጣ ጊዜ በትእምርተ መስቀል በማማተብ ይከላከላሉ። ይህንም የሚያደርጉት መስቀሉን በከበረ ደሙ በቀደሰው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉን ቻይ ርዳታው በመታመን ነው።

ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ:- «ቅዱስ መስቀልን በሰውነቴ ክፍሎች ሁሉ እሸከማለሁ፤ መስቀል በጉዞዬ ሁሉ ከእኔ ጋር ነው፤ መስቀል በፊቴ ነው፤ መስቀል በልቤ ውስጥ ነው» ይላል። (ጎርጎርዮስ ቅፅ ፪)

የሊቁ ነገረ መስቀል በአንድ በኩል ሕማምና መከራን ቢያመለክትም በቀጥታ ዕፀ መስቀሉንም የሚያመለክት መሆኑ ግልጥ ነው። ቅዱሳን አበው መስቀል ይዘውና አስይዘው ይጓዛሉና። «ለባስያነ መስቀል» ስለሆኑ ልብሰቸውም፤ አክሊላቸውም፤ በትረ ክህነታቸውም ባለ ትእምርተ መስቀል ነውና።

ቅዱስ መስቀል:- የክርስቶስ አካል የተቸነከረበት፤ ደሙ የነጠበበት ስለሆነ ታላቅ ኃይል በመሥራቱ እናከብረዋለን፤ እንሳለመዋለን፤ የአክብሮት ወይም የፀጋ ስግደት እንሰግድለታለን።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በዓመት ሁለት ጊዜ በመጋቢት ፲ ቀንና በመስከረም ፲፯ ቀን ልዩ ሥነ በዓል አድርጋ ታከብረዋለች። መጋቢት ፲ ቀን ንግሥት ዕሌኒ በ፫፻፳፯(፫፻፴፰) ዓ.ም መስቀሉን ከተቀበረበት አስቆፍራ ያገኘችበት ሲሆን መስከረም ፲፯ ቀን:-

ሀ. ቤተ ክርስቲያኑ ተሠርቶ ቅዳሴ ቤቱ የተከናወነበት፤

ለ. ቅዱስ መስቀሉ ከኢየሩሳሌም በ፯፻፴፩ ዓ.ም በፋርሳውያን ከተዘረፈ በኋላ በሕርቃል ንጉሠ ቁስጥንጥንያ በመስከረም ፲ ቀን ፯፻፳፰ ዓ.ም ወደ ቁስጥንጥንያ የገባበት፤

ሐ. ሕርቃል በመስከረም ፲፱ ቀን ፯፻፳፱ ዓ.ም ንግሥት ዕሌኒ በኀል ኀታ አሠርታ የነበረውን ቤተ ክርስቲያን አሳድሶ መስቀሉን ያስገባበት ስለሆነ ነው። (መስከ ረም ፲፱ ከጎርጎርዮሳዊ አቆጣጠር ነው)

በመስከረም ወር ቀኑ ይለያይ እንጂ የምሥራቅና የምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ቅዱስ መስቀሉን ያከብራሉ። ይህም የሆነው በብያኔ ነው። መስቀሉ የተገኘበት መጋቢት ወርኀ ጾም ስለሆነ በመስከረም እንዲከበር መወሰኑ በስንክሳር ተገልጦአል።

ይሁን እንጂ የመስከረም ያህል በአደባባይ ባይሆንም በመጋቢትም መከበሩ አልቀረም። መስከረም ፲፯ ቀን የመስቀል በዓል ልዩነት ብሔራዊ መሆኑ፤ ደመራውና የችቦው መብራት ነው። ይህም ትውፊታዊ መሠረት አለው።

ዕሌኒ መስቀሉ የተቀበረበትን ቦታ ለማወቅ ደመራ ደምራ፤ ዕጣን ጨምራ በእሳት አቀጣጥላ ጢሱ እንደ ቀስት ያመለከተበትን ቦታ በመቆፈር መስቀሉን አውጥታለች። የመስቀሉም መገኘት ዜና ለልጇ ለቄሣር ቆስጠንጢኖስ ይደርሰው ዘንድ ከኢየሩሳሌም እስከ ቁስጥንጥንያ በየተራራው መብራት እንዲበራ አድርጋለች ይህም የዘመኑ የዜና ማሠራጫ ዘዴ ነበር። በዚሁ መሠረት ቤተ ክርስቲያናችን የታሪኩን ድርጊት በሥዕል ገልጣ መስቀልን ታከብራለች።

በአንዳንድ አካባቢ ደመራው በሌሊት ሲቀጣጠል በአዲስ አበባና በሌሎች ከተማዎች ማታ በዋዜማው ይቀጣጠላል። ዋዜማና ዕለት አንድ በመሆኑ ልዩነቱ የጎላ አይደለም።

በከተማ በዋዜማ መከበሩ በተለይ በነገሥታት ዘመን የክብር ዘበኛ፤ የጦር ሠራዊትና ብሔራዊ ጦር ልዩ ሰልፍ ያደርግ ስለነበር ሌሊት የማያመች መሆኑ ታስቦ ነው። በገጠሩ ግን ይህ ዓይነቱ ሥነ-በዓል ስለማይደረግ በሌሊት ወይም ሲነጋ ደመራው ተቀጣጥሎ በዓሉ ይከበራል።

ይሁን እንጂ በቤተ ክርስቲያናችን የመስቀል ክብር በዓመትና በወር አይወሰንም፤ ነገረ መስቀል የማይወሳበት ዕለትና ሰዓት የለም። የክብረ መስቀል ድርሻ የሌለበት ሥርዓተ ማኅሌት፤ ሥርዓተ አምልኮትና ሥርዓተ ጸሎት የለም። የሰው ልጆች ሁሉ የበደል ካሳ በመስቀል ተፈጽሞአልና።

❖



www.ethiopianorthodox.org

# ወጣቶችና ቤተ ክርስቲያን

## ክፍል አንድ

## የወጣቶችና የቤተ ክርስቲያን ትርጓሜ

በትርጓሜ ቤት ዘይቤ ቤተ ክርስቲያን የአራት ጾታ ምእመናን ስብስብ (ጉባኤ) ናት። ከዚህ ስብስብ አንዱ ዓቢይ ክፍልም «ውሉድ» ናቸው። «ውሉድ» የሚለው ቃል የሕፃናትን፣ ወጣቶችንና ጎልማሶችን ክፍል የሚያጠቃልል ግዙፍ ቃል ነው።

«ጾታ» የሚለው ቃል በዚህ አገላለጽ «ክፍል» ማለት ሲሆን በዚህ አጋጣሚ ስለ ጾታ ምእመናን ዝርዝር ከዚህ ቀጥሎ በአጭር መግለጥ ይቻላል።

### የምእመናን ስብስብ (ጉባኤ)

ሀ. በተፈጥሮ ጾታ ሲከፈል – ዕድ ወአንስት (ሴትና ወንድ)

ለ. በእድሜ ጾታ ሲከፈል – አዕሩግ ወሕፃናት/ወደቂቅ (አባቶችና ልጆች)

ሐ. በመዓርግ ጾታ – ካህናት ወመኃይምናን (ካህናትና መኃይምናን/ካህንና ጨዋ)

– ዓቢይ ወንኡስ (አሳዳሪና ተዳዳሪ) በሚል መድበለ ማኅበር ይከፈላል።

የቤተ ክርስቲያን ወይም የምእመናን ስብስብ ወይም «መድበለ ማኅበር» በዚህ ዓይነት ጾታ ክፍል የተከፈለ ቢሆንም በዚህ ርእስ ትምህርት ለመናገር የተፈለገው «ውሉድ» የሚለውን ክፍል በማስመልከት ነው።

ወጣቶች የቤተ ክርስቲያን ሕዋስ ወይም አካል መሆናቸውን መገንዘብ ከተቻለ ዘንድ «ወጣቶች» ማለት ቤተ ክርስቲያን፤ ቤተ ክርስቲያን ማለትም «ወጣቶች» ማለት ጭምር መሆኑን መገንዘብ አስቸጋሪ አይሆንም።

ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው የሲኦል ኃይሎች ሊያናውጡት በማይችሉ መሠረት ላይ እንደሆነ ተጽፏል ማቴ. ፲፮፥፲፰። ቤተ ክርስቲያን በሁሉም ጾታ ምእመናን አንድነት ላይ የተገነባች የእግዚ አብሔር ቤት ከሆነች ወጣቱ ራሱ ቤተ ክርስቲያን (ወይም የቤተ ክርስቲያን አካል) ስለሆነ ለሕይወቱ ግምባታ የማይናወጥ ጽኑዕ መሠረት ያስፈልገዋል፤ ያም መሠረት በተግባር ሊታይ የሚችል ክርስቲያናዊ ሕይወት ነው።



በሌላም ቋንቋ ቤተ ክርስቲያንን ጠንካራና ጤነኛ የሆነ ሙሉ አካል ያላት የክርስቶስ አገልጋይ ለማድረግ የወጣቱን ትውልድ ክርስቲያናዊ ሕይወት ደኅንነት መጠበቅ ግዴታ ይሆናል። ይህ ሕይወት በአስተማማኝ ሁኔታ ሊጠበቅ የሚችለውም ወጣቱ ትውልድ ከልጅነት ጊዜው ጀምሮ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል በጥበብና በሞገስ እንዲያድግ ማድረግ ሲቻል ነው።

## ክፍል ሁለት

## የወጣቶችና የቤተክርስቲያን ትርጓሜ

### የወጣትነት ጊዜ ወርቃማነት

«ወጣቶችና ቤተ ክርስቲያን» የሚለውን አንቀጸ ትምህርት በዚህ በማጠቃለል «ክርስ ቲያናዊ ሕይወት በወጣትነት» የሚለውን ክፍል ለመቃኘት ሲሞከር ደግሞ ክርስቲያናዊ ሕይወት በወጣትነት ዘመን የሚያስገኘውን መንፈሳዊና ማኅበራዊ በረከት በዝርዝር መመልከት ይቻላል።

ቅዱስ መጽሐፍ ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የልጅነት ዘመን ሲተርክ «በጥበብና በቁመት፣ በሞገስም በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያድግ ነበር» ይላል ሉቃ.፪፥፶፪። እኛን ለማዳን ሰው የሆነው አምላክ ሕጻንም፣ ወጣትም ሆኖ ቀስ በቀስ በማደግ የልጅነት ዘመኑን በዚህ ዓይነት ሕይወት ያሳለፈው ለራሱ ክብርና ሞገስ ለማግኘት አይደለም፤ ትምህርትና አብነት ለሚያስፈልጋቸው ለዚህ ዓለም ሕፃናትና ወጣቶች ራሱን መልካም አርአያና ምሳሌ አድርጎ በማቅረብ የሕፃንነትና ወጣትነት ዘመን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ሕይወት ምን መምሰል እንዳለበት ለማስተማር እንጂ በእርግጥ የራሱን ግዴታ ለመፈጸም አይደለም። የዓለም መድኃኒት ራሱ የዓለም መምህር ሆኖ የሰውን ልጅ ያስተማረው በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም ማለት በመልካም አርአያና ምሳሌነትም ጭምር መሆኑን ለሚያውቅ አማኒ ይህን ምሥጢርም ማወቅ የሚሳነው አይሆንም። የሰው ልጅ ራሱ «ጊዜ ወርቅ ነው» እንደሚለው በእርግጥ ጊዜ ወርቅ ከሆነ የወጣትነት ጊዜን በሰውና በእግዚአብሔር ፊት የበለጠ ወርቃማ ማድረግ የሚቻለውም ይህ ሲሆን ነው – ማለት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል በጥበብና በሞገስ ለማደግና በክርስቲያናዊ ሕይወት በተባረከ የወጣትነት ዘመን ለመኖር ሲቻል።

የልጅነትና የወጣትነት ዘመን የነፋስና የእሳት ዘመን ነው። ስለሆነም በቀዳማዊው የልጅነት ዘመን እንደነፋስ በዘፈቀደ መንፈስና በዳኃራዊው ደግሞ እንደ እሳት መተኮስና መፋጀት ምንጊዜም የነበረ፤ ያለና የሚኖር የተፈጥሮ ባሕርይ ነው። ይሕውም የልጅነትና የወጣትነት ዘመን ተፈጥሮው ከእሳትና ከነፋስ የሆነው የሰው ልጅ ይህን የተፈጥሮ ባሕርይ በተግባር የሚያሳይበት እፍላ ወቅት በመሆኑ ነው።

በውኃነትና በመሬትነት ባሕርይ የሚገኙ አንዳንድ አበው በዚህ የነፋስነትና የእሳትነት ባሕርይ ዘመን ላይ የሚገኙ ውሉድ እንደ እነሱ የሰከነ ጠባይ ማሳየት እንደአለባቸው ስለሚጠብቁ በየትኛውም ጊዜና ቦታ የልጅነትና የወጣትነት ጠባይ የሚያሳዩትን ታዳጊ ሕፃናትና ወጣቶችን ሲተቹና ሲራገሙ፤ አልፈው ተርፈውም ዘመኑን ሲያማርሩ ይሰማሉ። ለልጅነትና ወጣትነት ባሕርይ ነፋስነትና እሳትነት ዕውቅና መስጠት ይሳናቸዋል። በዚያም ጠባያቸው ልጆች እግዚአብሔርን የሚያስቆጡ እየመሰላቸው ይጨነቃሉ።

አንድ ጊዜ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርት ልጆቻቸውን ይባርክላቸው ዘንድ ወደጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይዘው ለመቅረብ የሞከሩትን ወላጆች የከለከሉት ልጆቹ እንዳያውኩት በማሰብ እንደሆነ ይታመናል። ማቴ.፲፱፥፲፫–፲፭። ሙከራው የተደረገው ልጆች አዋኪዎች እንደሆኑ በማሰብ ቢሆንም አስተሳሰቡ ሰው ሰውኛ በመሆኑ በክርስቶስ አልተደገፈም፤ ልጆቹ ወደ ክርስቶስ እንዳይቀርቡ የሞከሩት ደቀ መዛሙርት ተገስጸዋል። የተከለከሉትም ልጆች ቀርበው በእንብርክ እድ ተባርከዋል።

በመሠረቱ ሰውን የፈጠረ አምላክ ልጅም ይሁን ሽማግሌ ስለፍጥረቱ ምንነት ያውቃል፤ «ሕፃናትን አትከልክሉአቸው ወደእኔ ይምጡ» ያለውም ከልጅነት ባሕርይ ውጭ ሁነው ወደ እሱ እንዲቀርቡ አይደለም፤ ወጣቶችም እንዲሁ። ስለሆነም ልጆችና ወጣቶች ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርቡ የሚፈለገው የተባረከ ልጅ፤ የተባረከ ወጣት ሁነው እንዲያድጉ፤ ልቅና ስድ – አደግ በመሆን ፈንታ ከላይ እንደ ተገለጸው በሰውና በእግዚአብሔር መካከል በጥበብና በሞገስ በማደግ በመንፈሳዊውም ሆነ በማኅበራዊው ሕይወት ለመልካም ጉልምስናና ሽምግልና ኑሮ ጽኑዕ መሠረት ለመጣል እንዲበቁ፤ በዚህ ዓይነት ክርስቲያናዊ ሕይወት የነፋስና እሳት ባሕርያቸውን በማርገብና በማቀዝቀዝ የልጅነትና ወጣትነት ኑሮዋቸውን ሕይወትነት ያለው ለማድረግ እንዲችሉ በተግሣጽ በትምህርትና ምክር ለማገዝ እንጂ የእድሜያቸው ሰው እንዳይሆኑ ለማድረግ አይደለም። ወይም በአንድ ጊዜ ተወልደውና በአንድ ጊዜ አድገው የአባቶቻቸው ዘመን ሰው እንዲሆኑ ለማድረግም አይደለም። «ክርስቲያናዊ ሕይወት በወጣትነት» የሚለው ምኞት ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ ሊሆን የሚችለውም ልጆችና ወጣቶች በዚህ ሁኔታ የራሳቸው ዕድሜ የሚጠይቀውን ክርስቲያናዊ ሕይወት በመኖር መልካም አዳጊ ክርስቲያን ለመሆን ሲበቁ ነው።

## ክፍል ሦስት

## ከክርስቲያን ወጣቶች የሚጠበቅ የከዊንና ገቢር ግዴታ

ስለዚህ ርእስ ለመናገር በቅድሚያ የሁሉም ጾታ ምእመናን ሕይወት መመሪያ የሆነውን ቅዱስ መጽሐፍ ማናገር ግዴታ ይሆናል።

«አንተ ጎበዝ በጉብዝናህ ደስ ይበልህ፡ በጉብዝናህም ወራት ልብህን ደስ ይበለው፤ በልብህ መንገድ፡ ዓይኖችህም በሚያዩት ሂድ፤ ዳሩ ግን ስለዚህ ነገር ሁሉ እግዚአብ ሔር ወደ ፍርድ እንደሚጠራህ ዕወቅ...» መክ.፲፩፡፱–፲።

«የጭንቀት ቀን ሳይመጣ፡ ደስ አያሰ ኙም የምትላቸውም ዓመታት ሳይደርሱ በጉብ ዝናህ ወራት...ፈጣሪህን አስብ» መክ.፲፪፡፩–፰።

«አቤቱ ጌታዬ ሆይ ከልጅነቴ ጀምሮ ተስፋዬና መታመኛዬም አድርጌሃለሁ።» መዝ.፸፡፭–፮።

«ፈጣሪዬ ከልጅነቴ ጀምሮ ይቅር ብልኸኛልና (አስተምረኸኛልና) ጌትነትህን እናገራለሁ፡ ፈጽሜ እስከ አረጅ ድረስም» መዝ.፸፩፡፲፯።

«ጎልማሳውም አለው ይህን ሁሉ ከልጅነቴ ጀምሮ ጠብቄያለሁ፤ እንግዲህ ምን ቀረኝ?» ማቴ.፲፱፡፳።

«ጎልማሶች ሆይ! ብርቱዎች ናችሁና፤ የእግዚአብሔር ቃል በእናንተ ዘንድ አለና፤ ክፉውንም አሸንፋችኋልና እጽፍላችኋለሁ» ፩ዮሐ.፪፥፲፬።

ስለወጣቶች መንፈሳዊ ሕይወት ትውፊት ከቅዱስ መጽሐፍ ብዙ መጥቀስ ይቻላል። ሆኖም የተጠቀሰው ቃል ሌላውን ሁሉ ስለሚወክል ለጊዜው ይበቃል። ከእያንዳንዱ ጥቅስ መረዳት እንደሚቻለው፤

ጠቢቡ ሰሎሞን በጉብዝና ወራት የሚሠራ ሥራ ሁሉ ትክክለኛ ካልሆነ በእግዚ አብሔር ዘንድ እንደሚያስጠይቅ በማስጠ ንቀቅ በወጣትነት ወራት ራስን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርንም ደስ የሚያሰኝ ኑሮ መኖር በመጀመሪያው ዘመን ጀምሮ ተግባራዊ መሆን ያለበት የሰው ልጅ ግዴታ እንደሆነ ይመክራል።

ነቢዩ ዳዊት እግዚአብሔርን ተስፋ በማድረግ ማለት በእሱ በመታመንና ጌትነቱንም በመመስከር የአምልኮትን ግዴታ መፈጸም በልጅነት ዘመን መጀመር ያለበት ግዴታ መሆኑን በራሱ ምሳሌነት ይናገራል (ተናግሯል)።

ሐዋርያው ዮሐንስ ልቡናቸው ለቃለ እግዚአብሔር ዘር መልካም ምድር ለሆነውና ክፉውንም ሁሉ በማሸነፍ ኃያልነታቸውን በተግባር ለአረጋገጡት የዘመኑ ክርስቲያን ወጣቶች የጻፈው የምስጋና ቃል በተመሳሳይ ሕይወት ለተገኙና ለሚገኙ የየትኛውም ዘመን ወጣቶች ሁሉ የተደረገ ሙገሳ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ከልጅነት ጀምሮ አምላካዊ ሕግንና ትእዛዝን ጠባቂ ሆኖ መኖሩን በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፊት በኩራት የተናገረው ጎልማሳ በአነጋገሩና በአስተሳሰቡ ተመካ ሂናውዳሴ – ከንቱ ወዳድ ወይም አፍቃሪ ሆኖ ባይገኝ ኑሮ «ይህን ሁሉ ከልጅነቴ ጀምሮ ጠብቄያለሁ፤ ሌላ ምን ቀረኝ?» ሲል ያቀረበው ጥያቄ ይበል የሚያሰኝ የመልካም ወጣትነትና ጎልማሳነት ቃል ነበር። ይህም ሆኖ ከዚህ ጎልማሳ የሕይወት ታሪክ ወጣቶች የሚያገኙት ትምህርት አለ፤ ከልጅነት ጀምሮ አምላካዊ ሕግንና ትእዛዝን ጠባቂ ሆኖ ማደግ የነበረና የሚኖር ሃይማኖታዊ ግዴታ መሆኑን ከዚህ ወጣት የሕይወት ታሪክ ለማወቅ መቻል አንድ ትምህርት ሲሆን በእግዚአብሔር ፊት ተነሣሒ እንጂ ተመካሂ ወጣት ሆኖ መገኘት ደካማነትና ፍሬ ቢስነት መሆኑን ማወቅ ደግሞ ሌላ ትምህርትነት አለው።

በመሆኑም ይህን ጠቅላላ ዕውቀት ማወቅና ይህን ጥንቃቄ መጠንቀቅ በዘመነ አሪትም ሆነ በዘመነ ወንጌል ከልጅነት ጊዜ ጀምሮ የሚጠበቅ ግዴታ መሆኑ በየዘመኑ ለሚነሡ አበውና ውሉድ ሁሉ ግልጽ ሊሆን ይገባል። አባቶች ወጣቱን በትምህርት ሳይወልዱና ልጆችም ከአባቶቻቸው በግብር ሳይወለዱ በመንፈሳዊው ሕይወት አባትና ልጅ ተብለው ሊጠሩ አይችሉም። ይህ ሊሆን የሚችለው አባቶች የሥጋ ልጆቻቸውን በመንፈስም መውለድ ሲችሉና ልጆችም በዚያ ዓይነት መንፈስ ተወልደው የአባቶ ቻቸው ልጆች ለመሆን ሲበቁ ነው።

ይስሐቅ በሥጋ ብቻ ሳይሆን በመንፈስም የአባቱና የእናቱ ልጅ የሆነ ወጣት ስለሆነ እንደ እናቱና አባቱ በእግዚአብሔር ዘንድ የተወ ደደና የተከበረ ሰው ሆኖ ኑሯል፤ የተባረከ ዘር ለማግኘትና የሕዝበ እግዚአብሔር አባት ለመሆን የበቃውም በሥጋ ብቻ ሳይሆን በመንፈስም የአብርሃምና ሣራ ልጅ በመሆኑ ነው።

ኢትዮጵያ የአያሌ ቅዱሳን አበው ሀገር ናት፤ ሌላው ቀርቶ ዘውድ ጥለው የመነኑና በዘውድ ሥልጣን ላይ ሁነውም የምናኔ ዓይነት ኑሮ የኖሩ መሪዎች የተገኙባት የቅዱሳን አበው መገኛ የሆነች ቅድስት ምድር ናት። አሁንም ቢሆን በእምነታቸው ጽናትና በትሩፋታቸው ብዛት የክርስትናው ዓለም የሚያደንቃቸው ምእመናን በብዛት የሚገኙት በዚህች ሀገር ነው። በመሆኑም ይስሐቅ በሃይማኖት አብርሃምንና ሣራን ለመተካት የቻለ እምሳያ ልጅ ለመሆን እንደበቃ ሁሉ እንዲሁ የኢትዮጵያ ቅዱሳን አበውን የሚተካ እምሳያ ልጅ በብዛት እንዲወለድ ከዚህ ዘመን ትውልድ ይጠበቃል። ወፍ ዘራሽ ሳይሆን የእነዚያ ቅዱሳን አበው ዘር እንዲረባ ይፈለጋል።

«ከዊንና ገቢር» የሚለው ቃል ወጣቱ በወጣትነት ዘመኑ ምን መሆንና ማድረግ እንዳለበት ለማመልከት የገባ ቃል ከሆነ ዘንድ በወጣትነት ዘመን የክርስቲያናዊ ሕይወት ከበርቱ መሆን የሚቻለው እንዲህ መሆንና እንዲህ ማድረግ ሲቻል ነው።

www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል አራት

# ወጣቱን በሚመለከት ከሃይማኖት አባቶች የሚጠበቅ የከዊንና ገቢር ግዴታ

ጥቅስ፤ «እሱም ሕዝብን በሚገባ መንገድ ለእግዚአብሔር ለማዘጋጀት፤ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች፤ የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን አእምሮ (እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ) ለመመለስ በኤልያስ መንፈስና ኃይል ይመጣል» ሉቃ.፩፡፲፯–፲፰፤ ሚል.፫፡፲፬።

ይህ ቃል ለዮሐንስ መጥመቅ የተነገረና የተፈጸመ ትንቢት እንደሆነ ከዚህ ቅዱስ መጽሐፍ ሙሉ ቃል መረዳት ይቻላል። ኤልያስ ለአምልኮቱ ቀናዒ፤ በመስተጋድሎቱ በቋዒ፤ በዚህ ዓለም ኑሮው ባሕታዊና መልአካዊ፤ በጸሎቱ ሥሙርነት ፍጹም የእግዚአብሔር ሰው መሆኑን ያረጋገጠ መንፈሳዊ አባት መሆኑ ይታወቃል። ፩ነገ.፲፯፡፩–፯፤ ፲፰፡፩–፵፯፤ ፲፱፡፩–፳፩፤ ያዕ.፭፡፲፯።

መጥመቁ ዮሐንስም በኤልያስ መንፈስና ኃይል የተነሣ ካህን፤ ነቢይና ሰማዕት ሆኖ መነሣቱ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች ለመመለስ ብቃት ያለው አባት (መምህር) ለዚህ ዓለም እጅግ በጣም አስፈላጊ እንደ ሆነ የሚያመለክት ነው። በትክክለኛ እምነትና ምግባር ጸንተው አምልኮተ እግዚአብሔርን ሲፈጽሙ የኖሩ አበውን ልብ ወደ ውሉድ እንዲተላለፍ የማድረጉ ተግባር ከምንም ነገር የሚበልጥ ኃላፊነት በመሆኑ ይህን ኃላፊነት በተግባር መወጣት ከሃይማኖት አባቶች ብቻ ሳይሆን ከወላጆችና ከኅብረተሰቡ ሕያዋን አበውም የሚጠበቅ ግዴታ መሆን ይኖርበታል። ይህ ካልሆነማ ተተኪው ትውልድ አሳዳጊ የበደለው ልቅና – ስድ አደግ ይሆንና የአገርንና የቤተ ክርስቲያንን አደራ ለመቀበል ብቃት የጎደለው መሆኑ አይቀሬ ይሆናል።

የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የመመለሱ ተግባር አፈጻጸም የሁሉም ግዴታ ሊሆን የሚችለው ወላጆች የአብርሃምና የሣራ ዓይነት እናትና አባት ከሆኑ ብቻ ነው። ያለዚያ ግን እንደ ኤሳው ያለውን አባት ልብ ወደ ልጆች እንዲመለስ ማድረግ ተተኪውን ትውልድ መበከል ስለሚሆን አለማድረጉ በኃላፊነት የሚያስጠይቅ አይሆንም።

ኢትዮጵያ ለሃይማኖታቸው ቀናዕያን የሆኑ አበውና ውሉድ ሲፈራረቁባት የኖሩ ሀገረ እግዚአብሔር ናት። በሃየማኖት ትምህርት የሀገር ነፃነትና አንድነት፤ የሰላምና ብልጽግና አስፈላጊነት የታወቀባት መጽሐፍ ቅዱሳዊት ሀገር ናት። በሕዝቧ የፈጠራ ችሎታ የአያሌ አስደናቂ ቅርሳ ቅርስ ባለቤት ለመሆን የበቃች የታሪክ ሀገር ናት። ጥንታውያን ገዳማት የሚገኙባትና አያሌ የቃል ኪዳን ቅዱሳን የተነሡባት መንፈሳዊት ሀገር ናት።

ይህ ሁሉ የሆነው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ህልውናና የተዋጣ ትምህርት ስለሆነ የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን በዚህ ኢትዮጵያዊነቱ ጸንቶ ይኖር ዘንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንንም በተዋሕዶ እምነቷና ትምህርቷ ለዘላለም ጸንታ መኖር ይኖርባታል።

## ክፍል አምስት

# የወጣቶች ኦርቶዶክሳዊ ግዴታ

፩. ኦርቶዶክሳዊ እምነትና ምግባር በአገርና ቤተ ክርስቲያን ፍቅር፤ በኢትዮጵያዊ ጨዋነትና ቁም – ነገረኝነት፤ በሰው አክባሪነትና መንፈሳዊ ጀግንነት የአባቶችና እናቶች አምሳያ ልጅ ሆኖ መገኘት፤

፪. ሲነገሩትና ሲመከሩት የሚሰማ፤ ሲመሩት የሚከተል፤ ከቶና ደግን ከስሕተት ሳይሆን ከአበው ምክርና ከቃለ እግዚአብሔር የሚማር፤ ተው ሲሉት በቀላሉ የሚመለስ ሰው አክባሪና እግዚአብሔርን ፈሪ ሆኖ መገኘት፤

፫. ሃይማኖቱንና የቤተ ክርስቲያን አባልነቱን እየቀያየረ እንደ ኤሳው ብኩርናውን/ክብሩን ለምሥር የሚሸጥ አሳፋሪ ልጅ አለመሆን፤

፬. ከጋብቻና ከድንግልናዊ ሕይወት ውጭ የሆነ ሌላ የክርስትና ሕይወት ስለሌለ የሁሉም ዓይነት ችግር መጋለጫ የሆነውን ሦስተኛውን ዓይነት ኑሮ ላለመኖር መጠንቀቅ ወይም ከዚያ ኑሮ ፈጥኖ መውጣት፤

፭. የአባቶችንና እናቶችን ኦርቶዶክሳዊ እምነትና አምልኮ በልማድ ሳይሆን በትምህርታዊ ዕውቀት በመውረስ መፈጸም፤

፮. በኦርቶዶክሳዊ ቋንቋ በመጸለይና በኦርቶዶክሳዊ ዜማ በመዘመር፤ ቅዱስ መጽሐፍን በኦርቶዶክሳዊ ቋንቋ በማንበብና በመተርጎም፤ በመማርና በማስተማር ወዘተ...አምልኮተ እግዚአብሔርን ከልጅነት ጀምሮ መፈጸም ማለት በዚህ ዓይነት ኦርቶዶክሳዊ እምነትና ምግባር በሰውና በእግዚአብሔር መካከል በጥበብና በሞገስ ማደግ፤ መጎልመስ «የወይፈን በሬ» መሆን ማለት እንደ ሕፃን ሳይሆን እንደ ባለ አእምሮ የሚያስብ የልጅ ሽማግሌ ለመሆን መብቃት፤

፯. በዚህ ዓይነት ሕይወት ሥጋዊና ዓለማዊ የሆነውን የወጣትነት ሰውነት መንፈሳዊና ሰማያዊ ማድረግ ወዘተ... ከኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ወጣቶች የሚጠበቅ ኦርቶዶክሳዊ ግዴታ ሊሆን ይገባል።

ወጣቱ ትውልድ የእግዚአብሔር መንፈስ ማለት የጥበብና የማስተዋል መንፈስ፤ የምክርና የኃይል መንፈስ፤ የዕውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ማረፊያ ከሆነ ኢሳ.፲፩፡፪ የወጣትነት ዘመን የክርስቲያናዊ ሕይወት ፍሬ የሚለቀምበት የበረከት ዘመን ሲሆን ማየት እንደ ተአምር የሚቆጠር አይሆንም።

በአሁኑ ጊዜ ይህ ዓይነቱ ሕይወት በብዙዎች ኦርቶዶክሳውያን ወጣቶች ላይ በግልጽ በመታየት ላይ ስለሆነ ቤተ ክርስቲያናችን ይህን ጸጋ ምልዓት ያለው ለማድረግ አቀባበሏን ማሳመር ይኖርባታል። የራቀውን በማቅረብና የመጣውንም በደስታ በመቀበል በመልካም አያያዝ የመጋቢነት ተግባሯን መፈጸም ይገባታል። በየአጥቢያው የሰንበት ት/ቤት በማቋቋምና በማስተማር ወጣቱ ትውልድ በጥምቀት ብቻ ሳይሆን በዕውቀትም ተወልዶ በዐራቱም ማዕዘኑ ኦርቶዶክሳዊ እንዲሆን ማድረግ ለሚያስችል ሐዋርያነትና ሐዋርያዊ ተግባር አፈጻጸም ከምንጊዜውም በበለጠ ዝግጁ መሆን ይጠበቅበታል። የወጣቱ ትውልድ እምነት እንደ ለማኝ ጥሬ ድብልቅልቁ የወጣ መሆን የለበትም። ከስንፍና ሁሉ የሚከፋ ስንፍና፤ ከድካመት ሁሉ የሚከፋ ድካመት ይሆናል። ይህ ዓይነቱ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ለቤተ ክርስቲያናችን ጥንካሬ ተጨማሪ ምልክት ስለሆነ የሚያኮራ ነው። ስለሆነም ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

የአብ ጸጋ የወልድ ቸርነት፤ የመንፈስ ቅዱስ አንድነት ከቤተ ክርስቲያናችን ወጣቶች ጋር ይሁን ዛሬም፤ ዘወትርም ለዘለዓለሙ አሜን፤ ✣

መልዓከ ታቦር ተሾመ ዘሪሁን

# ከ ወ ጣ ቱ ለ ወ ጣ ቱ

## የኔ የማሸነፍ ምሥጢር በውስጤ ካለው እምነት የሚመነጭ ነው

ሻለቃ ኃይሌ ገ/ሥላሴ

**ዛ**ሬ በሀገራችን ውስጥ ቀርቶ በመላ ዓለም የሚገኙ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች ይልቁንም ደግሞ ወጣቶች የ፳፮ ዓመቱን ሻለቃ ኃይሌ ገ/ሥላሴን ያውቁታል። ማወቅ ብቻ ሳይሆን ያደንቁታል፤ በተለይ ደግሞ የሀገሩ ልጆች፤ ያፈቅሩታል፤ ይሳሱለታል፤ ይመኩበታል፤ ይኮሩበታል።

በአበበ ቢቂላ፤ በማሞ ወልዴ፤ በምሩፅ ይፍጠር ወዘተ የተለኮሰውን የድል ችቦ በአጭር ጊዜ ወደ ሰደድ ነበልባል የለወጠው ኃይሌ፤ አበው «እስመ ስሙ ይመርሆ ሐበ ግብሩ» እንደሚሉት እናትና አባቱ ኃይሌ ሲሉት ምናልባት አልበገር ባይነቱን፤ ኃያልነቱን፤ አሸናፊነቱን ታይቷቸው ይሆናል። በዘጠኝ ወራት (እ.ኤ.አ በ፲፱፻፺፰ ዓ.ም) አምስት ሪኮርዶችን የሰበረ፤ በአጠቃላይ የአስራ አምስት ሪኮርዶች ብቸኛ ባለቤት፤ በአራት ተከታታይ የአትሌቲክስ ሻምፒዮናዎች በማሸነፍ ብቸኛው ኢትዮጵያዊና አፍሪቃዊ ኃይሌ እንደሌሎች ስፖርተኞች ባገኘው ውጤት አይኩራራም፤ አይመጻደቅም፤ ይልቁንም «ገና ምኑን ሠራሁና» ነው የሚለው። ይህ ደግሞ የቀደሙ አበው የትህትና አባባልና የአዋቂነት መገለጫ ነው።

ብዙዎቻችን ኃይሌን ከሩቁ የምናውቀው ቃሉን የማያጥፍ፤ ሀገሩን አፍቃሪ፤ በሩጫ ጥበቡ ተፎካካሪዎቹን «አሸባሪ» በመሆኑ ሊሆን ይችላል። ከሁሉም በላይ ግን ኃይሌ ሃይማኖቱን አክባሪና ትሁት ወጣትም ነው። በቅርቡ «የፈለገ ጥበብ እንግዳችን» እንዲሆንልን ባነጋገርኩ ጊዜ ጥያቄየን በደስታ ነበር የተቀበለው። ጊዜ ስላልነበረው ያነጋገርኩት በስታዲየም ልምምድ ላይ በነበረበት ወቅት ነው። የተጨዋወትነው በጣም ለአጭር ጊዜ ቢሆንም ከኃይሌ ያገኘሁት ቁም ነገር ለመንፈቅ የሚበቃ ነበር። «ከድል ስንቁ» ሻለቃ ኃይሌ ገ/ሥላሴ ጋር ያደረኩት ቃለ ምልልስ በሚከተለው መልክ አቅርቤዋለሁ።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በልጅነትህ የቤተ ክርስቲያን (የቄስ) ትምህርት ተምረህ ነበርን?

**ሻ**/ኃይሌ – በዚህ በኩል ብዙ ተማርኩ አልልም፤ ከቄስ ት/ቤቱ ይልቅ የዘመናዊው ት/ቤት ይቀርበኝ ነበር፤ አጥቢያ ቤተክርስቲያናችን ትንሽ ራቅ ይላል። ለተወሰነ ጊዜ ተከታትዬ ነበር አልጨረስኩትም፤ የተወሰነች ፊደልና አቡጊዳ ነበር የተማርኩት።

**ፈ**ለገ ጥበብ – አጥቢያ ቤተክርስቲያናችሁ ማን ይባላል?

**ሻ**/ኃይሌ – ቅዱስ ጊዮርጊስ ነበር

**ፈ**ለገ ጥበብ – ከሃይማኖት በዓላቶቻችን (እንቁጣጣሽ፤ መስቀል፤ ልደት፤ ጥምቀት፤ ፋሲካ) መካከል የቱ ነበር በይበልጥ የምትወደው? ልጅ ሳለህ ማለቴ ነው።

**ሻ**/ኃይሌ – በእውነቱ ልጅ ሳለሁ ብቻ ሳይሆን እስከ አሁንም ደስ የሚለኝ በዓል ቢኖር ጥምቀት ነው። ድሮ ልጆች ሁላችንም በአንድነት ተሰባስበን ወደ ቤተክርስቲያን የምንሄደው፤ የምንጨፍረው፤ የምንጫወተው፤ በጥምቀት በዓል ነበር። አስታውሳለሁ ጥምቀት እንደ ነገ ሆኖ ዛሬ እንቅልፍ አይወስደንም፤ ነጋ አልነጋ እያልን አሁንም አሁንም ከብርድ ልብስ መገለጥ ነው። አንዳንዴ ሳይነጋ የምንሄድበት ጊዜም ነበር። እና ጥምቀት በዓል በአከባቢያችን ትልቁ በዓል ነው፤ በሌላውም አካባቢ እንደዛ ይመስለኛል።

ከጥምቀት ቀጥሎ ፋሲካ ነው፤ ቤተሰቦቼ የካህናት ቤተሰብ ጠንካራ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ስለሆኑ ፋሲካን በደመቀ ሁኔታ ነው የምናከብረው።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ከፍተኛ የሆነ የቤተክርስቲያን ፍቅር፤ ጽኑ እምነት እንዳለህ በቅርብ ከሚያውቁህና ከሃይማኖት አባቶች ሰምቻለሁ። ይህ ሊሆን የቻለው ቤተሰቦችህ ለሃይማኖታቸው ካላቸው ፍቅር የወረስከው ነው ወይስ ሌላ ምክንያት ይኖርሃል?

**ሻ**/ኃይሌ – ምክንያቱ እንዲህ ነው ማለት ያስቸግራል፤ ለምን ቢባል እምነት እንዴትና ከምን እንደሚመጣ አይታወቅም፤ እኔ ቅዱስ ጊዮርጊስንና ኪዳነ ምሕረትን በጣም በጣም እወዳቸዋለሁ፤ በተለይ ደግሞ ለኪዳነ ምሕረት ያለኝ ፍቅር የተለየ ነው። ለኪዳነ ምሕረት ይህን ፈጽሚልኝ፤ ይህንን አድርጊልኝ ብዬ ነግሬያት





www.ethiopianorthodox.org

እንዲት ነገር ሳትፈጽምልኝ የቀረችው ነገር የለም። ቅዱስ ጊዮርጊስም እንደዚሁ፤ እኔ ግን የምወዳቸው ያል ኩዋቸውን ሁሉ ስለፈጸሙልኝ (ስለሚፈጽሙልኝ) አይደለም። እምነቱ ከድሮ ከአያት ቅድመ አያቶቼ ተያይዞ የመጣ ስለሆነ ነው። ስለዚህ እምነት ለሥራ ወይም ለሌላ ጊዜያዊ ጥቅም ብለው የሚከተሉት አይደለም፤ እምነት ለራስ ነው፤ ሰዎች በእግዚአብሔር እመኑ ማለት በሕይወታቸው አንድ ታላቅ ነገር ጨበጡ ማለት ነው። በእኔ አስተሳሰብ እምነት የሌለው ሰው በሕይወቱ ውስጥ እየኖረ ሳይሆን እንደ በድን (ባዶ) ነው።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በተለያዩ ጊዜያት ወደ ቁልቢ ቅዱስ ገብርኤል ስሄድ «ቅዱስ ገብርኤል በዚህ ውድድር እንዳሸንፍ ያደረግህልኝ እንደሆን …ይህን አደርጋለሁ…ይህን እሰጥ ሃለሁ» የሚሉ ከአትሌቶች የተጻፉ (የአትሌቶች ስም የሌላቸው) የስለት ደብዳቤዎች ያጋጥሙኛል። ከእነዚህ አትሌቶች አንዱ አንተ ትሆን እንዴ?

**ሻ**/ኃይሌ – በተለይ ቅዱስ ገብርኤልን በተመለከተ እኔ ሳልሆን አንድ ጊዜ ታላቅ ወንድሜ ስለኔ ተስሎልኝ ነበር። በ፲፱፻፹፬ ዓ.ም ስቱትጋርድ ውድድር ነበረብኝ። በዛን ጊዜ ወንድሜ «በዚህ ውድድር ካሸነፈ በሚሸለማት መኪና አንተ ዘንድ (ገብርኤል) ይዤው እመጣለሁ» ብሎ ተሳለ። በስለቱ መሠረት ጉዞአችንን ወደዛ ቀጠልን። በእውነቱ የስለት ነገር በጣም ከባድ ነው። ከተሳልክ ስለትህን ሳትጨምር ሳትቀንስ መስጠት (መመለስ) አለብህ። ወንድሜ የተሳለው «በሚ ሸለማት መኪና ይዤው እመጣለሁ» ብሎ ነው። ወደ ቁልቢ ስንሄድ ግን ወንድሜ የተሸለምኩዋትን መኪና እየነዳ እኔ ደግሞ በሌላ መኪና ፊትና ኋላ ሆነን ነበር የምንጓዘው። በዚህ መልክ ስንጓዝ ገብርኤል ልንደርስ የተወሰነ ኪ/ሜ/ ሲቀረን (አዋሽ እንዳለፍን) የነበርኩባት መኪና ተገልብጣ ፊቷን ወደ አዲስ አበባ አዙራ ቆመች።

መኪናዋ እንዳልነበረች ነበር የሆነችው፤ በእኔ ላይም ሆነ አብረውኝ በነበሩ በባለቤቴና በወንድሜ ላይ ግን ትንሽ ጭረትም እንኳ አልነበረንም፤ ለምልክትም አልተነካንም። መኪናዋ እንደዛ ተጨረማምታና ተሰባብራ ያዩ ሰዎች «ከዚህ አደጋ እንዴት ሰው በሕይወት ሊተርፍ ይችላል?» እያሉ ይገረሙና የእግዚአብሔርን ተአምር ያደንቁ ነበር። ከዛ በኋላ ገብርኤል እንኳን ከዚህ አደጋ አተረፍከኝ እንጂ መኪናዋ የራስዋ ጉዳይ ብዬ በተሳልኩባት መኪና በመሆን ጉዞዬን ወደ ገብርኤል ቀጠልኩ። በሰላምም ተሳልሜ ተመለስኩ። እና ያመንክበት እምነትህ የተሳልከውን ነገር መፈጸም አለብህ። ቅዱስ ገብርኤል እኔን ለመጉዳት ቢፈልግ አያቅተውም፤ እርሱ ግን ሊያስትምረኝ ነው የፈለ ገው፤ አስተማረኝ፤ እምነት ማለት ለአንድ ለሰው ልጅ ሕይወት አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ወሳኝ የሆነ ነገርም ነው።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በዓለማችን ታዋቂ የሆኑ ስፖርተኞችን ከነበሩበት እምነት ወደ ሌላ ሃይማኖት ለማስቀየር የሚደረግ ጥረትና እንቅስቃሴ እንዳለ ይታወቃል። በዚህም ለገንዘብና ለጊዜያዊ ጥቅም ሲሉ ሃይማኖ ታቸውን የለወጡ፤ ዜግነታቸውን የቀየሩ ስፖርተኞች እንዳሉ አንተም ታውቃለህ። በበኩልህ የዚህ ዓይነት ፈተና አጋጥሞህ ያውቃል? እግረ መንገድህንም በእምነትህ ምክንያት የደረሰብህ ችግር ካለ ብትገልጽልኝ?

**ሻ**/ኃይሌ – በዚህ በኩል በጣም…በጣም…ብዙ ነው። በተለይ ደግሞ በዚሁ በኛ ሀገር። እኔ ግን በዚህ በኩል የሚመጡትን በትህትና ጥሩ ነው እያልኩ ነው የምመልሳቸው፤ በበኩሌ ረዥም ታሪክ ያለው መመኪያችን፤ መከበሪያችን፤ መለያችን የሆነውን የኦርቶዶክስ ሃይማኖት እያለኝ ሌላ ሃይማኖት አልመኝም፤ ቅድመ አያቴ ቄስ ነበሩ፤ ሌሎችም መላ ቤተሰቦቼ የእግዚ አብሔር አገልጋዮች ናቸው። ታቦት የሚተክሉ፤ አብያተ ክርስቲያናት የሚያሳንጹ አገልጋዮች ስለሆኑ ይህንን የመሰለ እምነት ትቼ ለምን ሌላ ሃይማኖት እይዛለሁ? ብሎ ለት በእም ነቴ ስለምጸና ነው እንጂ ምክራውማ! ፈተናውማ ምኑ ተነግሮ!!


አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ያሉ የሃይማኖቶች ቁጥር እኔም አንተም በትክክል አናውቀውም፤ በእውነት ለኢትዮጵያውያን (ሁሉም የየራሱ እምነት መያዝ ቢችልም) በተለይ ደግሞ ለኔ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነት የተሻለ አለ ብዬ አላምንም። ፈተናው ግን እጅግ ከባድ ነበር። ኦርቶዶክስ በመሆኔ ግን እግዚአብሔር ይመስገን በሥራዬ ተጽእኖ አልደረሰብኝም፤ እንዲያውም ኦርቶዶክስ በመሆኔ ክብር ነው ያገኘሁት፤ እምነቴ አስከብሮኛል።

**ፈ**ለገ ጥበብ – የሥራ ጠባይህ (የስፖርት ተግባርህ) በጾምና በጸሎት ላይ የሚያሳድርብህ ተጽዕኖ ይኖራል?

**ሻ**/ ኃይሌ – በዚህ ነገር የሚያስቸግረኝ የለም፤ አንድ ነገር ግን ልነግርህ እፈልጋለሁ፤ በአሁኑ ወቅት እኔ አልጾምም፤ ምክንያቱ በተለያዩ ሀገሮች እሄዳለሁ፤ ለምሳሌ ያህል አርብና ሮብ እንኳን ልጹም ብል አንድ ችግር አለ፤ እዚህ ሮብ ቢሆን እዛኛው ሀገር ሐሙስ ወይም ማክሰኞ ይሆናል። ስለዚህ ስፖርቱን እስካቆም ድረስ መጾም የሚሆንልኝ አይመስለኝም። ስፖርቱን ሳቆም ግን እኔ እንጃ…በእምነት ደረጃ ይህን እሆናለሁ ይህን እፈጽማለሁ አይባልም፤ ትልቁ ነገር ግን ጋብቻዬ የተክሊል ጋብቻ ነው፤ ስለዚህ ለወደፊቱ በተቻለኝ መጠን የአጽዋማትን ሥርዓት እፈጽማለሁ፤ ለዚህም እግዚአብሔር ይረዳኛል።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ባለፈው ፈለገ ጥበብ መጽሔታችን ዶክተር የማነ የአሸናፊነትን ምስጢር አስመልክ ተው ባቀረቡት ጽሑፍ አንተን በመጥቀስ የኃይሌ የማሸነፍ ምሥጢር «በራስ ከመተማመን መንፈስ የመነጨ ነው» የሚል ሐረግ አስፍረው ነበር። ይህንን የዶክተር አባባል ምን ያህል ታምንበታለህ?

**ፈ**ለገ ጥበብ – ቀደም ሲል ቅዱስ ጊዮርጊስ በተለይ ደግሞ ኪዳነ ምሕረትን በይበልጥ እንደምታፈቅር




**ሻ**/ ኃይሌ – በዚህ አምንበ ታለሁ፤ የምጨምርበት ግን አለ፤ በራስ የመተማመን መንፈስ ሊመጣ የሚችለው ጠንካራ እምነት ሲኖር ነው እላለሁ። እምነት ካለህ ታሸንፋለህ፤ እምነት ከሌለህ ግን በራስ የመተማመን መንፈስ የሚገኝ አይመስለኝም። የራሴን በተመለከተ የኔ የማሸነፍ ምስጢር በአብዛኛው ያለው በውስጤ ካለው እምነት ነው።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ብዙውን ጊዜ ፊትህ ፈገግታ አይለየውም፤ ሳቂታና ደስተኛም ሆነህ ነው የምትታየው፤ ይህ ባሕሪይህ ለአሸናፊነትህ ያበረ ከትከው አስተዋጽኦ አለው ትላለህ?

**ሻ**/ኃይሌ – አንድ አስተዋጽኦ አለው እላለሁ፤ ስፖርት የምሠራው ለመደሰት፤ ለመጫወት ነው፤ ስለዚህ እግዚአብሔር እስከፈቀደ ድረስ ለወደፊቱም ከዚህ የተለየ ባሕርይ ይኖረኛል ብዬ አላምንም፤ ልቀይር ብልም አልችልም።

ነግረኸኛል፤ ብዙ ሰዎችም እንዳን ተው አብልጠው የሚያከብሩዋቸው ታቦታት አሉዋቸው፤ ለዚህም ሁሉም ሰው የየራሱ የሆነ ምክንያት ሊኖረው ይችላል ያንተውን ልትነግረኝ ትችላለህ?

**ሻ**/ ኃይሌ – እንደ ነገርኩህ ጊዮርጊስ ያው ተወልጄ ያደግኩበት አጥቢያዬ ነው። እንዲያውም ሕፃን ሳለሁ ቤተክርስቲያን ሁሉ ጊዮርጊስ ብቻ ነበር የሚመስለኝ። ከዛን ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ቅዱስ ጊዮርጊስን አፈቅረዋለሁ። እዚህ ላይ ለኔ ሁሉም ታቦት ማርያም፤ ሚካኤል፤ ገብርኤል… ልዩ ስፍራ አላቸው፤ በተለይ እየሄድኩ ጸሎት የማደርግባቸው ደግሞ አሉ። ለምሳሌ እዚህ አዲስ አበባ እስካለሁ ኪዳነ ምሕረት አልቀርም። ደጇን ሳልረግጥ አልውልም። ምክንያቱን ግን እኔም አላውቀውም፤ የሷ ሥራ ነው።

**ፈ**ለገ ጥበብ – እግዚአብሔር እዛ ያድርስህና በእድሜ እየገፋህ መጥተህ የሩጫው ጊዜህን ስትፈጽም ቀሪ ሕይወትህን ምን እየሠራህ ለማሳለፍ ነው ያቀድከው?

**ሻ**/ ኃይሌ – ብዙ ዕቅድ አለኝ፤ እንደምታየው ሩጫ ጊዜያዊ ነገር ነው። አንዳንድ ለሕይወቴ የሚረዱኝ ነገሮች እሠራለሁ እላለሁ። ያ አደርጋለሁ፤ እንደዚህ እሠራለሁ ብዬ ግን ከአሁኑ ማወቅ አልችልም። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ያኔ ጊዜው ይወስነዋል።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በዚህ አጋጣሚ ለእድሜ አቻዎችህ ለሆኑ ወጣቶች የምታስተላልፈው መልእክት ይኖርሃል?

**ሻ**/ ኃይሌ – ወጣት ማለት ከእናት ከአባቱ የተረከበውን እምነት ማቆየት ብቻ ሳይሆን ሀገርን የሚረከብ፤ አባት እናቱን የሚጦር፤ ሀገሩን የሚያስከብር መሆን አለበት። አሁን በወጣቱ ላይ አንድ በጣም አሳሳቢ የሆነ ነገር መጥቶበታል። ሁላችንም እንደምናውቀው (የሁለት ዓመት ሕፃንም ሳያውቀው አይቀርም) ኤድስ ወጣቱን በጣም እያጠቃው ነው። ወጣቱ ከዚህ የኤድስ በሽታ ራሱን መከላከል መቻል አለበት፤ ከዚህ በሽታ ሊድን የሚችለው ደግሞ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ያከበረ እንደ ሆነ ብቻ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? ቤተክርስቲያን ምን ትላለች? በማለት በሥነ ሥርዓት መኖር አለበት። እኛ ወጣቶች ሀገራችን ልንገነባ ራሳችንን ልንጠቅም የምን ችለው በቅድሚያ ራሳችንን ከዚህ ቀሳፊ በሽታ ማዳን ስንችል ነውና መልእክቴ ይኸው ነው።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ኪዳነ ምሕረት በሄድክበት ሁሉ ትከተልህ።

**ሻ**/ኃይሌ – አሜን ለሁላችን።

www.ethiopianorthodox.org

# «መልካም እረኛ እኔ ነኝ» የሐ.፲፥፩–፲፩

ከመምህር ቀጸላ መንግሥቱ



ይህን ቃል የተናገረው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን በመልካም እረኛ የተመሰለ እርሱ በአባግዕ የተመሰሉ ምእመናን ናቸው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እራሱን በመልካም እረኛ መስሎ የተናገረበት፤

፩. በዮሐንስ ወንጌል በምዕራፍ ፱ እንደተጻፈ ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው በደረቅ ግንባር ዓይን ፈጥሮ ያዳነውን እንዳ ያመሰግንና እንዳያምን ባንገላቱት ጊዜና እርሱንም የጸረፉበትን ኃይለ ቃል ለማስተካከል ነው።

ሀ. ሑር ሀብ ስብሐተ ለእግዚ. አብሔር ንሕነሰ ነአምር ከመ ኃጥእ ውእቱ ዝ ብእሲ፤ ያዳነህ እግዚአ ብሔር ነው እንጂ ይህ ሰው ኃጢአተኛ በመሆኑ አላዳነህምና ለእግዚአብሔር ምስጋና አቅርብ ብለውታልና ኃጥእ እንዳልሆነ ጌር ኖላዊ መሆኑን በሥራው ለመግለጥ፤

ለ. እግዚአብሔር ሙሴን ቃል በቃል እንደ ተነጋገረው እናውቃለንና የሙሴ ደቀ መዛሙርት ነን በማለት ከፈጣሪያቸው ፍጡርን ከመምረ ጣቸውም በላይ «ወለዝንቱሰ ብእሲ. ኢነአምር እም አይቴ ውእቱ» ይህን ሰው ግን ከየት እንደመጣ አናውቀ ውም ስላሉት ከየት እንደመጣ ለማስ ረዳት ነው። ይህም ቃል፤ ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ ብሎ ወደ ፈጣሪያቸው ሕዝቦች እንዲሁም ወልድየ ዘበኩርየ ብሎ ወደ መረጣ ቸው ወገኖቹ መጣ። እነሱ ግን አልተ ቀበሉትም ተብሎአልና። ውስተ ዚአሁ መጽአ ወእሊአሁ ኢተወከ ፍዎ እንዲል፤

ሐ. «አንሰ መጻእኩ ለኵነኔ ዝንቱ ዓለም ከመ እለ ኢይሬ እዩ ይርአዩ ወእለ ይሬእዩ ይዑሩ» እናውቅም በሚሉ ሐዋርያት ልፈርድላቸው፥ እናውቃለን በሚሉ ፈሪሳውያን ልፈርድባቸው መጥቼአለሁ ብሎ ነበርና ለምሕረት እንደ መጣ ለማጠየቅ ነው።

፪. «አማን አማን እብለክሙ ዘኢቦእ እንተ አንቀጽ ውስተ አጸደ አባግዕ ወአርገ እንተ ካልዕ ገጽ ሠራቂ ወጕህልያ ውእቱ» ያላቸውን በግብ ሐዋርያት ምዕ.፭.... የተወቀሱትን ቴዎዳስ ዘግብጽና ይሁዳ ዘገሊላ የመሰሉ ናቸው። ቴዎዳስ ዘግብጽ እኔ አምላክ ነኝ በማለት አራት መቶ ያህል ሰዎችን አስከትሎ ነበር፤ ነገር ግን ይህ መስሐቲ ጠፋ፤ አምነው የተከተ ሉትም ሁሉ ጠፉ፤ እንደ ምናምንቴም ሆኑ ይላል። ይሁዳ ዘገሊላም በዚያው ወራት ብዙ ሰዎችን ከእውነተኛው እምነት አስፈንግጦ አስኮብልሎ በማሸፈት እርሱን እንዲከተሉና እንዲያምኑ ስላደረገ እርሱም ጠፋ። ያመኑበትም ሁሉ ጠፉ፤ ተቀሰፉ። ምክንያቱም ወደ በጎች በረት በበሩ የማይገባና የማይወጣ ሌባና ወንበዴ ነው ተብሎ ተጽፎአልና።

ደግሞ ሌባ ሊሰርቅ፤ ሊያርድና ሊያጠፋ እንጂ ለሌላ አይመጣምና ነው። በአንጻሩ ግን መልካም እረኛ ሰውነቱን ለበጎች አሳልፎ ይሰጣል። እኔም ሕይወት እንዲሆንላቸውና እንዲበዛላቸው ስለመጣሁ መልካም እረኛ እኔ ነኝ አለ።

፫. በብሉይ ኪዳን የነበሩትን መኳንንት፤ መሳፍንት በሕዝቅኤል አድሮ ሲገስጻቸው «አሌ ሎሙ ለኖሎተ እስራኤል ወኢርእዩ አባግዕየ እለ ኮኑ ኖሎተ ርእሶሙ» ብሎአ ቸዋል። ሕዝ.፴፬፥፩–፲፰፤ ኢሳ. ፶፥፲፩።

እኒህ የእስራኤል መሪዎች ጠባቂዎች መሳፍንቱና መኳንንቱ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ሥል ጣን ራሳቸውን በድሎት፤ በምቾት፤ በተድላ በደስታ ጠበቁበት፤ እንዲ ሁም ከሥጋዊ ጠላት ከረሃብ፤ ከንዴት በመጠበቅ ተገለገሉበት እንጂ ራሳቸውን ከክሕደት፤ ከኃጢአት አልጠበቁበትም ምክንያቱም መሾማ ቸው መሳፍንቱ፤ መኳንንቱ ህዝቡን ሊጠብቁ ከዓመፅ ሊርቁ፤ ለተራበ በግብር ለተበደለ በነገር ሊገኙ ነበር። እነርሱ ግን «በልዑ ሰብሐ» ሰብህ ትርፍ ሥጋ ነው። ስለዚህ «ኢትንሣእ ኀልያን» የምትል ሕግ እያለቻቸው ትርፍ ገንዘብ ይበላሉ፤ መማለጃ ይቀበላሉ። ይህ ተግሣጽ ለመኳንንቱ ብቻ አይደለም፤ የሹመት ማዕረግ ላላቸው ሁሉ ለሚዳኙ ነው እንጂ ዘጸአ ፳፫፥፰። «ወይለብሱ ጸምረ» ከድሆች ወስደው በተረፈ ልብሳ ቸውን ይገፋሉ የላም መንጃ፤ የሸማ መከንጃ፤ የማር መቅጃ፤ የሠፋሪ፤ የቆጣሪ የሚሉት አለና። «ወዘደከመ ኢያጸንዑ» እንደ ተባለው በጣዖት የደከመውን በአሪት አያጸኑትም። እንደ ኢዮሳፍና፤ ኢዮሳፍጥ «ሑሩ ወመሐሩ አሪተ ውስተ ኵሉ ምድረ ይሁዳ» ብሎ ባወጀ ጊዜ በመላው በምድረ ይሁዳ አሪት ተሰብካ ነበር። እነርሱ ግን በአምልኮተ እግዚአ ብሔር፤ በገቢረ ጽድቅ ሕዝቡን መምራት ሲገባቸው ለሥጋዊ ፍላጐ ታቸውና ለምድራዊ ተድላ ማመ ቻቺያ አደረጉት «ወዘሐመ ኢትፈ ውሱ፤ ወዘተሰብረ ኢትሐድሱ» እንደ ተባለው በክሕደት

የታመመውን በሃየማኖት አይፈው ሱትም፤ በኃጢአት የተሰበረውን በንስሐ አይጠግኑትም «ወዘጉየ ኢይመይጡ» ግብር መርት አገዛዝ ጸንቶበት በስደት አገር ጥሎ ቁርበት ጠቅልሎ የሄደውን ባዋጅ ከርስቱ ከነገዱ አይመልሱትም። «ወዘተገድፈ አይሐስሱ በዑዋዌ» የጠፋውን በማጣት አይመልሱትም። እውነተ ኛው እረኛ ግን ከነዚህ የተለየ በመሆኑ «ለልየ እርዕዮሙ ለአባግዕየ ወአነ አዐርፈክሙ ይቤ አዶናይ እግዚአ ብሔር» እኔ በካህናት አድሬ እጠብ ቃችኋለሁ፤ ለነገሥታት ከመገዛት አሳርፋችኋለሁ ለጊዜው ይህ ሲሆን ፍጻሜው ግን ሰው ሁኜ ሥጋ ለብሼ አድናችኋለሁ ማለትን ያሳያል። «ንዑ ኀቤዩ ኵልክሙ ሥሩኃን ወክቡዳነ ጾር ወአነ አዓርፈክሙ» ማቴ.፲፩፥፳፰ ሸክማችሁ የከበዳችሁ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ «እስመ አርዑት የኒ ሠናይ ወጾር የኒ ቀሊል» ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀላል ነውና ይላል። «አሐስስ ዘተገድፈ ወእመይጥ ዘጕየ» በዑዋዊ የጠፋውን በሚጠት እመልሳለሁ (እሻዋለሁ) በስደት የሄደውን በዓዋጅ እመልሳለሁ ዕዝ.፩፥፩። «እሔድስ ዘተሰብረ ወአጸንዕ ዘደከመ» በኃጢአት የተሰበረውን በንስሐ አድሳለሁ በጣዖት የደከመውን በሃይማኖት አጸናዋለሁ በማለት መልካም እረኝነቱን ያስረዳል። እነሱ ግን «ወይሰትዩ ጽሩየ ማየ» ግብሩን አሥራቱን ይቀበላሉ ወገኖቹ ግን ከሠራዊታቸው የተረፈውን ይመገ ባሉ፤ ከእህሉም፤ ከዘይቱም፤ ጥሩ ጥሩውን ወስደው አዳፋውን አተላውን ይተውላቸዋልና በእንቢ ታቸው በደንደሳቸው ይጋፋሉ ደሃ ውን፤ ደካማውን በሥልጣናቸው ያጠ ቃሉ በስደት በዑዋዊ እስኪበተኑ፤ ለአሕዛብ ምግብ እስኪሆኑ ድረስ ህዝቡን ያጠፉቸዋል፤ እርሱ ግን

ወገኖቹን ከመኳንንቱ ከነገሥታቱ አድኖ ዳግም ለምርኮ ለዘረፋ አይዳርጋቸውም መልካም እረኛነቱን በዚህ ያረጋግጣል። እንዲሁም በዮሐ.፳፩፥፲፮ ቅዱስ ጴጥሮስን ያገለግሎቱን የፍቅሩ መግለጫ ያደረገው በየደረጃቸው መጠበቅ ያለባቸውን ምእመናን በጎቹን ጠብቅ፤ ግልገሎቹን ጠብቅ፤ ጠቦቶ ቹን ጠብቅ ሲል አስገንዝቧል።

መልካም እረኛ የደከሙትን በጎች በማጽናናት የታመሙትን በማሳከም፤ ግልገሎቹን በመታቀፍ ለበጎቹ ያለ ውን ፍቅር ይገልጻል።

የመልካም እረኛ መጀመሪያ ለበጎቹ የሚጨነቅ፤ የሚያስብ በመሆኑ ወደ ለመለመ መስክ ወደ ጠራ ውሃ ያሰማራቸዋል፤ ከሌባ ከተኩላ ይጠብቃቸዋል። ፊት ለፊትም ይሄድላቸዋል። እነሱም እሱን አብነት አድርገው ይከተሉታል። በጎቹንም ያውቃል በጎቹም ያውቁታል። የማያውቁትን እረኛ ግን አይከተሉትም። መልካም እረኛ በጎቹ እንዳይጠሙ፤ እንዳይራቡ፤ እንዲጨነቅ መልካም እረኛ ክርስቶስም ምእመናኑን ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ፤ በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ ያመኑበት፤ ሊቀበሉት ስለአላቸው መንፈስ ቅዱስ ተናገሯል። ዮሐ.፯፥፴፯–፴። ይህንን የሕይወት ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ለዘላለም አይጠማም። እኔ የምሰጠው ውኃ በእርሱ ውስጥ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የሕይወት ምንጭ ነውና። ዮሐ.፬፥፲፫–፲፬። የዚህ ዓለም እረኛ ምንም ለጊዜው የጠራ ውኃ ቢመርጥ ቆይቶ የሚጐሽ የሚደፈርስ ጥራጊ ቆሻሻ የሚወድቅበት የሚደርቅ እና ዳግም የሚያስጠማ ነውና የሕይወት ውኃ ሊሆን አይችልም። ይህን የሕይወት ውኃ ከባሕርዩ የሚፈልቅ ደግሞ የማያስጠማ የሰጠን መልካም እረኛ ነው።

የዚህ ዓለም እረኛ በጎቹን ለጊዜው ወደ ለመለመ መስክ ቢያሰማራቸው፤ ቆይቶ የሚደርቅ በጭቃ እግር የሚረገጥ ደግሞም የሚያስርብ ልምላሜውም ወቅትና ጊዜ የሚጠብቅ ነው። መልካሙ እረኛ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚሰጠው ምግብና መጠጥ ግን «የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምንም ሁል ጊዜ ከቶ አይጠማም» ይላል። ዮሐ. ፮፥፴፭–፴፮። የዚህ ዓለም እረኛ ስለበጎቹ ሕይወቱን አሳልፎ አይሰጥም መልካሙ እረኛ ክርስቶስ ግን ስለ በጎቹ ሕይወቱን አሳልፎ የሚሰጥ ከበጎቹም በፊት ተላልፎ የሚሰጥ ነው። ምክንያቱም ዓለም የምትድነው በእኔ ደም ነው ብሏልና ይህም ምን ያህል ሰውን መውደዱን ያስረዳል። ከዚህ በፊት የሕዝብ እረኛ የነበሩ ሙሴ ዳዊት ስለ ሕዝባቸው ሲሉ ተላልፈው ሕይወታቸውን በመስጠት ቆርጠው እንደ ተነሱ በብሉይ ኪዳን መጽሐፍ እንረዳለን። ሙሴ ሕገ ኦሪትን በደብረ ሲና ከእግዚአብሔር ለመቀበል ሄዶ ሳለ ቢዘገይ፤ እስራኤል፤ «አሮን አሮን ግበር ለነ አማልክተ ለየሐውሩ ቅድሜነ ወይጸብኡ ጸረነ» አሮን፤ በፊት በፊታችን የሚሄዱ ጠላቶቻችንን ድል የሚነሱ (የሚቃወሙ) አማልክት ሥራልን አሉት። እስመ ዝኩሰ ሙሴ ዘአውጽአነ ምድረ ግብጽ ኢነአምር ከመ ምንተ ኮነ፤ ይህ ከግብጽ ያወጣን ሙሴ፤ አመሌ አመሌ ሲል ያያት የደብረ ሲና እሳት በልታው እንደሆነ ወይም ወደ ግብጽ ሲሄድ ኤርትራ አሰጥሞት እንደሆነ አለበለዚያም ወደ አማቱ አገር ወደ ምድያም ሲሄድ አውሬ በልቶት እንደሆነ አናውቅም ብለው አሮንን ባስገደዱት ጊዜ አሮን

www.ethiopianorthodox.org

ስለ ፈራቸው ጣዖት አቁሞ እስራኤል ሆይ ከግብጽ ያወጡህ አማልክት እኒሕውልህ አለ። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ተቆጣ በእስራኤልም ላይ መዓት እንደሚያመጣ ሙሴንም ከእነርሱ ለሚበልጥ ሕዝብ እንደሚሾመው ቢጠይቀው እነርሱን ከምታ ጠፋቸው ከመዘገብከኝ የሕይወት መጽሐፍ እኔን ፋቀኝ ብሎ ሕይወቱን ለሚጠብቃቸው አሳልፎ ለመስጠት ወሰነ። ዘጸ.፴፪። ዳዊትም መልአክ መደምሰስ በዓውደ ኦርና የሚጠብቃቸውን ሕዝቦች ባጠፋ ጊዜ ምንተ ገብሩ እሉ አባግዕ እንዘ እኒኖላዊሆሙ ዘአበስኩ እኒህ በጎች ምን ሠሩ፤ እኔ ጠባቂያቸው እረኛቸው በድዬ ሳለ ስለዚህ የታዘዘው መቅሰፍት በእኔና በቤተሰቦቼ ይሁን አለ። ስለ ወገኖቹ ፍቅርም የራሱንና የቤተሰቦቹን ሕይወት አሳልፎ ለመስጠት ወሰነ። መልካም እረኛ ይ኿ል ይህ ነው። ፪ሳሙ.፳፬። እረኞች የሚላቸው በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር የመረጣቸው መሳፍንቱ መኳንንቱ ነገሥታቱ ካህናቱ ናቸው።

በሐዲስ ኪዳንም እስመ ኢይሰየም መኮንን ዘእንበለ እም ኀበ እግዚአብሔር ይላልና ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ መሾም መመረጥ ስለማይቻል ሁል ጊዜ መሪዎች ከእግዚአብሔር ይላካሉ። እግዚአብሔር፤ የላከውም መምህር የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራል። ዮሐ.፫፥፴፬። ነገር ግን እግዚአብሔር ያልላካቸው በእግዚአብሔር ስም የሚነግዱ እግዚአብሔር ያላዘዘውን በስሙ በድፍረት የሚናገሩ ወይም በሌሎች አማልክት ስም የሚናገር ነቢይ እርሱ ይገደል። እግዚአብሔርም ያልተናገረውን ቃል እንደ ተናገረ የምናውቀው ያ የተናገረው ቃል ሳይደርስ ሲቀር ነው። ዘዳ.፲፰፥፲፰–፳፪።

ስለዚህም ዛሬ ከእግዚአብሔር ተልከናል እያሉ ከነቢያት፣ ከሐዋርያት፣ ከሊቃውንት በተላ ለፈው ትምህርተ ሃይማኖት ፀንታ የኖረችውን የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት ለማናጋት የመጡትን የዘመኑ ሐሳውያን መሲሕ መጋለጥ ይኖርባቸዋል። መልካሙ እረኛ ከእግዚአብሔር የተላከ መሆኑን የምናረጋግጥባት፤

፩. የተናገረው ቃል የሚደርስ በመሆኑ ነው።

፪ኛ. የተናገረውን በተግባር የሚፈጽም መሆኑን ነው። ምክንያቱም የተናገረውን በተግባር የማይፈጽም ከሆነ አስመሳይና አታላይ ነው እንጂ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ሊሆን አይችልም። መጽሐፍ ለሌላው የምታስተምረውን ራስህን እንዴት አታስተምርም? ተው የፋና የገንዳ ይደርስብህ የለምን? ፋና ለሌላ ሲያበራ እሱ ይከስላል። ገንዳም ሌላውን ሲያጠራ እሱ ያድፋል። ሌላውን ሲያለመልም እርሱ ይደርቃልና ሮሜ.፪፥፳፩። ምሳሌ፤ አንድ ሊቅ ትርጓሜ መጻሕፍት እያስተማሩ ሳለ አንድ የራበው፣ ጉን የራቀው ሰው መጥቶ ስመ እግዚአብሔር ጠርቶ ራበኝ ጠማኝ ሲላቸው ረሀብስ ኢሰሚአ ቃለ እግዚአብሔር፤ ረሀብ ማለት የእግዚአብሔርን ቃል አለመስማት ነው ተቀመጥ አድምጥ አሉት። እርሱም ርቦታልና ጥሎአቸው በአቅራቢያቸው ወደምትገኝ ሴት ሲሄድ ጥሬ እያነፈሰች አገኛትና ስመ እግዚአብሔር ጠርቶ ለመናት፤ እርሷም ከያዘችው ጥሬ ቆንጥራ ብትሰጠው ነፍሱ ገብታ ሰውነቱ ተመለሰ። እዩት በዚህ ጊዜ እኒያ መተርጕም ንሕነ ናነብብ ወይእቲ ትተረጕም። ዛሬ በዘመናችን ተርጓሚ፣ ሰባኪ፣ አስተማሪ አለ። ግን የተናገረውን እሱ የማይፈጽመው ከሆነ አንባቢ እንጂ ተርጓሚ አይደለም። እንዲሁም አንድ አስተማሪ በማቴ.፲፪፥፵፯ ላይ ከደቀመዛሙርቱ አንዱ...መጥቶ እነሆ ወንድሞችህና እናትህ ሊገናኙህ መጥተው ከደጅ ቆመዋል አለው። ለነገረው ሰው እንዲህ አለው፤ እናቴ ማን ናት? ወንድሞቼስ እነማን ናቸው? አለና እጁን ወደ ደቀመዛሙርቱ አመለከተ፤ እናቴም ወንድሞቼም እነሆ በጉባዔ ያሉ ሕዝብ ናቸው አላቸው። የሰማይ አባቴን ፈቃድ የሚፈጽም ሁሉ እናቴም ወንድሜም እሱ ነው። አለና በዚህ ጉባኤ ያለነው ሁሉ እህትማማቾች ወንድማማቾች ነን ብሎ አስተምሮ ወደ ቤቱ ሄደ። ከቤቱ ከሄደ በኋላ ለዘበኛው ማንም ሰው እኔን ቢጠይቅህ የሉም በል ብሎ ትእዛዝ ሰጠው። በዚህ ጊዜ ትምህርቱን በጉባኤ ሲከታተል የነበረው አንድ ሰው የአስተማሪውን ቤት ጠይቆ ሄደና ባገኘው ጊዜ በር ቆረቆረ። በረኛውም ምነው ቢለው ወንድሜን ላነጋግር እፈልጋለሁ አለ። እሱም እንደ ታዘዘው የሉም አለው። ጭቅጭቅ በተነሣ ጊዜ ያ አስተማሪ ወጣና ምንድነህ? አለው። ያሰው እኔ እኮ ወንድምህ ነኝ አነጋግረኝ አለው። ያ አስተማሪ ፈረንጅ ነበርና ይህኛው ጠያቂው አፍሪቃዊ ስለሆነ እንኳን እንዳንተ ያለ እንደኔ ያለ ወንድምም የለኝ አለው። እዚያኮ ሲያስተምሩ በትምህርት ገበታ ያለነው ወንድማማቾች ነን ስላሉ ትምህርቱን በጉባዔ ከተከታተሉት አንዱ እኔ ነኝና ወንድምህ ነኝ አለው። አስተማሪውም መልሶ ያማ ከዚያው ነው እንጂ ከዚህ አይደለም አለ።

ስለዚህ ይህ አስትማሪ የተናገረውን በተግባር የማይፈጽም በመንፈሳዊ ሕይወት የባህርይ ለውጥ የማይታይበት አታላይና አስመሳይ ነው ማለት ይቻላል። ስለዚህ የተናገሩትን በተግባር አለመፈጸም፣ በእግዚአብሔር ስም ሌላውን እያስተማሩ የራስን ሕይወት ካላስተማሩበት እግዚአብሔርን ማስደብ ይሆናል።

እውነተኛው መልካም እረኛ ግን እስመ ስምዐ ቃላቲሁ ምግባሩ ውእቱ እንዳለ መጽሐፍ ነገሩን በሥራው ለመግለጥ፤

፩ኛ. አነ ውእቱ ኅብስተ ሕይወት ዘወረደ እምሰማይ። ከሰማይ የወረደ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ። ከዚህ ኅብስት የበላም ለዘለዓለም ሕያው ሆኖ ይኖራል። እኔ የምሰጠው ይህ ኅብስት ሥጋዬ ነው። የዘለዓለም ሕይወት ሊሆን። ስለዚህ ራሱን በኅብስተ ሕይወት መስሎ ሥጋውን በኅብስት እንደሰጠን ያስረዳል። ዮሐ.፮፥፲፩።

፪ኛ. አነ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ባለው መሠረት ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ዕውር ሆኖ የተወለደውን ሰው በደረቅ ግንባር ዐይን ፈጥሮ ብርሃን ሆኖታል።

፫ኛ. አነ ውእቱ ትንሣኤ ወሕይወት ዘየአምን ብየ እመኒ ሞተ የሐየ ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ ያመነብኝም ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል ባለው መሠረት የአራት ቀን እሬሳ አልዓዛርን ትንሣኤና ሕይወት ሆኖ አስነስቶታል።

፬ኛ. አነ ውእቱ ፍኖተ ጽድቅ ወሕይወት። የሕይወትና የጽድቅ መንገድ እኔ ነኝ፤ ያለ እኔ ወደአብ የሚመጣ የለም። እኔን ተወላዲ ካላለ አብን ወላዲ የሚለው የለም። ዮሐ.፲፬፥፮። ስለዚህም ራሱን በሕይወትና በጽድቅ መንገድ መስሎ ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ እንካሳ ሆኖ ለተወለደው ሰው ቅዱስ ጴጥሮስ ብርና ወርቅ የለኝም በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሣና ተመላለስ ባለው ጊዜ እግሩና ቁርጭምጭሚቱ ፀና ስለዚህ የጽድቅና የሕይወት መንገድ እኔ ነኝ እንዳለው ከእናቱ ማኅፀን ሽባ ሆኖ ለተወለደው ሰው የጽድቅና የሕይወት መንገድ ሆነው። ግብ ሐ.፫፥፩–፲።

፭ኛ. አነ ውእቱ ሐረገወይን ዘጽድቅ ወአቡየ ተካሊሁ ብሎ በተናገረው መሠረት እራሱ በወይን ሐረግ መስሎ ደሙን በወይን ሰጥቶናል። ራሱንም በሕጠተ ስርናይ መስሎ ሥጋውን በስንዴ ሰጥቶናል። ዮሐ.፲፭።

፮ኛ. አነ ውእቱ አንቀጸ አባግዕ ዘበአማን እውነተኛ በር እኔ ነኝ በእኔ በኩል የገባ ማለት በእኔ ያመነ ሰው ከክሕደት ይድናል፤ ወደ ሃይማኖት ይገባል። ሥራ ለመሥራት ይወጣል። መሠማርያም ያገኛል። ማለት እሳቱን፣ ሥለቱን፣ መስቀሉን ያገኛል ወይንም እኔን አብነት ያደረገ ከፍዳ ወንጌልን ወይወጽእ ለማስተማር ጉባዔን ያገኛል። እንግዲህ ራሱን በመግቢያና በመውጫ መሠማርያ መስሎ የምዕመናን አዳኝ አሠሪ፣ አሠማሪ መሆኑን ያሳያል።

፯ኛ. አነ ውእቱ ኖላዊ ኄር ኢሳ.፵፥፲፩፤ ሕዝ.፴፬፥፳፫ ከዚህም ቸር ጠባቂ እኔ ነኝ። የበጐች ባለቤት የሆነ ለበጐቹ ነፍሱን አሳልፎ እንዲሰጥ፣ እርሱም ለምእመናን ቤዛ ራሱን ለሞት ለሕማም አሳልፎ ሰጥቷል።

ስለዚህ ማንኛውም የመልካም እረኛ ተከታይ የሆነ መንፈሳዊ አስተማሪ ያስተማረውን በተግባር መተርጐም አለበት። ምክንያቱም ተመርጦ መሾም ለማስተማር ነውና «የሹም ሰነፍ ባይለፈልፍ» እንዲሉ። ይህንም ላስተዋለው ለመረመረው ሰው ሹመትን ሺሕ ሞት አስመስሎ ያሳየዋል። መንፈሳዊ ሹመት መሾም እንደ ክርስቶስ መከራ ለመቀበል ምእመናንን ለማገልገል በሥራው ሁሉ ነቢያትን፣ ሐዋርያትን ለመምሰል ነውና።

እውቁ ባለቅኔ መልአከ ብርሃን የመልካሙን እረኛ ሕይወት በቅኔአዊ ምሥጢራቸው ገልጸውታል። ቅኔውም የሚከተለው ነው።

መወድስ ቅኔ፤

እምአፈ አርዌ በግዐ ለእመ አቀበ፤ ኖላዌ አባግዕ አዕላፍ ምንት ኄርውናሁ።

ወምንት ውእቱ ለዘይትአቀብ ረባሁ።

እምአፈ አርዌ በግዐ ድኅረ አቀበ ውእቱ እስመ ይበልዖ ለአርዌ ከማሁ።

ወለእመዝንቱ አይበልዖ እስመ ይሰይጦ በወርቅ ለዘይበልዕ ኪያሁ።

ትርጓሜ

የአዕላፍ በጐች እረኛ በጉን ከአውሬ አፍ ቢጠብቅ ደግነቱ ቸርነቱ ምንድን ነው? ለሚጠብቀውስ በግ ጥቅሙ ምንድን ነው? በጐቹን ከአውሬ አፍ ከጠበቀ በኋላ እንደ አውሬ እሱ ይበላዋልና። እሱ ባይበላውም በጉን ለሚበላ ሰው በወርቅ ይሸጠዋልና ጥቅሙ ምንድን ነው?

ለዓለም

ረባሕሰ ወበቍዔት ለኖላዊነ ትጋሁ

በበትረ መስቀሉ ድኅረ አቀበ እምአፈ አርዌ አባግዒሁ።

አምጣነ ደሞ ያስቲ እንዘ ያበልዕ ሥጋሁ።

ወኢያወጽኦ መንገለ አፍአ ለዘመጽአ መንገሌሁ።

ትርጓሜ

የመልካሙ እረኛ ትጋትና አጠባበቅ ግን ጥቅም አለው። በመስቀሉ በትር በጐቹን ከተጠበቀ በኋላ ሥጋውን እያበላ ደሙን ያጠጣልና። ወደሱ የመጣውንም ወደ ውጭ አያወጣውምና ሲሉ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ለሰዎች ያደረገውን ቸርነት፣ ደግነት ሁሉ ገልጿል። ✣



www.ethiopianorthodox.org

# እኔም ወጣት ነበርኩ



**እ**ቶ ዓለመ ሥላሴ ጐላ የታላቁ የአለቃ ጐላ መታፈሪያ ልጅ ናቸው። በዛው ላይ ከታወቁት ሊቅ ከየኔታ ወልደ ሥላሴና ከዝነኛው ባለቅኔ አለቃ ለማ የሐዲሳትና የቅኔ ዕውቀ ታቸውን አበልጽገዋል። በአጭሩ አቶ ዓለመ ሥላሴ ጐላ በቅኔ ባሕር ተወል ደው በቅኔ ባሕር እየዋኙ ነው ያደጉት ማለት ይቻላል።

አቶ ዓለመሥላሴ የ፹፮ ዓመት የእድሜ ባለጸጋ ናቸው። እንደዛም ሆነው መኪና ያሽከረክራሉ ያለመነ ጽር ያነባሉ። ከኢጣሊያ ወረራ በኋላ የትምህርት ሚኒስቴርን «ሀ» ብለው ካቋቋሙትና በአዲስ መልክ አደራ ጅተው አሁን ላለበት ደረጃ ካደረሱት ጥቂት ሰዎች አንዱ የሆኑት አቶ ዓለመ ሥላሴ ከ፲፱፻፴፬ ዓ.ም ጀምሮ ጡረታ እስከወጡበት ፲፱፻፷፰ ድረስ ከጸሐፊነት እስከ ዋና ዲሬክተርነት ባሉት የተለያዩ የሥልጣን እርከኖች ሠርተዋል።

በቀድሞው የተፈሪ መኮንን ት/ቤት ገብተው ዘመናዊ ትምህር ታቸውን ከመከታተላቸው በፊት ቅኔ፣ ሐዲሳትን ከብሉይ አራቱ ክፍለ ነገሥታትን ውዳሴ ማርያምንና ዜማን በሚገባ አጠናቀዋል። ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ባላነሰ እንዳሻቸው አቀላጥ ፈው ከሚያዙት ግዕዝ ሌላ ኢጣሊ ያንኛ፣ ሶማሊኛና ፈረንሳይኛ ቋንቋ ዎችን ይችላሉ።

የዛሬው የ«እኔም ወጣት ነበርኩ» አምድ እንግዳችን አቶ ዓለመ ሥላሴ ጐላ ሰፊ ዕውቀት፣ ተዝቆ የማያልቅ የሥራ ተመክሮ ያላቸው አዛውንት ናቸው። እንደዛም ሆና «ቁጥብነት»

## ዓለመ ሥላሴ ጐላ

### ባለቅኔው የትምህርት ዓምድ

ካሕሳይ ገ/እግዚአብሔር

ያሸንፋቸዋል። በቀጠሮየ መሠረት መቅረጸ ድምጼንና መቅረጸ ምስሌን ይዤ ቤታቸው ስደርስ በታላቅ ትህት ናና አክብሮት ከተቀበሉኝ በኋላ ያቀረ ቡልኝ የመጀመሪያ ጥያቄ «ስለ ሕይወት ታሪኬ ብዙ አይጠይቁኝ የሕይወት ታሪኬ እንዲጻፍ አልፈ ልግም፣ ይህን ሠራሁ ይህን አደረግሁ ማለትን አልወድም» ነበር ያሉኝ።

ቃለመጠይቁን ጨርሼ፣ የመጣሁ በትን ጉዳይ ፈጽሜ፣ በሥነ ጥበብ ውጤቶች (በሥዕሎች ፎቶግራፎችና ልዩ ልዩ የእደ ጥበባት ሥራዎች) ያሸበረቀችውን ሳሎናቸውን ለቅቄ ልወጣ ስል ወደ ቤት ስገባ የነገሩኝን ደግመው አስታወሱኝ። በአደራ መልክ። «...እኔ በተፈጥሮየ ልታይ ልታይ ማለትን አልፈልግም ይህንን ሲጽፉ በተቻለዎት መጠን ቀነስ አድርገው ይጻፉት...አደራዎትን» ብለው አሰናበቱኝ። አባባላቸው የሊቃውንት አበው አባባል በመሆኑ በጣም ደስ አለኝ። እኔም ትህትና



የተላበሰውን የአደራቸው ቃል ለማክበር ስል ካካፈሉኝ ቁና ሙሉ ቁም ነገር አንዷን ጭልፋ ጨልፌ ለማቅረብ ወሰንኩ፤ መልካም ንባብ።

**ፈ**ለገ ጥበብ – የትና መቼ ተወለዱ?

**እ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – በሸዋ ጠቅላይ ግዛት ሃራምባ ቅዱስ ሚካኤል በተለይ በለስ ተብላ በምትጠራው ሥፍራ ጥር ፯ ቀን ፲፱፻፮ ዓ.ም ተወለድኩ። ደብሩ ጥንታዊ ነው። አብዩና ስብስቴ የተቀበሩበት ነው፤ የተቋቋመው በ፲፯፻፰ ዓ.ም ነው።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ወደራስዎ እንመለስና ስለ ልጅነት ጊዜዎ ትንሽ ቢያወጉኝ?

**እ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – እዛ ከተወ ለድኩበት ሃራምባ ነው ያደግሁት፣ የተማርኩትም፣ ቅኔም የተቀኘሁት እዛው ነው። መጽሐፍ ለመማር ብቻ ነው አንኮበር የሄድኩት። እዛም ከሐዲስ ተክሌ ሐዲሳትን አነበብኩ ከኔታ ወልደ ሥላሴም ሐዲሳትን፣ ከብሉያትም አራቱ ክፍለ ነገሥት አነበብኩ፤ ከዛም አዲስ አለም ከየኔታ ቴዎድሮስ ውዳሴ ማርያም ዜማ ተማ ርኩ። ሐረር ድረስ በመሄድ ከታወቁ አለቃ ለማ ዘንድ ለሁለት ዓመታት ሐዲሳትን አንብቤአለሁ።

**ፈ**ለገ ጥበብ – አባትዎ የታወቁ የቅኔ ሊቅ እንደ ነበሩ ይታወቃል፤ ከሳቸው ዘንድ ቅኔ አልተማሩም ማለት ነው?

**እ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – አልተማርኩም፣ ሥራ ነበራቸው አለቃ ናቸው፣ ወደ አዲስ አበባ ይመጣሉ፤ በዛው ላይ አዲስ ዓለም ትክለኛ ናቸው ቁጭ አይሉም፣ አንዳንዴ ታድያ አባቴ ፊት ስቀኝ «ቃናዋ ደስ ትላለች፣ ትጣፍጣለች እንጂ ቀላል ናት» ይሉኝ ነበር።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በዚህ ዓይነት የቆሎ ተማሪ ሆነው አያውቁም ማለት ነው?

**እ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – በጭራሽ አግኝቶኝም አያውቅ፣ አዲስ ዓለምም ቢሆን የአባቴም የእያቴም ቤት ስለ ነበር እዛ ቁጭ ብየ ነው የተማርኩት።

**ፈ**ለገ ጥበብ .– ዘመናዊ ትምህርት እስከ ስንተኛ ተምረዋል?

**እ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – እስከ ሦስተኛ እንደዚህ ነው የተማርኩት፣ በኋላ አባቴ ካቶሊክ ትሆናለህ ብለው አስወጡኝና ሐረር ሄድኩኝ በዛን ጊዜ ትያትርም እሠራ ነበር በዚህም ሽልማት አግኝቼአለሁ፤ ዘፈንም ግጥምም እችል ነበር።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ከዛ በኋላ ትምህርትዎን አልቀጠሉም?

**እ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – ፈልጌ ነበር ነገር ግን ኢጣሊያን ሀገራችንን ወሮ እንደ ገባ አርባ የምንሆን ተማሪዎች ከት/ቤት አፍሶ ወደ ሞቃድሾ ወሰደን፤ እዛ ለሦስት ዓመት ተኩል ያህል በግዞት ተቀመጥኩኝ።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በሞቃዲሾ ስላሳለፉት የግዞት ሕይወት ሰፋ አድርገው ቢነግሩኝ?

**እ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – እሥረኞች አልነበርንም፤ የፖለቲካ ግዞተኞች ነን፤ ኮንፊናቲ ፖለቲቼ ይባላል፤ ቀን ቀን ለ፲፪ ሰዓት ነፃ ነን፤ የትም መሄድ እንችላለን ሥራ መሥራትም ይቻላል። ማታ ፲፪ ሰዓት ላይ ግን መገኘት ግድ ነው። ምግቡም የሚበቃ ነው፤ ሕክምናም በመጠኑ አለ። ልብስ ግን አይሰጠንም፣ ከቤተሰብ ገንዘብ ይላክልን ነበር ለእኔም አባቴ ይልኩልኝ ነበር። ከመካከላችን የተፈረደባቸው እስረኞችም ነበሩ። የአሰቦትና ደብረ ሊባኖስ ገዳማት መነኮሳትም እንዳሉ ታፍሰው ተወስደው ነበር። ለሞቱት ፍትሐት ያደርጉ ነበር። ያለ ማቋረጥ ምሕላና ጸሎት ያደርጉ ነበር።

**ፈ**ለገ ጥበብ – በመጨረሻ እንዴት ወደ ሀገርዎ ተመለሱ?

**እ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – የሁለተኛ ዓለም ጦርነት ሲጀመር አንድ ኮሎኔል እስረኞችን ሰበሰበንና (ከሦስት ሺህ እንበልጣለን) «አሁን የኢጣሊያ መንግሥት ከባድ ሥራ አለበት እናንተ ወደ ሀገራችሁ ትመለሳላችሁ ጠባያችሁ ጥሩ እንደሆነ አውቃለሁ፣ ሀገራችሁ ስትገቡ እንደ አሁኑ መታሰር የለም፣ ጠባያችሁ ካላማረ ግን ትመታላችሁ» አለንና ተራ በተራ ላከን። እዚህ መጣን። እዚህም የጣልያን መንግሥት ነው ያለው አፊቾ ፖለቲኮ የሚባል አለ፣ ማታ ነበር የደረስነው፣ በማግስቱ ሄደን ነፃ ናችው የሚል ወረቀት ተሰጠን። መነኮሳቱ ግን ከኛ ቀደም ብለው ነበር የተመለሱት።

በኋላ እኔ፣ አቶ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ ደነቀ/ሸሽናፊ የሚባል ሌላም ጓደኛ ነበረን ሀገራችን እንገባለን ብለን ስንብት (ፈቃድ) ጠየቅን። የለም እዚሁ ሥራ እንሰጣችኋለን አሉንና እኔን ከፖለቲካው ምክትል ዲሬክተሩ ጋር (እሱ በመጠኑ ግዕዝ ያውቅ ስለነበር እኔን በመምረጡ) ተክለፃድቅን አመያ (ወሊሶ አካባቢ) ሰደዱት፤ ደነቀን ደግሞ ፍቼ በመውሰድ ሦስታችንንም ለያዩን።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ከነፃነት በኋላስ?

**እ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – ከነፃነት በኋላ ለተወሰነ ጊዜ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ሠርቻለሁ ያኔ ማስታወቂያ ሚኒስትሩ በእንግሊዞች ነበር የሚመራው።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ትምህርት ሚኒስቴርን ካቋቋሙት አንዱ መሆንዎን ሰምቻለሁ ሁኔታው እንዴት ነበር?

**እ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – አየህ ትምህርት ሚኒስቴርን እኮ አምስት ሆነን ነው ያቆየነው፤ እስከ ምሽቱ አምስት ሰዓት እንሠራ ነበር። በአንፃሩ የሰዓት እላፊው አንድ ሰዓት ነበር፣ ምኒስትሩ ነበሩ ማታ ማታ በየቤታችን የሚያደርሱን፣ ያኔ እኔ ጸሐፊ ነበርኩኝ። ሚኒስትራችን መኮንን ደስታ ይባላሉ በኋላ ደጃዝማች ተባሉ። ታድያ የኔ የአስተማሪ እጥረት ስለ ነበር ራሳቸው ጭምር ፕሮግራም ይዘው ተፈሪ መኮንን ት/ቤት ያስተምሩ ነበር። የትምህርት ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተሩ አቶ ሰረቀም ዳግማዊ ምኒሊክ ያስተምሩ ነበር። ሁላችንም እንደ አንድ ቤተሰብ ነበር የምንተያየው፤ ልንገርዎት፤ ትምህርት ሚኒስቴርን መጀመሪያ ስናቋቁም ከየቤታችን ወንበርና ጠረጴዛ በመውሰድ (ይዘን በመሄድ) ነው። ይህች ጠረጴዛ (ወደ ጠረጴዛዋ እያመለከቱ) ከኔ ጋር ትምህርት ሚኒስቴር ነበረች፤ ለመታሰቢያ ነው ያስቀመጥኩዋት።

**ፈ**ለገ ጥበብ – ለመሆኑ በዚያን ጊዜ አዲስ አበባ ውስጥ ስንት ት/ቤቶች ነበሩ?

**እ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – ምኒልክ ያው የድሮ ነው፤ ተፈሪ መኮንን አለ፤ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ (የአሁኑ ኮከበ



www.ethiopianorthodox.org

ጽባሕ) ነበር፤ መድኃኔ ዓለም እንደዚህ እንደዚህ አሉ ብቻ በጣም ጥቂት ናቸው፤ እቴጌ መነንም ነበር።

**ፊ**ለገ ጥበብ – በትምህርት ሚኒስቴር ለምን ያህል ጊዜ አገለገሉ?

**አ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – ከ፲፱፻፴፬ ዓ.ም ጀምሮ እስከ ደርግ ጊዜ ነበርኩኝ፤ በጡረታ የወጣሁት በ፰ ዓመቴ ነው። እንዲያውም በጊዜው የነበረው ሚኒስትር ዶክተር ኃይለ ገብርኤል ዳኘ ተማሪ ሆኖ ያውቀኝ ስለነበር እባክዎን ይቆዩልኝ ብሎኝ ነበር፤ እኔ ግን ይቅርታ አድርግልኝ ብዩ ነው የወጣሁት።

**ፊ**ለገ ጥበብ – ጡረታ ሲወጡ በምን ኃላፊነት ነበሩ?

**አ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – ዋና ዳሬክተር ነበርኩ፤ ብዙውን ጊዜየን ያሳለፍኩት በዋና ጸሐፊነት ነው። የምኒስትሩ ልዩ ጸሐፊም ሁኜ ሠርቻለሁ።

**ፊ**ለገ ጥበብ – በዚህ ዓይነት ያን የመሰለ የቅኔ ችሎታዎና ዕውቀትዎ ሳይጠቀሙበት ነው ያለፉት ማለት ነው?

**አ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – (ሳቅ...) ከዛ በፊት ብዙ ጊዜ ተጠቅሜበታለሁ። ኢጣሊያን ሀገራችንን ክለቀቀ በኋላ... ኧረ አሁንም እቀኛለሁ ቅድስት ማርያም፤ ቅድስት ሥላሴ ስሄድ የሚያውቁኝ ሲጋብዙኝ እቀኛለሁ፤ ዛሬ ብቻ የሚያውቁኝ አለቁ... (ፊት ቅጭም) ደግሞ ቅኔ ባደጉና እድሜ በጨመሩ ቁጥር ጹሱም እያደገ ይሄዳል።

**ፊ**ለገ ጥበብ – የቅኔ ነገር ከተነሳ ለመሆኑ ንጉሡና ሌሎች ባለሥልጣናት ፊት የመቀኘት ዕድል አጋጥሞዎት ያውቃል?

**አ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – አዎን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በ፲፱፻፳፫ ዓ.ም ነው የነገሡት። በነገሡ በዓመታቸው የመጀመሪያውን የዘውድ በዓላቸውን ሲያከብሩ ለኔ ተሰጥቶኝ እኔ ነበርኩ የተቀኘሁት። በዛን ጊዜ ቅኔ መቀኘት ከመጠን በላይ ነበር ደስ የሚለኝ።

**ፊ**ለገ ጥበብ – ቅኔ በመቀኘትዎ ያገኙት ሽልማትና የማይረሱት አጋጣሚ ይኖራል? በአኳያው ባለሥልጣኖችን ወይም ሌላውን በቅኔ ‹ጐሸም› አድርገው የደረሰብዎት ቅጣት (ተግሳጽ) ካለ ቢነግሩኝ?

**አ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – (ሳቅ...) አንድ ጊዜ ሐረርጌ ሳለሁ ጊዜ ያለ ጊዜ (ያለ ሰዓቱ) ተደወለ። አስተማሪዩ አለቃ ለማ ይባላሉ፤ እሳቸውን ተከትየ ሄድኩ፤ ብንጠብቅ ብንጠብቅ ሰው የማይመጣ ሆነ። በኋላ አንድ ደብተራ የማነ የሚባል መጣ። ምራ አሉት፤ ተራየ ተወጥቻለሁ ብሎ እጅ ነስቶ ቁጭ አለ። ራሳቸው ተነሱና መሩ፤ እኔን ተመራኝ አሉኝና ተመራሁ። በኋላ ቀስ በቀስ ሰው መጣ ፍትሐሊተ የሚባል ቅኔ አለ፤ ከዛ ተደረሰ። ሲደርስ ያንንም ሲቀኙት ያንንም ሲሉት በመሐሉ ጥቅልል አሉና ተቆጥተው ተቀመጡ። «ዛሬ አዳሬ ጢቆ መወድስ ቅኔ የሚል ጠፍቶ ቁጭ ብለው አነጉት ይባል» ብለው ቁጭ አሉ።

በኋላ አጋፋሪው አጋፋሪ አምሳሉ ይባላሉ መጡና እኔን «እባክህ ሰው ሁሉ ከሥራው ደክሞታልና አንተ ተቀኝ» አሉኝ። እኔም እሺ ተመሪ አምጡና አልኩዋቸው። አመጡ፤ ተቀኘሁ። ጠዋት ሰው ጸጥ ሲል (ቅዳሴ ሲገቡ) አጋፋሪውን «አም ሳሉ» ብለው ተጣሩና «ይኸ ልጅ እኮ ዛሬ አገር አውኋል ዕቃ ቤት ውሰደው» አሉ፤ እንድሸለም ነው። ያን ጊዜ የነበረኝ ደስታ እንዲህ አይም ሰልዎት። ደግሞ ያን ዕለት ዜናው በሁሉም ደብር ተሰማ፤ ዛሬ ዓለመ ሥላሴ ዘርፎ ተቀኘ እየተባለ ተወራ።

**ፊ**ለገ ጥበብ – የተሸለሙት ምን ነበር?

**አ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – አጋፋሪው ይዘውኝ ሄዱና ፲፭ ጥሬ ብር (ማርትሬዛ ብር) ሰጡኝ። እኔም በጣም ደስ ብሎኝ እባክዎ ሌላም ቀን እንደዚህ ላድረግ አልኩዋቸው። (ሳቅ...)። የሽልማት ነገር ከተነሳ ሌላም ልንገርዎ፤ ለነገሩ ብዙ ጊዜ ነው የተሸለምኩት፤ የአዲስ ዓለም ንብረእድ ነበሩ። ንብረ እድ አድማሱ የሚባሉ፤ ለሳቸው አሰረ ንጉሥ ተቀኝቼ ሰጥቻቸው ሰላሳ ጥሬ ብር ሸልመውኛል። በቅኔየ በጣም ተደንቀው ነበር። ከዚህ ውጭ በቅኔ ምክንያት ከሽልማት በስተቀር የደረሰብኝ ቅጣት የለም።

**ፊ**ለገ ጥበብ – አሁን ደግሞ ወደ ትምህርት ሚኒስቴር ልመልስዎ፤ በረዥም ጊዜ የአገልግሎት ዘመንዎ አይረሳኝም የሚሉት የሚያስደስትዎም ሆነ የሚያሳዝን አጋጣሚ ካለዎት ቢያጫውቱኝ?

**አ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – አንድ ነገር ልንገርዎት፤ በትምህርት ሚኒስቴር በነበርኩባቸው ዓመታት አንድ ቀንም ከፍቶኝ፤ ቅር ብሎኝ አያውቅም ትዝ አይለኝም። ምክንያቱም እኔ በተፈጥሮየ ከማንም ሰው ጋር በሰላም ነው የምኖረው። አንድ ቀን በአንድ ሰው ጉዳይ ሚኒስትሩ ዘንድ ተጠራሁና ሄድኩኝ። «አይ! ተወው አንተ ለምስክርነት አትሆንም» አሉኝ። እኔም «ምን አጠፋሁ» ብላቸው «ባንተ ዘንድ ሰው ሁሉ እኩል ነው ሰውን አሳልፈህ አትሰጥም» አሉኝ፤ እውነታቸው ነበሩ። አንድ ሰው ከመሥሪያ ቤቱ ተጣልቶ ሲመጣ ወይም ሲሄድ ሌሎች ሲፈሩት እኔ ግን ተከትዩ አባብየ አረጋግቸ ምንብየ ነው የምሰደው። ደግሞ በቢሮየ ብቻ ሁኜ ማዘዝ ሳይሆን በየቢሮው እየሄድኩኝ ችግራችሁ ምንድነው? ምን ብናደርግ ይሻላል? እያልኩ እጠይቃቸዋለሁ። ችግር ካለ አብረን ተመካክረን እንፈታዋለን በቃ...እንደዚህ ነበር ሥራዩን የምሠራው።

**ፊ**ለገ ጥበብ – በረዥም የአገልግሎት ዘመንዎ በርካታ ሚኒስትሮችን አይተዋል (ከሁሉም አብረው ሠርተዋል) ከነዚህ መካከል በሥራው፤ በማስተባበር ችሎታው ይበልጥ የሚያደንቁት ማንን ነው? ምክንያትዎንም አብረው ቢገልጹልኝ?

**አ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – እንግዲህ እውነቱን ልንገርዎት አይደል? ትምህርት ሚኒስቴርን ያቋቋሙት መኮንን ደስታ ናቸው። ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፤ ተግባረ እድ ያቋቋሙት መኮንን ደስታ ናቸው። ያኔ ት/ቤት ባለመኖሩ ጸሐፊ አልነበረም፤ ስለዚህ ንግድ ሥራ ትምህርት ቤት እስኪሠራ ዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ውስጥ ለሦስት ወር በንግድ ሥራ ሥልጠና የሚሰጥ ፕሮግራም ከፈቱ፤ መምህራን ማሠልጠኛ ባለመኖሩ ከፍተኛ የመምህራን እጥረት ነበር። ይህንን ለጊዜው (ማሠልጠኛ እስከሚሠራ) የሦስት ወር ሥልጠና እዛው ዳግማዊ ሚኒልክ ትምህርት ቤት ውስጥ አቋቋሙ። ቀስ በቀስ ሥልጠናው ወደ መንፈቅ ከፍ አለ። ገሚሱ ሲሰለጥን ገሚሱ ያስተምራል። ብቻ ከዩኒቨርስቲ በስተቀር ሁሉም እሳቸው ያቋቋሙት ጀምረውት የሄዱት ነው። ዩኒቨርስቲንም ያልከፈቱት በወቅቱ እዛ ደረጃ የደረሰ ተማሪ ስላልነበረ ነው።

ደጃዝማች መኮንን ምሁር ብቻ ሳይሆኑ ቆራጥም ነበሩ። አንድ ነገር አይሆንም ከተባሉ ለንጉሡ ሥራውን እተወዋለሁ ብለው ነበር የሚጽፉት። ከአቶ መኮንን በኋላ ሥራው ሌላ ሰው አይችለውም በማለት የትምህርት ሚኒስትርነቱን ራሳቸው ንጉሡ ደርበው ይዘውት ነበር። አቶ መኮንን ደስታ በስደት ጊዜ ካይሮ ውስጥ ያስትምሩ ነበር። ከጃንሆይ ጋር አብረው ነው የተመለሱት። ሲመጡ ታዲያ እሳቸው የጐጃም ባላባት ይባላሉ። «መኮንን ደስታ መስፍን ጊዮን ፀያሔ ፍኖቱ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ» እያሉ ወረቀት እየበተኑ ነው የመጡት። አንድ ተጨማሪ ነገር ልንገርዎ ከስደት ሲመለሱ እንግሊዛዊው ጄኔራል ዊንጌት አብሮአቸው ነው የመጣው። ታድያ የኢጣልያ አውሮፕላን ሲመጣ «አንተ ተደበቅ» ይላቸው ነበር «ለምን አንተስ? ሲሉት «እንግሊዝ የእኔ ዓይነት ብዙ ሰው አላት ኢትዮጵያ ግን ያንተ ዓይነት ሰው የላትም ይላቸው ነበር ይባላል። ይህንንም ያጫወቱኝ እሳቸው ናቸው።

ለመሆኑ አሁን መሠረተ ትምህርት የሚባለው «ምርፋቀ ትምህርት» በሚል ስም የጀመሩት መኮንን ደስታ እንደ ነበሩ ያውቃሉ? ምን ይህ ብቻ ምኞታቸው ትልቅ፤ ሕልማቸው ሩቅ ነበር። ምርፋቀ ትምህርትን ሲጀምሩ በተለይ ዘላኑን (ከብት አርቢውን) ኅብረተሰብ እየዞረ የሚያስተምር ልዩ የትምህርት ቡድን አዘጋጃለሁ ብለው ዕቅድ አውጥተው ነበር። ከቦረና፤ ከሶማሌ በአጠቃላይ ከመላ የኢትዮጵያ ጠረፍ አካባቢዎች የባላባት ልጆችን በማሰባሰብ በአዳሪነት ማስተማር የጀመሩት እሳቸው ናቸው። በአጠቃላይ የሥራ ሰው ነበሩ። ፐርሶኔል እገሌ ከሥራው ቀርቷል፤ አርፍዶ ይገባል፤ ይቀጣ ሲላቸው «እሱን ተወውና ከሁሉ በፊት የተሰጠውን ሥራ ሠርቷል አልሠራም?» ነበር የሚሉት። ሥራውን ከተወጣ ይሂድ ነበር የሚሉት ሰውን በሰዓት ተቆጣጥሮ ማሠራት አያምኑበትም ነበር።

**ፊ**ለገ ጥበብ – እርስዎስ ምን ዓይነት ሠራተኛ ነበር የሚወዱት?

**አ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – እኔም በሰዓቱ የሚገኝ፤ ሥራውን በሚገባ የሚያሸንፍ፤ እወዳለሁ።

**ፊ**ለገ ጥበብ – ከቅኔ መምህራን (ሊቃውንት) መካከልስ ማንን ያደንቃሉ? እርስዎን ካስተማርዎት መካከልም ሆነ በዝና ከሚያውቁዋቸው?

**አ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – በቅኔ አለቃ ለማን የሚያህል የለም። በትምህርት ሳይሆን እንደ እድልም ነው፤ ቅኔያቸው ከማንም ከምንም የሚበልጥ ነው። ለብቻ ነው! ደግሞ ሁሉንም ነው የሚያውቁት። መንግሥቱ ለማን ያውቁት ነበር? ከርሳቸው ዘንድ ሰማር እርሱ ልጅ ነበር።

**ፊ**ለገ ጥበብ – እንደ ትምህርት ባለሞያነትዎና የረዥም ጊዜ ልምድዎ የአሁኑና የበፊቱን ሥርዓት ትምህርት እንዴት ያዩታል?

**አ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – ይህንን መናገር አያስፈልግም!!

**ፊ**ለገ ጥበብ – ለወጣቱ ትውልድ የሚያስተላልፉት የአደራ መልእክት ይኖራል?

**አ**ቶ ዓለመ ሥላሴ – መቼ ይሰማሉ የአሁኖቹ? የዛሬው ልጅ እንደምን አደርክ ቢሉት ምን አገባህ የሚል ነው እኮ? በቅርቡ እዚህ አራት ኪሎ ያጋጠመኝን ልንገርዎ? አንድ ሽማግሌ ምርኩዝ ይዘው ይሄዳሉ፤ ጐብጠዋል፤ አንድ ልጅ በአጠገቡ ሲያልፉ ‹አባት እንዴት ጐበጡ?› አላቸው፤ እሳቸውም «ምን ያደርግ ልሃል አንተ አትደርስበትም» አሉት። አዩ ረገሙት ማለት ነው። እኛ ድሮ ሽማግሌዎች ሲመጡ ከተቀመጥንበት ተነስተን፤ እስኪሄዱ ድረስ ቆመን፤ አሳልፈን...እግዚአብሔር ይባርክህ፤ እደግ እንደዚህ ተብለን ነው ያደግነው።

**ፊ**ለገ ጥበብ – ታድያኮ ጥፋቱ የወጣቱ ብቻ ሳይሆን የወላጆችም ነው የሚሉም አሉ። ይህንን እንዴት ያዩታል?

www.ethiopianorthodox.org

**አ**ቶ ዓለመ ሥላሴ — ይህም አለ፤ እውነት ነው። እንዲያውም አንዳንድ ወላጆች ተመልሰው ልጆቻቸውን ይፈሯቸዋል። እኔ አያምኑኝም ልጁ እዚህ ዩኒቨርስቲ እያለ እንኳን እቀጣው እቆጣው ነበር። ልጁ ደግሞ ጠባየ መልካም በተማረበት ትምህርት ቤት ሁሉ የተመሰገነ ነበር። ስለዚህ እንዳሉት ካባቶችም ከወላጆችም ጥፋቱ አለ። የትዋልክ? የት ነበርክ? ብለው አይጠይቁም፤ እንዲያውም ለራሳቸው የማያደርጉትን ከአቅማቸው በላይ የሆነውን ነገር ተበድረው ሲያደርጉ ነው የሚታየው፤ የሚያስገርመውም ይህ ነው። ልጅ እኮ ልጅ ነው። መመራት ያለበት በእናትና በአባቱ፤ በቤተሰቦቹ በታላላቆቹ ነው። ስለዚህ በመልካም መንገድ ሊመራ ይገባዋል። እሱም ምክሩን መቀበል አለበት። ግን በታናሽነቱ ካላስተማሩት፤ ካልለመደ ኋላ ምክሩንም አይቀበልም።

**ፈ**ለገ ጥበብ — የግብረ ገብ ትምህርት መቅረት ለወጣቱ ትውልድ ጠባይ መበላሸት አስተዋጽኦ አለው የሚሉም ወገኖች አሉ የእርስዎስ አመለካከት እንዴት ነው?

**አ**ቶ ዓለመ ሥላሴ — እንዴ ዋናው ነው እንጂ! ዛሬ ሃይማኖት የት አለ? ማን ሥነ ምግባር ያስተምራል? ማን ይሰብካል? ወጣቱን ትውልድ እኮ ለምን እንደዚህ ታደርጋለህ? ይህ መጥፎ ነው ወደዚህ ሂድ የሚለው የለም።

**ፈ**ለገ ጥበብ — ሊመሆኑ የርስዎን ፈለግ የተከተለ ልጅ ኤለዎት?

**አ**ቶ ዓለመ ሥላሴ — ያለኝ ወንድ ልጅ አንድ ነው፤ እሱም ውጭ ሄዶ እዛ ነው ያለው። እየመጣ ይጠይቀኛል። ሁለቱ ሴቶች ናቸው አንዷ ውጭ ነው ያለችው አንዷ ደግሞ እዚህ እተባበሩት መንግሥታት አዳራሽ (ኢሲኤ) ነው የምትሠራው።

**ፈ**ለገ ጥበብ — ከቀሎ ተማሪነት ጋር የተያያዘ ባይሆንም ከተማሪ ጊዜ ትዝታዎ እንደዚሁም በሥራ ላይ ከገጠመዎት ገጠመኞች የሚነግሩኝ አስገራሚ አጋጣሚ ይኖራል?

**አ**ቶ ዓለመ ሥላሴ — አንድ የሚያስደንቅ ነገር ልንገርዎት፤ ሐረርጌ አለቃ ለማ ዘንድ ስንማር አንድ ተማሪ እፀፋርስ ጠጣ አሉኝና ሄድኩኝ። እሱ ይለፈልፋል በቃ እንዲህ ነው፤ እንዲህ ነህ እያለ፤ ብቅ ስል «ዓለመ ሥላሴ ዝም ብለህ እኮ ነው ሐዲሳትን የምትደክመው አንተ እኮ ጸሐፊ ሆነህ ነው የምትኖረው» አለኝ። አይገርምም? በወቅቱ እሱ አለኝ ብዬ መማሬን አልተውኩም ተመልሼ ስመጣ ግን እሱ እንዳለው ትምህርት ሚኒስትር ጸሐፊ ሆንኩኝ።

አንድ ጊዜ ደግሞ እንዲህ ሆነልዎ በጣም አዋቂ፤ ችሎታ ያለው ጸሐፊ ነበረኝ። ለጃንሆይ የሚሄደው ወረቀት እሱ ነው የሚጽፈው፤ ሲበዛ ባለሞያ ነው። ግን ይጠጣል፤ ሲጋራ ያጨሳል። አንድ ቀን (ፕሬዚዳንት ቲቶ የመጣ ጊዜ) የቲቶን የሕይወት ታሪክ ተጽፎ በአስቸኳይ ይምጣልኝ አሉ፤ ጃንሆይ። ጸሐፊው ቢፈለግ ቢፈለግ የለም። መኪናየን ያዝኩኝና ደጃች ውቤ ሰፈር ሄድኩኝ። ይገርምዎታል ቁጭ ብሎ ይጠጣል፤ በሥራ ሰዓት እኮ ነው «ምነው እባክህ ሥራውስ?» ስለው «ይልቅስ ለሲጋራ የሚሆን ገንዘብ ካለህ ስጠኝ» አለኝ። ለምኘ አመጣሁትና ጻፈው። ከዛ ሚኒስትሩ ጽሑፉን ሲያዩ ይህ ጸሐፊ ሳይሆን ሰዓሊ ነው ለመሆኑ ደመወዙ ስንት ነው አሉኝ። ደመወዙን ሊጨምሩለት እኮ ነው? ወደቤቱ የሚገባው ደመወዙ በተቀበለ በ15 ቀኑ ነበር። የሚገርመው ጡረታ እንደወጣ የ10ሺህ ብር ሎተሪ ደረሰው ብቻ ታሪኩ ብዙ ነው… አይበቃም?

### አቶ ዓለመ ሥላሴ በተለያዩ ጊዜያት ካበረከቷቸው ቅኔያት መካከል

#### መወድስ

ጠቢባን ጸረብት ወወቀርተ እብን፤ ከንቶ
ጻመው ለሐኒጸ ምኩራብ ወመርጡል፤
እምጣነ ጻማሆሙ ኮነ ለገጸ ሙስና ወሃጉል።
ባሕቱ ለወልድ ኢያጽአቆ
ሐኒጸ መቅደስ ዘአልቦ እምሳል፤
እንዘ ይሬስዮ ለእብነ ሐቅል
ለሐኒጸ መቅደስ ዘውስጥ ወእንተ እፍአ
ዘየአክል፤

#### ለዓለም

አንከሩኒ ሥነ ሕንጺሃ ለዘተፀውረት
ድንግል፤
እለ ያስተናድፉ መሠረተ ሐዋርያት ቅድም
እስራኤል፤
እስመ በሕንፃ የዐቢ መቅደስ እሙ ለቃል፤
እምሕንፃ ዘተሐንፀ በእርብዓ ወበስምንቱ
ቤተ በዓል።

#### ክብር ይእቲ

ተኩርዖተ ርእሱ ለወልድ ሶበ ርእየ
ወጥብጣቤሁ ዘባኑ፤
ኮከበ ራግ ሕዙን ጸበለ መሬት ተከድነ።
ወአዋልደ ወርህ ሳሌም እመ: ተናጸረ ሥነ፤
ትቤ ፀሐይ ኢትርአያኒ፤ እምጣነ ጸላም አነ፤

#### ዕጣነ ሞገር

ተከብቶ ኢትክል ሀገረ ሕማም መጥባሕት፤
መልዕልተ ጊዮርጊስ ደብር እንተ ተሃንጸት፤
እምጣነ እምሩሑቅ ትትራአይ እስከነ
እድማስ ሞት።
ቅድመኒ ተሐደሰት፤
በደመ ዘካርያስ ቅብዕ ወበደመ ጳውሎስ
ነገሥት
ሕፃናት እስከ አንከርዋ ዘከልኤ ዓመት።

#### አሰረ ንጉሥ

ኃይለሥላሴ እግዚእ እሠርገዋ በቅድመ
ብዙኃን ነገሥት፤
ለገነተ ጽጌ ምድርነ ምልዕተ ፍሬ ማኅሌት፤
በሥነ ጽጌያት ጳዖሳት።
ወይእቲኮነት ርእሰ ማዕዘንት፤
ዘኅዕሌሃ የሐቅ ማዕተት።

# ትምህርተ ሃይማኖት



የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በቀደምትነት ከታወቁ የዓለም አቢያተ ክርስቲያናት አንዷ እንደሆነች ግልጽ ነው።

ቤተክርስቲያኒቱ የተቋቋመችበትን ዘመን ከእውነተኛ የታሪክ ገጽታ ስናስተያየው፡ ምንም እንኳን በነገሥታቱ አኵስም በአብርሃ ወአጽብሐ ሐዋርያዊ ተልዕኮዋን ያስፋፋች መሆኑ ቢታወቅም፡ የተመሠረተችው ግን በ፴፬ ዓ.ም ነው። የሐ.ሥ.፰፡፳፮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በጃንደረባው ሐዋርያነት በአኵስም ከተማ ከተቋቋመች ጀምሮ እስከ አብርሃ ወአጽብሐ ዘመን ድረስ ግልጽ የሆነ መለያ አላስቀመጠችም ነበር።

በአቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ዘመነ ጵጵስና እና በአብርሐ ወአጽብሃ ዘመነ መንግሥት ግን ሕዝባውያኑና ካህናቱ፡ ሊቃውንቱና መኳንንቱ፡ የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖችና ነገሥታቱ የሚያምኑት እምነት «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት» ተብሎ እንዲጠራ ሆነ።

ይህ ስያሜ በመላ ኢትዮጵያ ለሚኖሩ ክርስቲያኖች የእምነታቸው መለያና የክርስትናቸው መጠሪያ ሆኖ እስከ አሁን ድረስም ያገለግላል።

«ኦርቶዶክስ» የሚለው ቃል የጽርዕ ቃል ሲሆን ትርጉሙ የቀና ርቱዕ እምነት የሚል ትርጉም ይኑረው እንጂ፡ ቤተ ክርስቲያኒቱ ከሌሎች የተለየችበትን አቋም ለይቶ አያሳይም።

«ተዋሕዶ» የሚለው ቃል ግን ቤተ ክርስቲያኒቱ የተመሠረተችበትን እምነት ወይም ሃይማኖት ስምን ከምግባር አስተባብሮ ይዞ በመገኘቱ ቤተ ክርስቲያኒቱ መለያ አድርጋ ትጠራበት አለች።

ይህ ስያሜ እንደ አጋጣሚ የተገኘ ነገር አልነበረም። ነገር ግን ንጽሕናን

## ትምህርተ ተዋሕዶ

ከመም.ዕንቁባሕርይ ተከስተ

ከቅድስና፡ ሊቅነትን ከመንፈሳዊነት ጋር አሚልተው በያዙ ሙሉ ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር በሰጡ፡ በእምነትና በትምህርት በበሰሉ፡ በሀገር ሊቃውንት ድካምና ጥረት የተገኘ ነው እንጂ።

### ትምህርተ ተዋሕዶ
### (አንቀጸ ተዋሕዶ)

የተዋሕዶ ትምህርት «አንቀጸ ተዋሕዶ» ይባላል። ምሥጢረ ተዋሕዶ ሊገኝ የቻለው «ተወሐደ» አንድ ሆነ ካለው አንቀጽ የወጣ፡ የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶን የሚያስረዳ ስለሆነ ነው። (ሃይማኖተ አበው ፊልክስዮስ ሰማዕት ክፍል ፪) ተመልከት።

ይህም የልደታቱን መንኝ ሲያዩ ጥቅስ «ከመ ነአምን ዘአልቦቱ እም በሰማያት ወአብ በዲበ ምድር፡ በሰማይ ያለእናት ከአብ መወለዱን፡ በምድርም ያለ አባት ከድንግል ማርያም መወለዱን እናምናለን» ተብሎ መግለጫ የተሰጠበት ወይም ባሕርያተ ልደታትን በመገንዘብ «ነአምን ክልኤተ ልደታተ» ተብሎ እንዲታመንበት ያስቻለ፡ ምሥጢር መሆኑ ይታወሳል። ለዚህም ቅዱስ ባስልዮስ በሰፊው አብራርቶታል።

«ይደልወነ ንእመን ከመ ቦቱ ለወልደ እግዚአብሔር ክልኤቱ ልደታት ቀዳማዊ ልደቱ እም እግዚአብሔር አብ እምቅድመ ኵሉ መዋዕል፡ ወዳግማዊ ልደቱ እም እግዚእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም በደኃሪ መዋዕል።»

ለወልደ እግዚአብሔር ሁለት ልደታት እንዳሉት እናምን ዘንድ ይገባናል፡ አንዱ ከዘመን ሁሉ አስቀድሞ ከእግዚአብሔር አብ የተወለደው ልደት ነው። ሁለተኛውም ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በኋላ ዘመን የተወለደው ልደት ነው። (መዝ. ፪፥፯።፩፻፲(፩፻፱) ቁጥር ፫። ማቴ. ፲፱፥፳፰። ዮሐ.፲፮፥፳፮ እና ፳፰። ገላ.፬፥፬። ሃይማኖተ አበው ምዕ.፴፬ ቁጥር ፮ ክፍል ፳ ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ምዕ.፴፰፥ ክፍል ፪ ቁጥር ፲፯፥፲፰።)

የተዋሕዶ ይዘታ ከሁለት ባሕርያተ ልደታት ምንጭነት፤ አንዱን የአማኑኤልን ህላዌ ቅውም አድርጎ ሲያስገነዝብ ጥቅስ ቁርሎስ «ኢትፍልጥ ሊተ እምድኅረ ትድምርት እስመ ዘፈለጠ እንተ ባሕቲቶ ብእሲ ወእንተ ባሕቲቶ አምላክ ቃለ ክልዔተ ይረስዮ ለአማኑኤል፤ ከተዋሕዶ በኋላ አትለይብኝ፡ ከተዋሕዶ በኋላ

www.ethiopianorthodox.org

ብቻውን ሰው፣ ብቻውን አምላክ ቃል የሚል ሰው ቢኖር፣ አማኑኤልን ሁለት ያደርገዋል።» ብሎአል።

ባስልዮስ ዘእንጸኪያም፣ «ኢይት ከፈል ኀበ ክልዔቱ ህላዌያት እም ድኅረ ተዋሕዶ እስመ ለምንታዌ አእተታ ተዋሕዶ፣ ወተዋሕዶኒ ያግኅሥ ኩነኔሁ ለምንታዊ እስመ ውእቱ ተዋሕዶ አካላዊ ዘኢትከፈል ከተዋሕዶ በኋላ ወደ ሁለት ባሕርይ አይከፈልም፣ ተዋሕዶ ሁለትነትን አስወግዶአልና፣ የሁለትነትንም ፍርድ አርቆአል። እርሱ የማይከፈል አካላዊ ተዋሕዶ ሆኖአል» ብሎአል። (ሃይማኖተ አበው ዘባስልዮስ ምዕ.፲፮ ቁጥር ፲፯ ክፍል ፩)

ቅዱስ አትናቴዎስም «አኮ ዘንብል እስመዘንቱ ወልድ ክልኤ ህላዌ ለአሐዱ ዘንሰግድ ወለካልኡ ዘኢንሰግድ አላ አሐዱ ህላዌ ውእቱ ዘእግዚአብሔር ቃል ዘተሰገወ። ንሰግድ ሎቱ ምስለ ሥጋሁ አሐተ ስግደተ።

ይህ ወልድ ለአንዱ የምንሰግ ድለት ለአንዱ የማንሰግድለት ሁለት ባሕርይ ነው፣ የምንል አይደለም፣ ሰው የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ባሕርይ አንድ ነው እንጂ፣ ከሥጋው ጋር አንዲት ስግደትን እንሰግ ድለታለን እንጂ ብሎአል። (ሃይማ ኖተ አበው ዘአትናቴዎስ ምዕ.፳፯ ቁጥር ፲፫ ክፍል ፲፫።)

ቅዱስ አቡሊድስም «ወኢንከ ፍሎ ለሰማያዊ እምነ ምድራዊ ወኢለ ምድራዊ እምሰማያዊ እስመ ክፍላትሰ ዐመፃ ውእቱ ወኢነህቦሙ ለእለ ይብሉ ክልኤ ህላዌ ምክንያተ ለፍ ልጠት» ሰማያዊ መለኮትን ከምድ ራዊ ሥጋ፣ ምድራዊ ሥጋንም ከሰማ ያዊ መለኮት አንለየውም፣ መከፈል ክሕደት ነውና፣ ሁለት አካል ሁለት ባሕርይ ለሚሉ ሰዎች ለመለየት ምክንያት አንሰጣ ቸውም።» (ሃይማኖተ አበው ዘአቡሊድስ ምዕ.፴፱ ቁጥር ፳።)

እኛ ግን መለየት፣ ሕፀት መቀላ ቀል ሳይኖርበት አንድ ሆነ እንላለን፣ ከተዋሕዶ በኋላም ወደ ሁለትነት አይከፈልም እንላለን (ዮሐ.፫፥፲፰። ፩ቆሮ.፰፥፮ ሃይማኖተ አበው ዘቴዎ ዶጦስ ምዕ.፶፫ ቁጥር ፴፩ ክፍል ፫።)

በምሥጢረ ሥጋዌ (በተዋሕዶ) ትምህርት ከትስብእትና ከተዋሕዶ በፊት ስለ ነበረው አቋም በአንቀጽ ተከፍሎ ሊነገር ሲገባ፣ ከትስብእትና ከተዋሕዶ ወዲህ ስላለው ምሥጢር ግን በአንቀጸ ተዋሕዶ መነገር እንዳለበት የኢትዮጵያ ሊቃውንት ሁሉም የሚስማሙበት ነው።

ስለዚህም ዮሐንስ አፈወርቅ «ወአሠረ ክልዔቱ ህላዌያት በበይና ቲሆሙ በተዋሕዶ «ሁለቱን እየራስ የሆኑትን ህላዊያት በተዋልዶ አንድ አደረገ» ይላል። (ሃ.አ.ገጽ.፪፲0፵፱) ክፍል ፳፪ ቁጥር ፳፪።

ሳዊሮስ ዘአንጾኪያም «ኢይት ክሐል ይፍልስ ሥጋ ዘይትዌለጥ ኀበ ዘኢትዌለጥ መበ ከመ ግብር ዘይከውን እምክልዔቱ ህላዌያት ሶበ የኀብሩ በበይናቲሆሙ ይከውኑ አሐደ እንዘ አሐዱ አሐዱ እምኔሆሙ እምኀላዌሁ እንዘ ቀዳሚ ክልዔቱ።

## ትርጉም

የሚለወጥ ሥጋ የማይለወጥ ባሕርይ ወደ መሆን ይለወጥ ዘንድ አይቻልም፤ ከሁለት ባሕርያት እንደሚገኝ ሥራ፤ ጥንቱን ሁለት ሲሆኑ አንዱም አንዱ ከባሕርዩ ሳይለወጥ እርስ በእርሳቸው በተዋሕዶ ጊዜ አንድ ይሆናሉ።» ብሏል።

ሃይ.አበው ገጽ ፫፻፸፰ ክፍል ፰ ቁጥር ፴

ተዐቅቦ ማለት — አለ መለወጥ፣ አለመቀላቀል፤ አለመጣፋት አለመደባለቅ፣ ነው ከትንሣኤሙ ታን እንደ ነፍስና በኋላ ሥጋ ተዋሕዶ ነው።

ቅዱስ አትናቴዎስም ስለ ምሥጢረ ተዋሕዶ በተናገረበት አንቀጽ እንደሚከተለው ይገልጻል።

«ወኪያሁ ለቢሶ ቃለ እግዚአብሔር ሥጋ ኮነ እንዘ ኢይትዌለጥ እምህላዌ መለኮቱ ወለውእቱኒ ሥጋ ዘለብሶ ኢትዌ ዕሩየ ምስሌሁ በአሐዱ ህላዌ እንዘ ኢይትዌለጥ እምህላዌ ሰብእናሁ።

የእግዚአብሔር ቃል ከባሕርየ መለኮቱ ሳይለወጥ እርሱን ተዋሕዶ ሰው ሆነ፣ የተዋሐደውን ያንን ሥጋም ከሰውነቱ ባሕርይ ሳይለወጥ አንድ አካል፤ አንድ ባሕርይ፣ በመሆን ከእርሱ ጋር አንድ አደረገው (ሃይማኖተ አበው ዘአትናቴዎስ ምዕ.፴ ቁጥር ፯።)

ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት ዘእግ ዚናዙም

«ወኢፈለስ ህላዌ መለኮቱ ኀበ ህላዌ ትስብእቱ ወኢህላዌ ትስብእቱ ኀበ ህላዌ መለኮቱ አላ በአሐዱ አካል ወለደቶ እግዚእትነ ማርያም ድንግል ወበአሐዱ ህላዌ ሰገዱ ሎቱ ሰብአ ሰገል።

## ትርጉም

የመለኮቱ ባሕርይ ወደ ሰውነቱ ባሕርይ አልተለወጠም የሰውነቱ ባሕርይም ወደ መለኮቱ ባሕርይ አልተለወጠም፤ ድንግል ማርያም አንድ አካል ሆኖ ወለደችው እንጂ፤ ሰብአ ሰገልም አንዱ ባሕርይ ሆኖ ሰገዱለት እንጂ (ማቴ.፩፥፲፰–፳፭ ምዕ.፪፥፩–፲፪። ሃይማኖተ አበው ዘጎርጎርዮስ ምዕ.፰ ቁጥር ፲፯ ክፍል ፩)

የኮነንና የኀደረን አብነት (ትርጉም)

«ቃል ሥጋ ኮነ፤ ቃል ሥጋ ሆነ» «ወኀደረ ላዕሌነ፡ በእኛም አደረ» በሚል በቅዱስ መጽሐፍ አባባል የተዋሕዶ ምሥጢር መመሥረቱ ይታወቃል። ዮሐ.፩፥፲፬። «ኮነና፡ ኀደረ» ሆነ፤ አደረ (እነዚህ ሁለቱ የተዋሕዶውን አንቀጽና የተአቅቦን ምሥጢር በመያዝ፤ እንደ አለቃና እንደ ጠበቃ ሆነው ይጠባበቃሉ። በ«ኮነ» የተነሱት መናፍቃን በ«ኀደረ»፤ በኀደረ «የተነሡት መና ፍቃን በ«ኮነ» ይረታሉ።» ኮነ፣ ኀደረ» እንደ አለቃና እንደ ጠበቃ ይጠባ በቃሉ እንጂ፤ አንዱ ከሁለተኛው ተነጥሎ! ተለይቶ! «ኮነ» ለብቻው፣ ኀደረም» ለብቻው፤ በመነጣጠል የተዋሕዶን ምሥጢር ጠንቅቆ ለመጠበቅ፤ አያስችሉም። ይህ የኢት ዮጵያ ሊቃውንት የብሂላዊ ትርጓሜ አብነታዊ አዋጅ ነው።

የእነዚህም ትንትና ለመርዳት የሚከተለውን ይመለከቷል።

ለምሳሌ ንስጥሮስ «ኮነን» «የኀደረን» ንባብ ይዞ ምሥጢሩን ሳይመረመር በአንድ ክርስቶስ ሁለት ህላዌያት አሉ» ብሎ በመተርጐም ውስጣዊ መለያየትን፤ መፈራረቅን (ቡዓዴንና ፍልጠትን) በምሥጢረ ተዋሕዶ አመጣ። ለዚህም «የኮነን» እውነተኛ ትርጉም ወይም ፍቺ የያዘ ከኀደረ ጋር የሚያገናኝ (የሚያስማማ) ተዐቅቦ እንዲኖር አስፈለገ እነሆም» ዘእንበለ ቡዓዴ፣ ዘእንበለ ፍልጠት፣ በኢተላፅቆ ያለ መለየት፣ ያለ መከፈል፤ ያለመነባበር (አነባብሮ) የሚሉ ቃላት የ«ኮነ»ን ምሥጢር ይዘው «ኀደረ» ያለውን አንቀጽ እንዲጠብቁ ተደርጐ የሥግው ቃል በተዋሕዶ ተጠናቀቀ።

አውጣኪ በአንዱ ሥግው ቃል (ክርስቶስ) ቱስሕተ (መደባለቅ) (ውላጤ የሰውነት መለወጥ) ሚጠት (መለዋወጥ) እንዳለበት፣ ሰውነቱ ወደ አምላክነቱ እንደ ተለወጠ ተናገረ።

አውጣኪ «ኀደረን» በመተው የ«ኮነን» ንፍቺ በተሳሳተ አተረጓጐም «ኮነን» ተለወጠ» በሚል ቃል ተርጉሞ ተሰናከለበት ( «እንደ እሱ ሐሳብ ወይም አተረጓጐም ቢሆን ኖሮ ምሥጢረ ተዋሕዶን ደመሰሰበት።

ለዚህም ጠንቃኛ ትርጉም መጠበቂያ (ልጓም) አስፈለገ። እነሆም «ዘእንበለ ቱስሕት ዘእንበለ ውላጤ፤ ዘእንበለ ሚጠት ያለመደበላለቅ፤ ያለመለወጥ ያለመለዋወጥ ያለመ መላለስ» የሚሉ ቃላት። የኀደረን ምሥጢር ይዘው የኮነን ፍቺ ወደሌላ እንዳይሄድ ይኸውም በመለወጥ እንዳይተረጐም ይጠብቁ ዘንድ ተደረገ።

ስለአንቀጸ ተአቅቦ መጻሕፍት ጠንቅቀው ያስረዳሉ። ለዚህም

አቡሊድስ እንደ ገለጸው «ወዓዲንብል አልቦቱ ቱሳሔ ወኢካልዕ ነገር ዘከመዝ ወኢይተልዎ ንባበ ቱሰሔ በእንተ ነገረ ተዋሕዶ ወልድ ወልደ እግዚአብሔር ተሰነአወ ወኮነ ሰብአ ወበእንተ ዝንቱሂ ነገር ኢይበው ቱሳሔ ውስቴቱ ዘከመ የእምኔ አልከቱ ወኢተወለጠ ህላዌ ቃል ኀበ ህላዌ ትስብእት ወህላዌ ትስብእት ኀበ ህላዌ ቃል ጸዕሙ ይሄልው ክልኤቱ ህላዌያት በበዓላቲሆሙ እንበለ ውላጤ።

ዳግመኛም መቀላቀል ይህንንም የመሰለ ሌላ ነገር የለበትም እንላለን ተዋሕዶው እውነተኛ ስለሆነ ተቀላቀለ ማለት አይስማማውምና። የእግዚአብሔር ልጅ ወልድ ዋሕድ ነፍስን ሥጋን ነስቶ ሰው ሆነ ባልን ጊዜም ስለዚህም ነገር ቢሆን እነዚያ እንደሚያምኑ መቀላቀል የለበትም፣ የቃል ባሕርይ የሥጋን ባሕርይ ወደመሆን፣ የሥጋ ባሕርይም የቃልን ባሕርይ ወደመሆን አልተለወጠም፣ ሁለቱ ባሕርያት ያለ መለዋወጥ፣ ባለመቀላቀል ጸንተው ይኖራሉ እንጂ (ዮሐ.ምዕ.፩ ቁጥር ፩–፲፰። ፫፥፲፰ ፩ቆሮ.፰፥፮።) ሃይማኖተ አበው ዘአቡሊድስ ምዕ.፵፫ ቁጥር ፭–፮ ክፍል ፩።

በዚህም ተዐቅቦ የሥግው ቃል ተዋሕዶ ተጠነቀቀ፤ ታወቀ። ይህ ተዐቅቦ ባይኖር የአውጣኪን ግንጥል ሐሳብ ለተከተለ ሰው የተዋሕዶ እምነቱንና በቅዱሳት መጻሕፍት ያለው የአተረጓጐሙን መንገድ ያቃውስበት ነበር።

መናፍቃን «ኮነ» ያለውን ይዘው «በትረ ሙሴ ኮነት ዓርዌ ምድር» የሙሴ ብትር ዓርዌ ምድር እባብ ሆነች» ዘጸ.፬ ቁጥር ፫።

«ብእሲተ ሎጥ ኮነት ሐወልተ ጼው ማለት የሎጥ ሚስት የጨው ሐውልት ሆነች» ዘፍ. ምዕ.፲፱ ቁጥር ፳፮) የሚለውን ገጸ ንባብ ይዘው ምሥጢሩን ሳይመረምሩ መለኮቱ ተለውጦ ሥጋ ሆነ ብለው ለተነሱ መልሱ «ኀደረ» አለባችሁ «ኀደረ» ብለው ለተነሱ መናፍቃን ደግሞ «ኮነ» አለባችሁ በማለት በኀደረ «የተነሱ መናፍቃን በ«ኮነ» በ«ኮነ» የተነሱ መናፍቃን በ«ኀደረ» ይረታሉ።

ማስጠንቀቂያ «ወበከመ ኀደርኩ ምስለ ሙሴ ከማሁ ኀደርኩ ምስሌከ ማለት ከሙሴ ጋር እንደ ሆንኩ እንዲሁ ከአንተ ጋር መሆኔን፤ እንዳለው አይደለም) ኢያሱ ምዕ.፫ ቁጥር ፯።

እግዚአብሔር በነቢያት፤ በሐዋር ያት፤ በሊቃውንት፤ በቅዱሳን እንደ ሚያድር በሥጋ ማርያም አደረ አይባልም።

«ወኢኀደረ ውስቴቱ ዘከመ ኮሎ ሰብ አላ ለሊሁ ነሥአ ሥጋ ሎቱ ለባሕቲቱ ወአስተዓመር በተዋሕዶ። አኮ ከመ ኮሎሙ ነቢያት ዘሰፍሐ ቦሙ ወተናገረ ውስቴቶሙ አላ ኮነ ሰብአ ፍጹመ ቃል ሥጋ ኮነ ወኢተ ወለጠ ኢያፍላሰ መለኮቶ ኀበ ከዊነ ትስብእት፤ ወረሰየ ፍጹሜሁ ቅድስተ በብርሃን ምስለ መለኮት»

በሰው ሁሉ እንደሚያድርም አላደረበትም፤ እርሱ ሥጋን ነስቶ ለእርሱ ለብቻው ገንዘብ አደረገው እንጂ። አድሮ እንደ ተናገረባቸው እንደ ነቢያት ሁሉ አይደለም። ፍፁም ሰው ሆነ እንጂ ቃል ሥጋ ሆነ አልተለወጠም፤ መለኮቱን ሰው ወደ መሆን አልለወጠውም። ከመለኮት ጋር ጽኑዕ አንድነቱን በተዋሕዶ አደረገ እንጂ። (ሃይማኖተ አበው ዘኢጲፋንዮስ ምዕ.፶፮ ቁጥር ፳፮–፳፰።

በዚህም «ቃል ሥጋ ኮነ» ቃልም ሥጋ ኾነ አለ እንጂ ኀደረ በሥጋ አላለም። የመለኮትና የትስብእትን ተዋሕዶ የሚያስረዳ የነፍስ የሥጋ ተዋሕዶ ባይኖር ኖሮ በየጊዜው እንደ አሸን የሚፈሉ መናፍቃን ሰውን ሁሉ እያሳቱ በክህደት ማዕበል ባናወጡት ነበር። ✣

www.ethiopianorthodox.org

# እስትጉቡእ

(እስትጉቡእ:- ጥርቅም፣ የተቀመመ፣ የተሰባሰበ ማለት ነው)

ካሕሳይ ገ/እግዚአብሔር

## በፍልስጥኤም ምድር በ፭ኛው ክፍለ ዘመን የታነጸ ቤተ ክርስቲያን በቁፋሮ ተገኘ

በሮማውያን (ቤዛንታይን) ዘመን በ፭ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተሠራ አንድ አስደናቂ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን በእስራኤል ቁጥጥር ሥር ባለው የጋዛ ሰርጥ (ፍልስጥኤም ግዛት) በከርሠ ምድር (አርኪዮሎጂስቶች) ተመራማሪዎች አማካኝነት በቁፋሮ ተገኝቷል።

በመጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ ስም የታነጸው ይህ ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን ፲፫ በ ፳፭ ሜትር ስፋት ያለው ነው። የቤተ ክርስቲያኑ ጣራ ከመፍረሱ በስተቀር የሕንፃው ግንብ፣ በምርጥ እብነበረድ የተሠራው የቤተ መቅደሱ ወለል፣ የግድግዳ ላይ ስዕሎችና በግሪክ ቋንቋ የተፃፉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ምንም ዓይነት ጉዳት ሳይደርስባቸው መገኘታቸው ታውቋል።

ይህንን ታሪካዊ ቤተ ክርስቲያን በቁፋሮ ያገኙት የከርሠ ምድር ተመራማሪ ያዕቆብ ሐስተር እንዳሉት ቤተ ክርስቲያኑ የፈረሰው በ፲፱፻፴፬ ዓ.ም ተደርጎ በነበረው የዓረቦች ወረራ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም። ቤተ ክርስቲያኑ በጦርነት ወይም በእሳት መፈራረሱን የሚያመለክቱ ማስረጃዎች ባይገኙም በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ከነበሩት የተለያዩ ስዕሎችና ቅርጾች ጉዳት የደረሰባቸው የመስቀል ምስሎች ብቻ መሆናቸው ድርጊቱ የዓረባውያን መሆኑን ያመለክታል ባይ ናቸው ምሁሩ።

ከጥፋት የተረፈው የቤተ ክርስቲያኑ ቀሪ ክፍል ከነበረበት ሁኔታ ብዙም ሳይለወጥ የቆየበት አንዱ ምክንያት የወቅቱ ወራሪዎች ፍርስራሹን ሦስት ሜትር ጥልቀት ባለው አሸዋ ደፍነውት (ቀብረውት) በመሄዳቸው ነው። አሸዋው የግድግዳ ላይ ስዕሎችንና ቅርጾችን ለዘመናት ሳይበላሹ እንዲቆዩ በማድረግ በኩል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጉን ተመራማሪዎች ደርሰውበታል።

በሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጣዊ ክፈል (ግድግዳ) ተጽፈው ከተገኙት ጥቅሶች መካከል «ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን ለአምላክ ለመድኃኒታችን እልል እንበል» መዝ.፺፭፥፩።

«አንተም በመግባትህ ብሩክ ትሆናለህ በመውጣትህም ብሩክ ትሆናለህ» ዘፍ.፳፰፥፯። የሚሉ ይገኙባቸዋል። ከዚህም በላይ በቤተ ክርስቲያኑ መግቢያ በር በልዩ ኅብረ ቀለም ያጌጠ አይከን ተንጠልጥሎ ተገኝቷል። ይህ በልዩ ጥበብ የተሠራው አይከን በላዩ ላይ ጽሑፍም አለበት። ከዚህ ባለ አሥራ አንድ መስመር ጽሑፍ ውስጥ ቤተ ክርስቲያኑ በመጥምቁ ዮሐንስ ስም መታነጹን፣ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑ በ፭፻፵፬ ዓ.ም ተጀምሮ በ፭፻፶ ዓ.ም መፈጸሙን ይገልጻል። ቪክቶርና ዮሐንስ የተባሉ ምእመናን ለቤተ ክርስቲያኑ ሕንፃ ሥራ የላቀ አስተዋጽኦ ማበርከታቸውን በዚህ አይከን ሰፍሮ የተገኘው ጽሑፍ በተጨማሪ ያስረዳል።

ያዕቆብ ሐስተር በአይከኑ ላይ የአስተዳዳሪው (የአበምኔቱ) ስም አለ መጠቀስ ቤተ ክርስቲያኑ በጥቂት ምእመናን ተሳትፎ መሠራቱን፣ በአካባቢውም የነበረው ሕዝብ አነስተኛ መሆኑን ይጠቁማል ብለዋል። ከዚህ በላይ ግን የዚህ ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያን በአካባቢው መገኘት በሮማው ጁስታንያን ቆስጠንጢኖስ (የአገዛዝ ዘመን) በ፮ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ በፍልስጥኤም ምድር በርካታ አብያተ ክርስቲያናት ተገንብተው እንደነበር ያሳያል።

የመጥምቁ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን በአሁኒቱ ፍልስጥኤም እምብርት መገኘት ሌላ የሚያመለክተው ቁም ነገርም አለ። በእስራኤላዊቷ በአሽቆሎን ከተማና በጋዛ መካከል ያለው ቦታ ከጥንት ጀምሮ የክርስቲያኖች መኖርያ አካባቢ እንደ ነበር በተጨባጭ የተረጋገጠበት አጋጣሚም ነው።

የጋዛ ሰርጥ እ.አ.አ በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም በተደረገው የአረቦች እስራኤል ጦርነት ወቅት በእስራኤል የተያዘ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ከፊሉ በፍልስጥኤም ራስ ገዝ ሥር ቀሪው ደግሞ ለአይሁዶች ሠፈራና ለእሥራኤል ጦር ሠፈርነት እያገለገለ ይገኛል። የአሁኑ የመጥምቁ ቅዱስ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን የተገኘው በአጋጣሚ እዛ አካባቢ የነበረው አሸዋ ለሌላ ሥራ እንዲነሳ (እንዲጠረግ) በተደረገበት ወቅት ነበር። ይህ ታሪካዊ ቤተ ክርስቲያን የተገኘው እስራኤል በጦር ሠፈርነት በምትገለገልበት ቦታ በመሆኑ ተጨማሪ የቁፋሮና የምርምር ሥራ ማከናወን አልተቻለም።

ቀደም ሲልም አሁን በቁፋሮ ከተገኘው የመጥምቁ ዮሐንስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ በአሠራራቸው እጹብ ድንቅ የተሰኙ የገላ መታጠብያና የዓሣ ማራብያ ገንዳዎች በቁፋሮ ተገኝተው ነበር። የከርሠ ምድር ተመራማሪው ያዕቆብ ሐስተር «አሁንም የቤተ ክርስቲያኑ ሙሉ አካል ገና ተቆፍሮ አልወጣም፣ በአካባቢው በአሸዋ ተቀብረው የሚገኙ በርካታ ቅርሶች ይገኛሉ በመሆኑም የእስራኤል ወታደራዊ ባለ ሥልጣናትን በማስፈቀድ ተጨማሪ የምርምር ቁፋሮ ለማካሄድ እቅዱ አለኝ ለዚህም መንግሥት ይተባበራል የሚል እምነት አለኝ» ብለዋል።

ምንጭ:- ኢኩሙኒካል ኢንተርናሽናል ኒውስ ቡለቲን ፲፮ ማርች ፲፱፻፺፱

## የመናፍቃን ዘመቻ

«...በክርስትናው እምነት ከቅዱስ ወንጌል የምንማረው «አንድ እግዚአብሔር፣ አንድ ሃይማኖት፣ አንዲት ጥምቀት» የሚል ነው። በዚህ መሠረት ያመነውንና የተጠመቀውን በትምህርተ ወንጌል የሚመራውን ክርስቲያን አስተምራለሁ አሳምናለሁ ማለት ክርስቶስንና ክርስትናውን መከፋፈል ነው። ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስም ያስተማረው «...ከኢየሩሳሌም ጀምሬ እስከ እልዋሪቆን ድረስ እየዞርሁ የክርስቶስን ወንጌል ፈጽሜ ሰብኬአለሁ። እንዲሁም በሌላው ሰው መሠረት ላይ እንዳልሠራ የክርስቶስ ስም በተጠራበት ስፍራ ሳይሆን ወንጌልን ለመስበክ ተጣጣርሁ...» በማለት ነው።

የሚስዮናውያኑ ዘመቻና እንቅስቃሴ ከዚህ እምነትና ዓላማ አንፃር ሲመለከቱት በብዙ መልኩ የተለየና የራቀ ነው። የሚሸን ተግባር እውነት ከሆነ የወንጌል ብርሃን ወደ አልደረሰበት፣ የክርስትና እምነት ወደ አልተሰበከበት አካባቢ ሄዶ ማስተማር ማሳመንና ማጥመቅ ሲሆን ባመነና በተጠመቀ ሕዝብ መካከል ገብቶ ቤተሰብን ከቤተሰብ፣ ሕዝብን ከሕዝብ ማለያየት የሚያመለክተው ከወንጌሉ በስተጀርባ ስውር ዓላማና ተልእኮ መኖሩን ነው»

(«ዘመቻ ፌሊጶስን» በተመለከተ ሐምሌ ፲፱፻፺ ዓ.ም ከወጣው መግለጫ የተወሰደ)

## ሐውልትና ቀብር

«...የክርስቲያኖች ሐውልት ቤተክርስቲያን ናት፤ አማንያን በአርባ፣ በሰማንያ ቀን እየተጠመቁ ከአብራክ መንፈስ ቅዱስ ከማሕጸነ ዮርዳኖስ በመወለድ ከሥላሴ ልጅነትን ይቀበሉባታል። ከዚህ ዓለም በሞተ ሥጋ በሚለዩበትም ጊዜ የዕረፍት ቦታቸው ናት። ቤተክርስቲያን የጸሎት፣ የመስዋዕት ቦታ ከመሆኗም በላይ በተስፋ ትንሣኤ የሚታረፍባት ስለሆነች ሲያዩት ደስ በሚያሰኝ፣ ሲመላለሱበት ኅሊናን በሚስብ ንጽሕና መጠበቅ ይኖርባታል እንጂ የሐውልት መከማቻ ልትሆን አይገባም።

ሐውልት የሞተን ወገን በቋሚ ዘንድ ስለሚያዘናጋ፣ በዚሁ በምድር ላይ እንዳለ አድርጎ ስለሚያሳስብ ትንሣኤን የሚያስረሳ አፍአዊ ምልክት (ከንቱ መለያ) ነው።»

✣ ✣ ✣

«...በመካነ መቃብራችን መስቀል አለ። መስቀል ለኛ የሕይወት ጥላ ነው። በረከተ ሥጋንና በረከተ ነፍስን አስገኝቶልናል ብለን እናምናለን። በምንሞትበትም ጊዜ እንደ ቤተክርስቲያናችን ቀኖና በጸሎተ ፍትሐት፣ በዕጣን፣ በመሥዋዕት፣ እንሸኛለን፤ አሁን በመካነ መቃብር እንዛመድ የሚሉን ግን ይህን ሁሉ አይቀበሉም፣ አይፈጽሙም «ሥጋውን ደሙን መታሰቢያ ነው» ይላሉ። እኛ ግን የምንቀበለው አማናዊ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር፣ ደሙንም አማናዊ ደመ ወልደ እግዚአብሔር ብለን ነው። ባጠቃላይ በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንገናኝም። ስለዚህም በትምህርተ ሃይማኖትና በቀኖና ቤተክርስቲያን የማይመስሉንን በምሥጢራተ ቤተክርስቲያን ከኛ ጋር አንድነት የሌላቸውን በመካነ መቃብር አንቀበልም።»

«ሃይማኖት የለየንን መቃብር አንድ አያደርገንም» በሚል ርእስ መስከረም ፲፱፻፹፯ ዓ.ም ከታተመው መጽሐፍ የተወሰደ

## መክሰስ (ጠቅላላ ዕውቀት ለታዳጊዎች)

ከዓለማችን:-

ትልቁ ክፍለ ዓለም – ኤሲያ

ትልቁ ተራራ – ኤቨረስት (ኔፓል) ፰ ሺህ ፰ መቶ ፵፰ ሜ.

ትልቁ ባሕር – ደቡብ ቻይና ባሕር

ትልቁ ውቅያኖስ – ፓስፊክ (፩ መቶ ፷፭ ሚሊዮን ፫ መቶ ፹፬ ሺህ ስክዌር.ኪ.ሜ.)

ትልቁ ምድረ በዳ – ሰሐራ (አፍሪቃ)

ትልቁ ደሴት – ግሪንላንድ (ሰሜን አትላንቲክ) ፪ ሚሊዮን ፩ መቶ ሮ፷ ሺህ ፮ መቶ ስክዌር.ኪ.ሜ.

ረዥሙ ወንዝ – ናይል (ዓባይ) ፮ ሺህ ፮ መቶ ፸ ኪ.ሜ

ረዥሙ ፏፏቴ – አንገል ፏፏቴ (ቬኑዙላ) ፱ መቶ ፶፮ ሜ.

ዝቅተኛ ስፍራ – ሙት ባሕር (እስራኤል)

ጥልቅ ውቅያኖስ – ማሪዮናስ ስትሬንች (ፓስፊክ) ፲፩ ሺህ ሜ

ትልቁ እርጥብ መሬት – ዊያ አለ አለ ተራራ (ሐዋይ)

በጣም ደረቅ ቦታ – አታካማ ምድረ በዳ (ቺሌ)

ረዥሙ ግንብ – ቻይና ግንብ (፪ ሚሊዮን ፬ ሺህ ኪ.ሜ)

✣ ✣ ✣

የምድር ወገብ ዙርያ – ፬ ሚሊዮን ፪ ሺህ ፯ መቶ ፶፮ ኪ.ሜ

የፀሐይ ወገብ ዙርያ – ፬ ሚሊዮን ፫ መቶ ፶፪ ሺህ ኪ.ሜ

የጨረቃ ወገብ ዙሪያ – ፫ ሺህ ፬ መቶ ሮ፮ ኪ.ሜ

የፀሐይ ሙቀት – ፲፭ ሚሊዮን $^0$.ሴ.

✣ ✣ ✣

- ከዓለማችን ሕዝብ መካከል ፹% ከምድር ወገብ በላይ ባለው የዓለማችን ክፍል ይኖራል።
- መሬት ከጨረቃ አራት እጅ ትበልጣለች
- ፓስፊክ ውቅያኖስ በስፋት የእስያ ክፍለ ዓለምን በሦስት እጅ ይበልጣል
- የወረቀት ገንዘብን ለመጀመርያ ጊዜ ሠርተው የተጠቀሙት ቻይናውያን ነበሩ፤ በ፰መቶ ዓ.ዓ

www.ethiopianorthodox.org

- የመጀመርያው ባንክ የተከፈተው በ፩ ሺህ ፩ መቶ ፷፩ ዓ.ም በኢጣልያ ሀገር ነበር።
- የዓለማችን የመጀመርያው የትያትር ት/ቤት የተመሠረተው በቻይና በ፰ ዓ.ዓ ሲሆን ፒርጋርደን ተብሎ ይጠራ ነበር።
- ትልቁ የዓለማችን እንስሳ ሰማያዊ ዓሣ ነባሪ ነው
- ከእንቁላል ጣይ እንስሳት በአንድ ጊዜ በርካታ እንቁላል በመጣል የምትታወቀው ኦሸን ሰንፊሽ (Ocean Sunfish) የተባለች የዓሣ ዝርያ ስትሆን በአንድ ጊዜ ፴ ሚሊዮን (ሠላሳ ሚሊዮን) እንቁላሎችን ትጥላለች
- ትልቅ እንቁላል የምትጥለው ደግሞ ሰጎን ናት። አንድ የሰጎን እንቁላል ከ፲፭–፳ ሴ.ሜ. የሚደርስ ቁመትና .፩.፯ ኪ.ግ ክብደት አለው። አንድ የሰጎን እንቁላል ለመብሰል ቢያንስ ለ፵ ደቂቃዎች ያህል መቀቀል አለበት።
- ከወፎች በጣም ትንሽ እንቁላል የምትጥለው ቫሪቬይን የተባለች ወፍ ናት። የቫሪቬይን እንቁላል ቁመት ከ፲ ሚ.ሜ ያነሰ ሲሆን ክብደቱ .፴፯ ግራም ብቻ ነው።
- ትልቅ ምላስ ያለው እንስሳ ዓሣ ነባሪ ሲሆን የአንድ ዓሣ ነባሪ ምላስ ከ፬.፭ ቶን በላይ ይመዝናል።
- ትልቅ አንጐል ያለው እንስሳም ስፐርም የተባለው የዓሣ ነባሪ ዝሪያ ሲሆን የአንጐሉ ክብደት ፱.፪ ኪ.ግ ነው።

## እንዲህም ተፈርዷል

አንድ ጊዜ አፄ ቴዎድሮስ ዘመቻ ሲሄዱ በአንድ አገር ሰፍረው ሰነበቱ። በጊዜው በነበረው አሠራር መሠረት ወታደሩ በየአርሶአደሩ ቤት ተመራ። ከወታደሮቹም አንዱ ባንዲት ድኻ ሴት ቤት ተመርቶ ነበርና የነበረቻትን ብቸኛ ሀብት አንዲት ዶሮዋን ከጫጩቶቿ ነጥሎ አርዶ በላባት። በማግስቱም ንጉሡ በበቅሎ ተቀምጠው ጉዞ እንደ ጀመሩ ያች ድኻ ሴት ፲፪ ጫጩቶች በወንፊት ይዛ «ጃንሆይ እግዚአብሔር ያሳይዎ ክርስቶስ ያመልክትዎ እኔ ባርያዎ ሴት ድኻ ስለ ኾንኩ አንዲት ዶሮ ነበረችኝና እሷኑ እያረባሁ ያመት ልብሴንና የለት ጉርሴን ችላኝ ትኖር ነበር። ነገር ግን ትላንትና አንዱ ወታደር አርዶ በላብኝ» አለችና ጮኸች።

እሳቸውም «የኔ አሽከር እንኳን ዶሮና በሬስ አርዶ ቢበላ ምናለበት» ብለው ወታደሩን አስጠሩት። እንደመጣም «በሬም አርደህ ብትበላ ግድ የለም ብቻ እውነቱን ንገረኝ።» ቢሉት ድርጊቱን አመነ። ከዛ «ቆማጣ ቆመጥማጣ እንግዲያማ እነዚህ ጫጩቶች እናታቸው ሙታባቸው ታቅፎ የሚያሳድጋቸው የለምና ያሳዝናሉ፣ ብርድና ችጋርም ይገድላቸዋል፣ ንሳማ እናታቸው ዘንድ ደብላቸው (ቀላቅላቸው) እናታቸው ትታቀፋቸው» አሉና ከበቅሎአቸው ተቀምጠው እንደቆሙ ፲፪ቱን ጫጩቶች አስዋጡት። ለድኻዋም ገንዘብ ሰጥተው ሸኙዋት።

> **ተጠንቀቁ**
>
> ኃጢአት – ምቀኛ ነው – ከፈጣሪ ይለያል
> ኃጢአት – ስስታም ነው – ወንድሙን ይጠላል
> ኃጢአት – ጨካኝ ነው – ለእሳት ይዳርጋል
> ኃጢአት – ቆሻሻ ነው – ሰዎችን ያረክሳል
> ኃጢአት – ክፉ ነው – ወንድሙን ይገድላል
>
> ከመክሊት

## ምድሪቱ ትመስክር

ራስ እምሩ (ደጃዝማች እያሉ) ሐረርጌን ይገዙ በነበረበት ጊዜ አንድ ሰው ሁለት ሰዎች ጉድጓዳ (ሰዋራ) ቦታ ጠብቀው ከደበደቡኝ በኋላ ገንዘቤን ቀምተውኛል ሲል ከሰሰ። ራስ እምሩ ዘንድ ተከሰው የቀረቡት ሁለት ተከሳሾችም «ሀሰት አንተን ደብድበን ገንዘብህን መቀማት የለብንም ከፈለግክ ርታን አሉት» ራስ እምሩም ከሳሹን «ለመሆኑ ምስክር አለህ ወይ» ቢሉት «የለኝም» አላቸው። በል «እስጥ ብለህ ተወራረድና ገንዘብህን የቀሙባትን ምድር ምስክር ቁጠራት» አሉት።

እሱም እንዳዘዙት ተወራርዶ ምድሪቷን ምስክር ከቆጠረ በኋላ ራስ እምሩ አመሳካሪ ዳኛ ጨምረው አንዱን ተከሳሽ ከሳቸው ጋራ አስቀርተው ከሳሽ ከሁለተኛው ባላጋራው ጋራ ምድሪቷን ዕወቂልኝ እንዲል ላኩት። ከዚህ በኋላ ትንሽ ቆይተው እሳቸው ጋራ የቀረውን ተከሳሽ «አንተ እነዚያ ሰዎች ይኸን ጊዜ ከቀማችሁበት ቦታ አይደርሱምን?» ብለው ቢጠይቁት «አይደርሱም» ብሎ መለሰላቸው። ራስም ሰው ልከው እነዚያ በቶሎ እንዲመለሱ አደረጉ። ከተመለሱ በኋላም ሊመሳከር የሄደውን ቀማኛ «ባለንጀራህ እውነቱን ተናግሯልና አንተም እውነቱን አውጣ» አሉት። እሱም «አዎን ደብድበን ገንዘቡን ቀምተነዋል» ብሎ አመነ፤ ሁለቱም ተቀጡ። ✣

# የዘመን አቈጣጠር

ከመ/ር ያሬድ ፈንታ

## ዓመተ አዳም ወኖኅ



**ዓ**መተ አዳም ወኖኅ ማለት አዳምና ኖኅ ዘመናትን ይቈጥሩበት የነበረ የጊዜ አቈጣጠር ሥርዓት ነው። ሙሴም ይህን የጊዜ አቈጣጠር ሥርዓት ተከትሎ የአበውን ትውልድና ዕድሜ ሲጽፍ አዳም የኖረበት ዘመን ዘጠኝ መቶ ሠላሳ ዓመት ሆነ፣ ሞተም ብሎ ይገሯምርና አዳም በተፈጠረ በ፪ ሺህ ፪ መቶ ፶፯ ዓመት በኖኅ ዕድሜ በስድስት መቶኛው ዓመት በሁለተኛው ወር ከወሩም በ፲፯ኛው ቀን ማየ አይኅ ዘንሞ በምድር ላይ መቶ አምሳ ቀን ከቈየ በኋላ ውኃው ጐደለ። የኖኅ መርከብም በ፯ኛው ወር ከወሩም በ፲፯ኛው ቀን በአራራት ተራሮች ላይ ዐረፈች ይላል።

ሙሴ በሁለተኛው ወር ማየ አይኅ ዘነመ፣ በሰባተኛው ወር መርከቢቱ በተራራ ላይ ዐረፈች ብሎ የጻፈው እሑድን መነሻ በማድረግ ነው። ምክንያቱም ሁለትር ወር ሰባት ወር ብሎ ለመጻፍ መሠረቱ አንድ ብሎ መዠመር ነውና። ስለዚህ እሑድ መጋቢት ፳፱ ቀን ጥንተ ፍጥረት፣ ጥንተ ዕለት ጥንተ ዘመን መሆንዋ በዚህ ይታወቃል። ሁለተኛ ወር የተባለው ግንቦት ሲሆን ሰባተኛ ወር የተባለውም ጥቅምት ነው። ይህም ከግንቦት ፲፯ ቀን እስከ ጥቅምት ፲፯ ቀን ያለው የዕለታት ቁጥር የ፶ ቀን ይሆናል። የ፶ ቀን በዐውደ ወርኅ ሲሰፈር አምስት ወር ይሆናል። እንዲህም የሚሆነው በአዳምና በኖኅ የጊዜ አቋጣጠር ሥርዓት እንጂ በሌሎቹ የጊዜ አቀጣጠር ሥርዓት እንዲህ ትክክል አይመጣም።

በጥንት ዘመን ዓመታት የሚቈጠሩባቸው ልዩ ልዩ የቀን መቁጠሪያዎች ነበሩ። ማየ አይኅ በምድር ላይ የቈየበት ቀን በእነሱ አቈጣጠር ሥርዓት ቢቆጠር ያንሳል ወይም ይበዛል እንጂ ትክክል የ፶ ቀን ወይም ፭ ወር ሊሆን አይችልም።

ምሳሌ (ሀ) የቀድሞ ሮማውያን አቆጣጠር ሥርዓት የየወሩ ምድብ ቀን ፴፮ ሆኖ የዓመቱ ወሮች ዐሥር ብቻ ናቸው፣ የአምስት ወር ቀንም ድምር የ፩ መቶ ፹ ቀን ይሆናል።

ለ. የቀድሞ ዮናናውያን አቈጣጠር ሥርዓት የየወሩ ምድብ ቀን አንድ ጊዜ ሠላሳ ሌላ ጊዜ ሠላሳ አንድ ሆኖ የአምስት ወር ቀን ድምር የ፶፫ ቀን ይሆናል።

ሐ. የጨረቃ አቈጣጠር ሥርዓት የየወሩ ምድብ ቀን አንድ ጊዜ ፳፱ ሌላ ጊዜ ፴ ሆኖ የ፭ ወር ቀን ድምር ፩ መቶ ፵፯ ይሆናል።

መ. የኢትዮጵያ የዘመን አቈጣጠር ሥርዓት ግን በዓመተ አዳም ወኖኅ አቈጣጠር ሥርዓት የተመሠረተ ስለሆነ ማየ አይኅ በምድር ላይ የቈየው የ፶ ቀን ወይም ፭ ወር እንደሆነ በትክክል ያስረዳል። ያውም እንዲህ ነው። የየወሩ ምድብ ቀን ፴ ሆኖ የ፭ ወር ቀን ድምር የ፶ ቀን ይሆናል። ይህም እግዚአብሔር ለሙሴ የገለጸለት የጊዜ አቈጣጠር መንገድ ነው።

«ወከሠተ እግዚአብሔር ለሙሴ ከመ ኍልቈ ኃምስቱ አውራኅ ምእት ወኃምሳ ዕለት ውእቱ። ወበዝንቱ ቃል አንቅሐ ለእእምሮ ዓመተ አዳም ወኖኅ» እንዲል አቡሻክር።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም ከላይ እንደተገለጸው አዳምና ኖኅ ሙሴም ባስተማሩት ሐሳበ ዘመን መሠረት ዓለም መጋቢት ፳፱ ቀን ተፈጠረ። ወቅቱም እንደ ዕብራውያን አቈጣጠር ከአራቱ ክፍላተ ዓመት አንዱ ዘመነ መፀው ነው። መፀውም ጥንተ ዓመተ ዓለም ይባላል። ምክንያቱም ሰማይና ምድር በውስጣቸው ያለው የፍጡራን ወገን ሁሉ የተፈጠሩበት ወቅት ስለሆነ ነው ብላ ታስተምራለች።

ዳግመኛም በዘመነ መፀው በኀጢአት ተበላሽቶ የነበረው ዓለም፣ ሕይወተ ነፍስ አጥቶ ደክሞ የነበረው የሰው ልጅ ባሕርይ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ታድሷል።

ሦስተኛም በዘመነ መፀው ክርስቶስ ዳግመኛ ይመጣል፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ይደረጋል ተብሎ በቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፏል። በሊቃውንት ተተርጉሟል።

ዛሬ ባራቱ ክፍላተ ዓመት ማለት በክረምት፣ በመፀው፣ በሐጋይ፣ በጸደይ፣ ጊዜያቸውን ጠብቀው የሚያድጉት የሚያብቡትና የሚያፈሩት ዛፎች ሁሉ ያን ጊዜ ምድር ሣርና ቡቃያን ታውጣ በሚለው መለኮታዊ ትእዛዝ ባንዲት ዕለት በሠሉስ አብበው አፍርተው ተገኝተዋል። ከዚያ ወዲህ ግን ብዙ ተባዙ በሚለው መለኮታዊ ትእዛዝ መሠረት ተፈጥሯቸው ግብር እምግብር ስለሆነ ጊዜያቸውን ጠብቀው ያድጋሉ

www.ethiopianorthodox.org

ያብባሉ፣ ያፈራሉ። ይህም በእግዚ አብሔር ዘንድ አንድ ቀን በሰው ዘንድ አንድ ሺሕ ዓመት መሆኑን ያስረዳል። (ዘኍ.፲፬፥፴፬) አቡሻክር

ማክሰኞ የብስ የታየባት፣ ማያት በተወሰነ ቦታ የተከማቹባት የመገሮመ ሪያው ወር የባተባት አራቱ ክፍላተ ዓመት የታወቁባት ቀመር የተገሮመ ረባት ስለሆነች ጥንተ ቀመር ትባላ ለች። በዘመነ ሐዲስም ፍሬ ሕይወት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለ ደባት በጌታችን ጥምቀትም ማያት የተቀደሱባት ስለሆነች ጥንተ ጥምቀት ትባላለች።

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንም ከዚህ በላይ የተገለጸውን ሐሳብ መሠረት በማድረግ ዓለም እሑድ መጋቢት ፳፱ ቀን ተፈጠረ፣ የዓለም መድኃኒት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እሑድ መጋቢት ፳፱ ተፀነሰ፣ እሑድ መጋቢት ፳፱ ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፣ እሑድ መጋቢት ፳፱ ዳግመኛ ይመጣል ብላ ታስተምራለች። ይህም ትምህርት ታላላቅ የሆኑ የእግዚ አብሔር ሥራዎች የተፈጸሙበትና የሚፈጸሙበት ቀን እሑድ መሆኑን ያስረዳል። እሑድ ማለት ፍጥረት የተገሮመረበት ቀን ማለት ነው። መገሮመርያ ወይም መነሻ የሆነ ሁሉ አንድ ወይም እሑድ ተብሎ ይቈጠራል። መነሻን የሚከተል ደግሞ ሁለት ወይም ሠኑይ ይባላል። እንዲህ እየተቆጠረ እስከ መጨረሻው ደርሶ ቀድሞ ወደነበረበት ይመለሳል። ለተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ሥርዓቱ እንዲህ ነውና።

የብሉይና የሐሳበ ዘመን ሊቃውንትም የዘመናትን ታሪክ ሲጽፉና ሲያስተምሩ ከቀዳማይ አዳም እስከ ዳግማይ አዳም ያለውን ዘመን እንዲህ ከፍለውና ደምረው ጌታችን የተወለደበትን ዓመት ለይተው ያመላክታሉ። ይህም

ከአዳም እስከ ኖኅ – ፪ ሺህ ፪ መቶ ፶፮ ዓመት

ከኖኅ እስከ ሙሴ – ፩ ሺህ ፭ መቶ ፹፰ ዓመት

ከሙሴ እስከ ሰሎሞን – ፭ መቶ ፺፫ ዓመት

ከሰሎሞን እስከ ክርስቶስ – ፩ ሺህ ፷፫ ዓመት

ከአዳም እስከ ክርስቶስ – ፭ ሺህ ፭ መቶ ዓመት

ይህም ዓመተ ፍዳ፣ ዓመተ ኩነኔ ተብሎ ይታወቃል። ከጌታችን ልደት ወዲህ እስከ ዛሬ ያለው ዘመንም ፲፱፻፺፪ ዓመት ነው። ይህም ዓመተ ሥጋዌ ይባላል። ከክርስቶስ ልደት በፊትና በኋላ ያለው ዘመን ሲደመርም ፭ ሺህ ፭ መቶ+ ፲፱፻፺፪= ፯ ሺህ ፬ መቶ ፺፪ ዓመት ዓመተ ዓለም ይባላል። ፯ ሺህ ፬ መቶ ፺፪ ዓመት በ፭ መቶ ፴፪ ዐቢይ ቀመርና በ፲፱ ንኡስ ቀመር ሲቀመር ፲፬ ዐቢይ ቀመር ፪ ንኡስ ቀመር ሆኖ ፯ ዓመት አበቅቴ ይተርፋል። ከ፯ ዓመት አንድ ሲቀነስ ፭ ወንበር ይገኛል። በተገኘው ወንበርም የዘመኑ አበቅቴና መጥቅዕ ይታወቃሉ።

አበቅቴ ማለት ተረፈ ዓመት ማለት ነው። በተገኘው አበቅቴ ሠርቀ ሌሊትና ሠርቀ ወርኅ ይታወቃል። ጥንተ አበቅቴ ፲፩ ቀን ነው። ይህ በተገኘው የዘመኑ ወንበር ፭ ተባዝቶ በዐውደ ወርኅ ሲቀመር ፩ ወር ሆኖ ፳፭ ይተርፋል። ይህ የዘንድሮ አበቅቴ ነው።

መጥቅዕ ማለት አዋጅ የሚነገ ርበት ነጋሪት ማለት ነው። ከዕለታት ተውሳክ ጋራ እየተደመረ መባጃ ሐመርን ያስገኛል። በመባጃ ሐመርም አጽዋማትና በዓላት ይታወቃሉ። ጥንተ መጥቅዕ ፲፱ ነው። ይህ በተገኘው ፭ ወንበር ተባዝቶ በዐውደ ወርኅ ሲቀመር ፫ ወር ሆኖ ፭ ይተርፋል። ይህ የዘንድሮ መጥቅዕ ነው።

በ፲፱፻፺፪ ዓመተ ሥጋዌ መስከረም እሑድ፣ ጥቅምት ማክሰኞ ይከታል። ጥቅምት በባተ በአምስተኛው ቀን ቅዳሜ በዓለ መጥቅዕ ይውላል። የቅዳሜ ተውሳክ ፰ በ፭ መጥቅዕ ላይ ሲደመር ፲፫ ይሆናል። ይህ የዘንድሮ መባጃ ሐመር ነው። የካቲት ሮብ ይብታል። የካቲት በባተ በ፲፫ኛው ቀን ሰኞ ጾመ ነነዌ ይገባል። የዐቢይ ጾም ተውሳክ ፲፬ ከመባጃ ሐመር ፲፫ ላይ ሲደመር ፳፯ ይሆናል የካቲት ፳፯ ሰኞ ዐቢይ ጾም ይገባል። የደብረ ዘይት ተውሳክ ፲፩ በ፲፫ ላይ ሲደመር መጋቢት ፳፬ እሑድ ደብረዘይት የሆሣዕና ተውሳክ ፪ በ፲፫ ላይ ሲደመር ሚያዝያ ፲፭ እሑድ ሆሣዕና እንዲሁም በዓለ ፍሥሕ ይውላል።

የስቅለት ተውሳክ ፯ በ፲፫ ላይ ሲደመር ሚያዚያ ፳ ዓርብ ስቅለት በ፳፪ኛው ቀን እሑድ ትንሣኤ ይውላል። የረክበ ካህናት ተውሳክ ፫ በ፲፫ ላይ ሲደመር ግንቦት ፲፯ ረቡዕ ረክበካህናት፣ የዕርገት ተውሳክ ፲፰ በ፲፫ ላይ ሲደመር ፴፩ ይሆናል። ሠላሳው የግንቦት ወር ሆኖ ሐሙስ ሰኔ ፩ ቀን ዕርገት ይውላል። የጰራቅሊጦስ ተውሳክ ፳፰ በ፲፫ ላይ ሲደመር ፵፩ ይሆናል። ሰኔ በባተ በ፲፩ኛው ቀን እሑድ ጰራቅሊጦስ በ፲፪ኛው ቀን ሰኞ ጾመሐዋርያት በ፲፬ኛው ቀን ረቡዕ ጾመ ድኅነት ይገባል።

ሃሌ ሉያ ዮም በዘንዜከር ሐሳበተ ሕጉ ወትእዛዛቲሁ ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወሐሳበተ አዝማነ ዓለም ወሠርቀ አውራኅ ዘሌሊት ወዘመዓልት፣ እንዘ ሀሎነ በዘመነ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ ቡሩክ ያብጽሐነ እስከ ዘመነ ቅዱስ ማቴዎስ ዜናዊ አሜን። ✤

www.ethiopianorthodox.org